ወንጌላዊው ማቴዎስ: በእግዚአብሔር መንፈስ ተመልቶና ተመርቶ በጻፈው: በጌታ የትውልድ ሐረግ ውስጥ: ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው: "ኢትዮጵያዊ" ከሚያሰኘው: ከካም÷ ከሴምና ከያፌት: ከሦስቱም ነገዶች ተዋሕዶ ከተገኘው ዘር መኾኑን: ዘርዝሮ ገልጿል። ይኹን እንጂ: ኢየሱስ ክርስቶስ: የሰውነቱን አካልና ባሕርይ: ማለትም: ነፍስንና ሥጋን የወረሰው: ከእናቱ፤ ከድንግል ማርያም መኾኑን: ወንጌላዊው እያወቀ: በእርሷ በኩል ያለውን: የትውልድ ሐረግ መግለጡን ትቶ: በዮሴፍ በኩል ያለውን የዘረዘረው: ያለምክንያት አልነበረም። ይህ ዘዴው: ስለዮሴፍና ስለድንግል ማርያም ማንነትና መተጫጨት: ከጻፈው ጋር: ተመሳሳይ ኾኖ ይገኛል።

ዮሴፍ: ሰው የኾነውን አምላክና አምላክን የወለደችውን ድንግል እንዲጠብቅ: ከእግዚአብሔር የተመረጠ: ጻድቅና ደግ ሰው እንደነበረ: የወንጌላዊው ጽሑፍ የሚያመለክት ሲኾን: በይፋ ግን: ለምን: እርሱ: የማርያም "እጮኛዋ" ተብሎ÷ እርሷም: የዮሴፍ "እጮኛው" ተብሳ: ኹለቱም: በዚህ አጠራር እንዲታወቁ ኾኑ? ይህ አድራጎት: የሕፃኑ የኢየሱስና የእናቱ የድንግል ማርያም እውነተኛ ማንነት: በጊዜው እስኪገለጥ ድረስ: በተለይ: በአይሁድ ዘንድ: የማያስፈልግ ተቃውሞን እንዳያስከትል: በእግዚአብሔር የተዘጋጀ ረቂቅ ዕቅድ መኾኑ ግልጽ ነው። የዚህንም እውነታ: ሕፃኑ ኢየሱስ: ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ኾኖት: ሊያስተምር እስኪጀምር ድረስ: አይሁድ: *"የዮሴፍ ልጅ እያመሰላቸው"* ይኖሩ እንደነበረ: ወንጌላዊው ሉቃስ: በጻፈው: የጌታ የትውልድ ሐረግ ውስጥ አረጋግጧል። ማቴዎስም: በቀጥታ: የድንግል ማርያምን ሳይኾን: እንደዕብራውያን ልማድ: በዮሴፍ በኩል ያለውን: የትውልድ ሐረግ ብቻ የጻፈው: በዚህ መሠረት መኾኑ ይታመናል: ይኸውም: ሙሴ: በኢትዮጵያዊት ሚስቱ ምክንያት: ከወንድሙ: ከአሮንና ከእኅቱ: ከማርያም ሳይቀር: ከእስራኤላውያን የደረሰበትን ክፉ ተቃውሞ በማሰብ: ወንጌሉን በጻፈላቸው አይሁድ ዘንድ: መልእክቱ: ተቀባይነትን እንጂ: ያን የመሰለ ተቃውሞ እንዳያስከትልበት: ተጠንቅቆና ተጠብቦ የፈጸመው ስልት መኾኑ ነው።[ደ፲፬]

ድንግል ማርያም: "ኢትዮጵያዊት" በሚያሰኛት: በዘር አባቷ: በመልከ ጼዴቅ በኩል ከወረሰችው: ከእግዚአብሔር መንግሥት: የቤተ ሕዝብነት ሀብት: የምልክና ጸጋና የክህነት በረከት ጋር: በእስራኤል በኩል: ከዳዊት የወረደውን በትረ መንግሥትና ከአሮን የተላለፈውን ሥልጣነ ክህነት: አጣምራ ይዛ: ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ: እስከእርሷ ድረስ ተጠብቀው: በኹለት አግጣጫ የመጡትን: እነዚህን: የቅዱሱን ኪዳን መለኮታውያን ውርሶች: *"ቃል ሥጋ ኾነ!"* ለተባለው ልጇ: ለኢየሱስ ክርስቶስ: በማሕፀኗ አስረክባለች። ይህም: *"በይሁዳ ንጉሥ: በሄሮድስ ዘመን: ከአብያ ክፍል የኾነ: 'ዘካርያስ' የሚባል: አንድ ካህን ነበረ፤ ሚስቱም: ከአሮን ልጆች ወገን ነበረች፥"* ካለ በኋላ: *"መልአኩ ገብርኤል: 'ማርያም ሆይ! ...ወንድ ልጅን ትወልጃለሽ: ስሙንም: 'ኢየሱስ' ትዪዋለሽ፤...ጌታ አምላክም: የአባቱን: የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል።"...እነሆም: ዘመድሽ ኤልሣቤጥ: እርሷ ደግሞ: በእርጅናዋ: ወንድ ልጅን ፀንሳለች።"* በሚለው ቃል ተረጋግጧል።[ደ፲፭]

ምዕራፍ ፭፡ ስባቱ ቅዱሳት ኪዳናት፡ ስድስተኛው ቃል ኪዳን፡- ኪዳነ ዳዊት፡
ድንግል ማርያም፡ "ኢትዮጵያ" ስለመኾኗና
የኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊነት።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ኢትዮጵያዊ" ከሚያሰኘው፡ ከካም፥ ከሴምና ከያፌት፡ ከሦስቱም ነገዶች ተዋሕዶ ከተገኘው፡ ከመልከ ጼዴቅ ዘር፡ ሰው ኾኖ የተወለደው፡ ለምን እንደኾነ፡ የኹለቱም ወንጌላውያን፡ የትውልድ ሓረጎች፡ በግልጽ ያስረዳሉ።

ይኸውም፡-

፩ኛ፡- "የአብርሃም ልጆች ነን!" ብለው፡ በአብርሃም ቃል ኪዳን ይመኩ የነበሩትን፡ አይሁድን ብቻ ሳይኾን፡ ከቃል ኪዳኑ ውጭ ያሉትን አሕዛብን ጭምር፡

፪ኛ፡- "የኪዳነ አራትን መሥዋዕት በማቅረብ፡ ከኃጢአት እንነጻለን!" የሚሉትን ብቻ ሳይኾን፡ በኪዳነ ልቡና እየኖሩ፡ በኃጢአት ቀንበር ውስጥ የሚገኙትን ወገኖች ጭምር፡

፫ኛ፡- አንዱን፡ የሴምን ነገድ ብቻ ሳይኾን፡ የቀሩትንም፡ የካምንና የያፌትን ነገዶች ጭምር፥ ማለትም፡ በጠቅላላ፡ የሰውን ዘር በሙሉ ለማዳን መኾኑን ነው።

ይህም፡ በተለይ፡ ማቴዎስ በጻፈው የትውልድ ሓረግ ውስጥ፡ ከተመዘገቡት፡ ከሴማውያኑ የትውልድ አባቶች ጋር፡ ታላላቅ እናቶች የኾኑትን፡ ግራንና ርብቃን፡ ራሔልንና ልያን ሳይኾን፡ ከቃል ኪዳኑ ውጭ የኾኑትንና በኃጢአተኝነታቸው የታወቁትን፥ እንዲሁም፡ ከካምና ከያፌት ነገዶች የተመለዱትን፡ ትዕማርንና ራኬብን፥ ሩትንና ቤትሳባን (ቤርሳቤሀን) ብቻ በመጥቀሱ ይታወቃል።

"የዮሴፍና የድንግል ማርያም መተጫጨት የተፈጸመው፡ በዝምድና የተቀራረበ ወንድና ሴት በሚጋቡበት በዕብራውያን ልማድ ስለኾነ፡ ዮትውልድ ሓረጋቸው የተነገረው በድንግል ማርያም በኩል ሳይኾን፡ በወንዱ በኩል ያለው ነው።" የሚል ይትበሃል አለ፣ ይኹን እንጂ፡ ያ ልማድ፡ እዚህ ላይ፡ ከዚያው፡ ከመተጫጨት ደረጃ እንዳላለፈ፡ ከዚህ የተነሣም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም፡ ያለወንድ ዘር፡ ሰው ኾኖ እንደተወለደ፡ ወንጌላውያኑ ማቴዎስና ሉቃስ እያወቁ፡ የእናቱን የትውልድ ሓረግ፡ በመጻፍ ፋንታ፡ የዮሴፍን ብቻ የዘረዘሩት፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላቸው፡ ያለምክንያት አልነበረም፣ ያም ምክንያት፡ መልእክታቸውን፡ እንደዚያ አድርገው ባይጽፉት ኖሮ፡ የምሥራቹ ቃል፡ በአይሁድ ዘንድ፡ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል፡ አስቀድመው ስለተረዱት እንደነበረ፡ መገንዘብ የሚያዳግት አይደለም።

እነሆ፡ በመለኮት ባሕርዩና አካሉ፡ የእግዚአብሔር ልጅ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የሰውነቱን ባሕርይና አካል የወረሰው፡ እናቱንና እርሱን ልጇን እንዲያገለግል፡ ከእግዚአብሔር ከተመረጠውና በሰዎች ዘንድ፡ "የማርያም እጮኛ" ከተባለው፡ ወንጌላውያንም፡ እንደዕብራውያን ልማድ፡ የዘር ሓረጉን ከጻፉለት፡ ከዮሴፍ ሳይኾን፡ ከእናቱ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ መኾኑ፡ እንዲህ የታመነ ነው።

ይህም ነገር፡ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል፡ "እነሆ ትፀንሻለሽ! ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ!" ብሎ፡ እመቤታችንን ባበሠራት ጊዜ፡ "ወንድ ስለማላውቅ፡ ይህ፡ እንዴት ይኾናል?" ብላ ላቀረበችለት ጥያቄ፡ "መንፈስ ቅዱስ፡ በአንቺ ላይ ይመጣል፡ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል። ስለዚህ ደግሞ፡ ከአንቺ የሚወለደው፡ ቅዱሱ፡ 'የእግዚአብሔር ልጅ' ይባላል፡" ሲል ባስማት መልሰ፡ እሙን ኾኗል።

በዚህ፡ በመልአኩ ቃል ብቻ ሳይኾን፡ እግዚአብሔር አብ፡ ገና ጥንት፡ በዘመነ ፍጥረት፡ "አባብ" በተባለው፡ በዲያብሎስ ላይ፡ መለኮታዊ ፍርዱን ሲሰጥ፡ "በአንተና በሴቲቱ መካከል፡ በዘርህና በዘርዋ መካከል፡ ጠላትነትን አደርጋለሁ! እርሱ፡ ራስህን ይቀጠቅጣል፡ አንተም፡ ሰኰናውን ትነክሣለህ፡" ብሎ በተናገረው፡ የመርገም ፍዳ መነሻነት፡ በአማናዊቷ ሔዋን፡ በድንግል ማርያም ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ወገኖችና በዲያብሎስ መካከል የተቀሰቀሰው፡ ጽኑ የመርኃት ሰልፍ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ ለዘጠኝ ሺህ ዓመታት ሲካሔድ ቆይቷል። በመጨረሻ፡ "እነሆ፡ ድንግል ትፀንሳለች፡ ወንድ ልጅንም ትወልዳለች፡" ተብሎ፡ በነቢያት የተነገረው የትንቢት ቃል፡ የሚፈጸምበት ዘመን ሲደርስ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በድንግል ማርያም የሰውነት ማሕፀን፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ፡ ያለወንድ ዘር፡ ከእርሷ፡ ከሴቲቱ፡ በድንግልና ተወለደ። ዕድሜው፡ ሠላሳ ሦስት ዓመት ሲኾንም፡ ዕርቃን ሰውነቱን፡ በመስቀል ላይ አስዘርግቶና አስቸንክሮ፡ ሥጋውን በመቁረስና ደሙን በማፍሰስ፡ ለእግዚአብሔር አብ ባቀረበው መሥዋዕትነት፡ ለሰው ዘር፡ ዘለዓለማዊ የኾነውን፡ የድል አክሊል አቀዳጀ፡ ይህንም ያደረገው፡ ዲያብሎስ፡ በአዳምና ሔዋን ላይ አውጆ ለከፈተው፡ የጠላትነትና የመርገም ሰልፍ፡ ማክተሚያ የኾነውን ታላቅ ተጋድሎ፡ በአሸናፊነት ከደመደመ በኋላ ነው።[፲፲፭]

የመጀመሪያው የእግዚአብሔር መርገም አብቅቶ፡ ምሕረቱ የተፈጸመበትን፡ ይህን፡ የመጨረሻውን መለኮታዊ ድርጊት፡ ወንጌላዊው ዮሓንስ፡ እንዲህ ሲል፡ በራእዩ በጻፈውና ቀደም ብዬ በጠቀስሁላችሁ ቃሉ ገልጾታል፡ አፍታትቶም፡ ተርጉሞታል፡- "ታላቅ ምልክትም፡ በሰማይ ታየ! ፀሓይን ተጐናጽፋ፡ ጨረቃ፡ ከእግሮቿ በታች ያላት፡ በራስዋም ላይ፡ የአሥራ ኹለት ከዋክብት አክሊል የኾነላት፡ አንዲት ሴት (ድንግል ማርያም) ነበረች። እርሷም፡ ወንሳ ነበር። ...ሌላም ምልክት፡ በሰማይ ታየ! እነሆም እርሱ፡ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ያሉት፡ ታላቅ ቀይ ዘንዶ (ዲያብሎስ) ነበረ።"[፲፲፮]

በኪዳነ አራቱ መሠረት፡ ዐሠርቱ ቃላት፡ በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፈባቸው፡ "ጽላተ ኪዳን" የተባሉት ዝዕቃዎች፡ የእርሱ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲኾኑ፡ ጽላቱን የያዘችው፡ "ታቦተ ጽዮን" ደግሞ፡ የቅድስት እናቱ፡ የድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗ፡ ጥርጥር የሌለበት እውነተኛ ነገር መኾኑን፡ ይህንኑም፡ ኢትዮጵያውያን፡ በየዕለቱ በሚደግሙት፡ የውዳሴ ማርያም ጸሎታቸው ላይ እንደሚያረጋግጡት፡ ከዚህ አስቀድሜ በቦታው ገልጬላችኋለሁ።

ምዕራፍ ፭፤ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት፤ ስድስተኛው ቃል ኪዳን፦ ኪዳነ ዳዊት፤ ድንግል ማርያም፡ "ኢትዮጵያ" ስለመኾኗና የኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊነት።

እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ፡ እግዚአብሔር፡ ይህችን ታቦተ ጽዮንን፡ ለምን፡ ወደኢትዮጵያ እንድትመጣ አደረገ? ማደሪያዋና ማረፊያዋም፡ "ኢትዮጵያ" እንድትኾን፡ ስለምን መረጠ? በዚህ ድርጊቱ፡ "ኢትዮጵያ"፡ የድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ በይፋ መግለጡ፡ በአዋጅ ማሳወቁም አይደለምን?

"እግዚአብሔር፡ ጽዮንን መርጧታልና፡ ማደሪያው ትኾነውም ዘንድ ወድዷታልና፡ እንዲህ ብሎ፡ 'ይህች፡ የዘለዓለም ማረፊያዬ ናት፡ መርጫታለሁና፤ በዚህች አድራለሁ።'" የሚለው ቃል የተነገረው፡ ምንም ፍጻሜው፡ ለድንግል ማርያም ቢኾን፡ ቀዳሚት ምሳሌዋና አርአያዋ ለኾነችው፡ ለ"ኢትዮጵያ" ሞምር መኾኑን፡ እነሆ፡ የትንቢቱ መጨረሻ አረጋግጧል።

ደግሞስ፡ *"ኢትዮጵያ ታብጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"*፡ ማለትም፡ *"ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!"* ተብሎ፡ በሴት አንቀጽ፡ የተነገረው፡ ሕያዉ የነቢዩ ቃል፡ አምላክን ለወለደች፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ካልኾነ በቀር፡ ከቶ፡ ለሌላ፡ "ለማን ተነገረ!" እንላለን? አዎን! "እግዚአብሔር"፡ እርሱ፡ ተወዳጁ ልጇ ሲኾን፡ እርሷ፡ ቅድስት እናቱ ደግሞ፡ "ኢትዮጵያ" ናት። ኢትዮጵያውያንም፡ የእርሷ፡ የድንግል ማርያም ልጆች ናቸው።[፻፲፮]

ይህን፡ መሠረታዊ እውነት፡ *"የእስራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ፡ ለእኔ፡ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?' ይላል እግዚአብሔር፡"* የሚለውና ኢትዮጵያውያን፡ ከእስራኤላውያን በፊት፡ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቁና የተወደዱ መኾናቸውን የሚያስረዳው የነቢዩ ቃል፡ ለዓለሙ ኹሉ ገሃድ አድርጎታል።[፻፲፯]

ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ "ኢትዮጵያ" ማለት፡ መላውን የሰውን ዘር፡ ማለትም፡ የካምን፡ የሴምንና የያፌትን ነገዶች ኹሉ የሚያጠቃልል መጠሪያ ስለኾነ፡ እነዚህን የሰውን ዘር ወገኖች፡ አንድ አድርጋና ወክላ፡ በሥልጣኗም፡ ከምድር እስከሰማይ ደርሳ፡ ራሷን፡ ወደእግዚአብሔር ለማቅረብ፡ እግዚአብሔርም፡ ከሰማይ ወደምድር ወርዶ፡ ወደእርሷ እንዲቀርብ ለማድረግ ብቻ ሳይኾን፡ በማሕፀኗ አድሮ ትወልደው ዘንድ፡ ፈቃዱን ለማግኘት፡ ይህንኑም ፈቃዱን ለማስፈጸም የቻለች፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በቀር፡ ሌላ ፍጡር፡ ከቶ፡ ማን አለ? ማንም የለም። ስለዚህ፡ "ኢትዮጵያ"፡ ድንግል ማርያም መኾኗ፥ "ድንግል ማርያም"፡ ኢትዮጵያ መኾኗ፡ በእነዚህ የእግዚአብሔር ቃላትና ድርጊቶች ተረጋግጦ ይታወቃል።

በመለኮታዊ ባሕርዩና አካሉ፡ ፍጹም አምላክ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ፍጹም ሰው የሚያሰኘውን፡ የሥጋ አካልና ባሕርይ የወረሰው፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመኾኑ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ኾኖ፡ በቅድሚያ እንደተገለጠው፡ እንደመልከ ጼዴቅ ኹሉ፡ የእርሷም ዘር፡ ፍጹም ኢትዮጵያዊ፡ ማለትም፡ ከካም፥ ከሴምና ከያፌት ነገዶች ውሕደት፡ የተገኘው ዘር መኾኑ፡ ጥርጥር የሌለበት እውነተኛ ነገር ነው።

የዚህም፡ ማስረጃውና ምልክቱ፡ ቀደም ብሎ፡ ተደጋግሞ፡ በጉልህ ተከሥቷል፡ ይኸውም፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌዎች ኾነው፡ በየዘመናቱ ከተገለጡት መካከል፡ በተለይ፡ በሙሴና በሰሎሞን፡ ሰውነትና ሕይወት፡ የተፈጸሙትን፡ ከዚህ የሚከተሉትን ድርጊቶች የያዘው እውነታ ነው፡-

፩ኛ፡- ሙሴ፡ የጣዖት አምልኮ ይፈጸምባት ከነበረችው፡ ከግብፅ አገር ወጥቶ፡ አምልኮተ እግዚአብሔር ወደሰፈነባት፡ ወደኢትዮጵያ፡ ለምን መጣ? መጥቶም፡ ኢትዮጵያዊት ሚስትን አግብቶና ልጆችን ወልዶ፡ ለምን በኢትዮጵያ ኖረ? በዚያስ፡ ለምን የእግዚአብሔር ምሥጢር ተገለጠለት? የኋላ ኋላስ፡ ያች፡ ሙሴ፡ ከእግዚአብሔር እጅ የተቀበላት ጽላተ ኪዳን፡ ከኢየሩሳሌም መጥታ፡ ለምን፡ በኢትዮጵያ ተቀመጠች?

፪ኛ፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ ለምን ወደኢየሩሳሌም ኼዳ፡ ከዳዊት ልጅ፡ ከሰሎሞን ተገናኘች? ወደአገርዋም ተመልሳ፡ ለታቦተ ጽዮን ወደኢትዮጵያ መምጣት፡ ምክንያት የኾናትን፡ ምኒልክን፡ ከእርሱ፡ በኢየሩሳሌም ጸንሳ፡ ለምን፡ በኢትዮጵያ ወለደችው? በኋለኛውስ ዘመን፡ ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሰሎሞንን፡ የእርሱ፡ ተቀዳሚ ምሳሌና አርአያ አድርጎ በማነጻጸር፡ ስለእርሷ፡ ስለ"ንግሥተ ሳባ" ለምን ተናገረ?

እንግዲህ፡ እነዚህ ምሳሌዎች፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ከኢትዮጵያዊቷ ድንግል፡ ከቅድስት ማርያም፡ ሰው ኾኖ የተወለደ መኾኑን ለማመልከት፡ በቅድሚያ የተከሠቱ ምልክቶች አይደሉምን? አዎን! በእርግጥ ናቸው።

ዳሩ ግን፡ አይሁድ፡ በነቢያት ትንቢት፡ ከቅድስት ማርያም፡ በድንግልና የተወለደውን ኢየሱስን፡ "መሢሕም፡ የእግዚአብሔር ልጅም፡ ንጉሣችንም አይደለም፡ አናውቀውም፡ አንቀበለውምም።" ብለው፡ ለምን ተቃወሙት? እንዲያውም፡ ከጥላቻቸው ጽናት የተነሣ፡ ስለምን ለሞት አሳልፈው አስከሰጠት ደረሱ? "የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ!" ብሎ፡ የእግዚአብሔርን ሥራ ስለሠራ ብቻ ነውን? አይደለም። በዚህ ረገድማ፡ ላቀረቡለት የተቃውሞ ምክንያቶች ኹሉ፡ የራሳቸውን መጻሕፍት እየጠቀሰ፡ ሊቋቋሙት ያልቻሉትን፡ አጥጋቢ መልስ በመስጠት፡ አሳፍሯቸዋል። ያም ኹሉ ኾኖ፡ አልተመለሱለትም። ይልቁንም፡ "ይህ፡ የእንጨት ጠራቢው ልጅ አይደለምን? ...ለመኾኑ፡ ከናዝሬት፡ መልካም ነገር ሊመጣ ይችላልን? ...በውኑ ክርስቶስ፡ ከገሊላ ይመጣልን? ከዳዊት ዘር፡ ዳዊትም ከነበረባት መንደር፡ ከቤተ ልሔም እንዲመጣ መጽሐፍ፡ አላለምን?" በማለት፡ ለምን፡ በየጊዜው፡ ልዩ ልዩ የማፍረሻ ሰበብ፡ የማዋረጃ ምክንያትና የነቀፌታ ስም እየሰጡ፡ ሊያጠፉት ተነሣሡበት?[፲፫፫]

በእነርሱ አንጻር ደግሞ፡ ኢትዮጵያውያን፡ "ምስ ኦንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር፡ ብሔራዊ ምልክታቸው በማድረግ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "አምላካችንና መሢሓችን፡ መድኃኒታችንና ሊቀ ካህናታችን ብቻ ሳይኾን፡ ንጉሣችንም ነው" ብለው፡ ለምን ተቀበሉት?

ምዕራፍ ፭፤ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት፤ ስድስተኛው ቃል ኪዳን፦ ኪዳነ ዳዊት፤
ድንግል ማርያም፡ "ኢትዮጵያ" ስለመኾኗና
የኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊነት።

ኢትዮጵያውያን፡ በዚህ መልክ የተቀበሉት፡ በሃይማኖት ብቻ ሳይኾን፡ ለምን፡ በሥጋ ጭምር ኾነ? አይሁድ፡ "በሥጋ አይዛመደንም!" በማለት፡ ኢትዮጵያውያን ግን፡ በሥጋ ጭምር የሚዛመዳቸው መኾኑን ስላረጋገጡ አይደለምን? ቀደም ብዬ እንደጠቀስሁላችሁ፡ በሥጋ፡ ወገኑና ዘሩ ያልኾነውን ባዕድ፡ ፈልጎና ፈቅዶ፡ በላዩ የሚያነግሥ ሕዝብ፡ በዓለም ላይ፡ ከቶ፡ አለን? የለም።

አይሁድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ "አንቀበለውም!" ብለው፡ የተቃወሙበት÷ የካዱበትና በአረማውያን እጅ ተሰቅሎ እንዲሞት አሳልፈው የሰጡበት ምክንያት፡ ልክ፡ በዘመነ ብሉይ፡ አርአያው ኾኖ በተገለጠው፡ በሙሴ ላይ አድርሰውት የነበረውን ይመስላል፤ አዎን! አይሁድ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያሳዩት ጽኑ ጥላቻና የመረረ ተቃውሞ፡ የእስራኤል ልጆች፡ በየዋሁ መሪያቸው፡ በሙሴ ላይ፡ "ኢትዮጵያዊት ሚስት ለምን አገባ? ለምንስ አብሩዋት ኖረ? ልጆችስ፡ ከእርሷ ለምን ወለደ?" ብለው፡ ወንድሙ፡ አሮንና እኅቱ፡ ሚርያም ሳይቀሩ፡ አብረው ዶልተው፡ በቅንዓትና በምቀኝነት ተነሥተውበት የነበረውን ዓይነት መኾኑ ግልጽ ነው።

ይህቺው፡ ኢትዮጵያዊት ሚስቱ ሲጳራና ልጆቿ፡ ከባሏ፡ ከሙሴ ዕረፍት በኋላ፡ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር፡ ወደምድረ ከነዓን አለመግባታቸው÷ ነገር ግን፡ ወደአባቷና ወደልጆቿ አያት፡ ወደዮቶር÷ ወደእናት አገራቸውም፡ ወደኢትዮጵያ መመለሳቸው÷ አይሁድም፡ በሙሴ ላይ የነበራቸው ጥላቻና ተቃውሞ፡ የቀጠለ መኾኑ፡ በተከታዩ አድራሳታቸው ተረጋግጧል። ይኸውም፡ አይሁድ፡ የአሮንንና የልጆቹን÷ ከእነርሱ በፊትና በኋላም የነበሩትን፡ የቅዱሳን አባቶችን የትውልድ ሐረግ፡ በእየመጻሕፍታቸው እያስፋፉ ሲመዘግቡ፡ ታላቁ የእግዚአብሔር ነቢይ የኾነውን፡ የሙሴን ግን፡ ያን ያህል ግምት ሳይሰጡት መቅረታቸው ነው። በዘመነ ብሉይ፡ ሙሴ፡ በአይሁድ ዘንድ፡ ያን ለመሰለ፡ ለዘረኛነት ፈተናና መከራ የተዳረገው፡ በኢትዮጵያዊት ሚስቱ÷ ጋብቻውና ትዳሩ ምክንያት ካልኾነ በቀር፡ በሌላ፡ በምን ነገር ሊኾን ይችላል?

ከክርስቶስ በኋላ፡ በዘመነ ሐዲስ፡ በአይሁድ ላይ፡ እነሆ፡ ለኹለት ሺህ ዓመታት ያህል፡ እየወረደባቸው ያለው የመከራ መዓት፡ በዚያን፡ በሙሴ ጊዜ፡ እግዚአብሔር ተቆጥቶ፡ በአሮንና በተለይ በእኅቱ፡ በሚርያም ላይ ሊያመጣ ቃጥቶት የነበረውን÷ ነገር ግን፡ በጻድቅ ባለሟሉ፡ በሙሴ ምልጃ የመለሰውን፡ መቅሠፍታዊ ቅጣት አይመስልምን? ይህም፡ የኋለኞቹ አይሁድ፡ *"የሚያደርጉትን አያውቁምና፡ ይቅር በላቸው!"* ብሎ በማለደላቸው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ከፈጸሙት የማፍ በደል፡ አኹንም ተጸጽተው፡ ንስሓ ስላልገቡ፡ ራሳቸውን፡ በራሳቸው በመኰነን፡ *"ደሙ፡ በእኛና በልጆቻችን ይኹን!"* ብለው የወሰኑትን ፍዳ፡ እየተቀበሉ መኖራቸውን በመቀጠላቸው እንደኾነ፡ እነሆ፡ በገሃድ ይታያል።

እንግዲህ፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ኢትዮጵያዊነት ለሚክዱ ኹሉ፡ ከሚጠቀሱላቸው ማስጠንቀቂያዎች መካከል፦

፩ኛ፡ የሙሴን ኢትዮጵያዊነት በመቃወማቸው ምክንያት፡ በአሮንና በእኅቱ ላይ ተሠንዝሮ የነበረው መለኮታዊ ቁጣ ይገኛል፤

፪ኛ፡ *"ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ፡ መልክ አይታችሁ አትፍረዱ!"* ባላቸውና በዚህ ኢትዮጵያዊ መልኩ የተነሣ፡ ለመስቀል ሞት አሳልፈው በሰጡት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያት፡ ይኸው፡ ለኹለት ሽህ ዓመታት፡ በአይሁድ ላይ እየወረደባቸው ያለው፡ የእልቂት መከራ ይመሰክራል፤

፫ኛ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመልኩና በዘሩ ኢትዮጵያዊ መኾኑን፡ አይሁድ ስላወቁ፥ በዚህ ማንነቱም፡ እርሱን በመናቅና በማዋረድ፡ ከሰደቡት በኋላ፡ ሊገድሉት ምክንያት ፈልገው፡ *"ከአንተ፡ ምልክት ልናይ እንሻለን፥"* ብለው በተንኰል በጠየቁት ጊዜ፡ የሰጣቸው ምላሽ እየጮኸ ይናገራል፤ ይኸውም፡ *"ንግሥተ ዓዜብ፡ በፍርድ ቀን ተነሥታ፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ትፋረዳለች፡ ታሳፍረዋለችም፡ የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ፡ ከምድር ዳርቻ መጥታለችና፡ እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ!"* ብሎ ያሰማው መለኮታዊ ቃሉ ነው።

ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡-

፩ኛ፡ በሥጋዊ ልደቱ፡ የካም፡ የሴምና የያፌት ነገዶች፡ በዘር፡ እንደገና የተዋሐዱበት በመኾኑ፥

፪ኛ፡ በመንፈሳዊ ዕድገቱ፡ ከኪዳነ ልቡና ተነሥቶ፥ ባኪዳነ አራት በኩል አልፎ፥ ወደኪዳነ መንፈስ ቅዱስ የደረሰ በመኾኑ፡ ይህ ኢትዮጵያዊነት፡ እግዚአብሔር፡ ለመላው የሰው ልጆች፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላዘጋጀው፡ መለኮታዊ ዕቅዱ፡ የመጨረሻው ግብ መኾኑ፡ ግልጽ ነው።

ይህም፡ በዘር፡ "ሴማዊ፥ ካማዊ፥ ወይም፡ ያፌታዊ ነኝ!" በማለት፥ በቀለምም፡ "ቀይ፡ ጥቁር፡ ወይም፡ ነጭ ነኝ!" በማለት፥ በሃይማኖትም፡ "አረማዊ/እስላም፥ አይሁዳዊ፥ ወይም፡ ክርስቲያን ነኝ!" በማለት፥ በአምልኮም፡ "ባለኪዳነ ልቡና፥ ባለኪዳነ አራት፥ ወይም፡ ባለኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ነኝ!" በማለት፡ ለሦስት ተከፋፍለው፡ እርስ በእርሳቸው የሚፋጁት፡ የዓለም ሕዝቦች፡ በዘርና በቀለም፡ በሃይማኖትና በአምልኮ ብቻ ሳይኾን፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ ሦስትም፡ ውሕደትን ያገኙበት አካልና ባሕርይ በመኾኑ ተረጋግጧል። ለዚህም፡ ራሱ፡ እውነተኛው ኢትዮጵያዊውና በእርሱ ላይ ሕያዋን ኾነው የሚታዩት የቅዱሱ ኪዳን ውርሶች ምስክሮች ናቸው፡ የ"ኢትዮጵያዊነት" መገለጫው፡ ይኸው፡ "ኢትዮጵያዊው ሰውነት" ነውና።

ነቢዩ ኤርምያስ፡ ማንንም ሳይፈራ፡ ከእግዚአብሔር የታዘዘውን መልእክት፡ ለሕዝቡ፡ በእውነት በማድረሱ፡ በአይሁድ ዘንድ፡ በጥላቻ ተፈርዶበት፡ እንዲሞት፡ እገድጓድ ውስጥ እንደተጣለ ተጽፏል። በዚያን ጊዜ፡ በኢየሩሳሌም ቤተ መንግሥት፡ አዛዥና የንጉሡ ባለሟል የነበረው፡ "ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ"፡ ኢትዮጵያዊ ወገኑ ከነበረው፡ ከኤርምያስ፡ ይነገር የነበረውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል፡ "ባሮክ" ከተባለው፡ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር አምኖና ተቀብሎ ይኖር ነበር፡ እርሱም፡ እምነቱና አስተሳሰቡ፡ ከማናቸውም የዘረኝነት ስሜት ንጹሕ ስለነበረ፡ በዚህ ነገር፡ እጅግ አዝኖ፡ በባለሟልነቱ፡ ኤርምያስን፡ ከንጉሡ አማልዶና ፍርዱ እንዲቀለልለት አድርጎ፡ ከሞት አድኖታል።

ምዕራፍ ፭፤ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት፣ ስድስተኛው ቃል ኪዳን፦ ኪዳነ ዳዊት፣ ድንግል ማርያም፡ "ኢትዮጵያ" ስለመኾኗና የኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊነት።

ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ፡ ከኤርምያስ በተነገረው፡ በእግዚአብሔር ቃል በመታመኑና ለነቢዩ ላደረገው የርኅራኄ ሥራ፡ እግዚአብሔር፡ *"በእኔ ታምነሃልና፡ ፈጽሜ አድንሃለሁ!"* **የሚል፡ የምሕረት ቃል ኪዳን አሰማው፡ የኤፌሶንያስ ደቀ መዝሙር ከነበረው፡ ከኢትዮጵያዊው ባሮክም ጋር፡ ከናቡከደነፆር ሠይፍና ከባቢሎን ምርኮ አተረፈው።** ይህ፡ የኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ፡ የዕርቅና የሰላም ሃይማኖታዊ ምግባር፡ ከላይ፡ ስለኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ የተሠነዘረውን እውነታ ያጠናክረዋል።

በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ፡ ለፍጹምነት የበቃውን፡ ይህን ፮ኛውን ቃል ኪዳን፡ ከእግዚአብሔር የተቀበለው፡ ንጉሡ ቅዱስ ዳዊት፡ የተወለደበት ሐረግ፡ የ"አቤሜሌክ" ወንድም ከኾነው፡ ከቦዔዝና ከሩት ልጅ፡ ከእሴይ በመኾኑ፡ በዳዊት ትውልድ ውስጥ፡ "አቤሜሌክ" የሚለው ኢትዮጵያዊ ስም መጠቀሱ፡ በዳዊት በኩል፡ ከኢትዮጵያዊው ዘር ጋር የሚያገናኝ፡ አንድ የትውልድ ሐረግ እንዳለ ያመለክታል። ደግሞም፡ አንዲት የሕግ ሚስቱን ወስዶ ለማግባት ሲል፡ ዳዊት፡ በጦር ሜዳ፡ በጠላት ሠራዊት እጅ እንዲገደል የፈረደበት አርዮን፡ በአንዲት ሚስት የተወሰነ መኾኑ ብቻ ሳይኾን፡ ሃይማኖታዊነቱና መንፈሳዊነቱ፡ ታማኝነቱና ጨዋነቱ፡ በዚያን ጊዜ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ብቻ ጸንቶ ይጠበቅ በነበረው አቋም መገኘቱ፥ "ቤትሳባ"፥ ወይም፡ "ቤርሳቤህ" የሚል፡ ኢትዮጵያዊ ስም የነበራት ሚስቱም፡ በዚሁ አቋም የጸናች ኾና መታየቷ፡ ኹለቱም፡ ባልና ሚስት፥ አለዚያም፡ ከኹለት አንዳቸው፡ ኢትዮጵያውያን ለመኾናቸው፡ አመልካች ፍንጭነት እንዳለው ማስተዋል አግባብ ይኾናል።[፻፲፱]

ስለዚህ፡ በመጀመሪያ፡ በአዳምና ሔዋን ተመሥርቶ፡ በመኻሉ፡ በኖኅ፡ በአብርሃም፡ በሙሴና በዳዊት የቀጠለውንና በፍጻሜው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለዘለዓለም የጸናውን፡ ኢትዮጵያዊውን የቅዱሱን ኪዳን ልደት፡ እንደመልከ ጼዴቅ፡ በእውነተኛ ሰውነት፡ እንደድንግል ማርያም፡ በመንፈስ ቅዱስ ብቅዓት የተቀበለ፡ ማናቸውም፡ ከአንድ ከሴም፥ ወይም፡ ከአንድ ከካም፥ ወይም፡ ከአንድ ከያፌት ነገድ ብቻ የተወለደ ሰው ኹሉ፡ "ኢትዮጵያዊ" ነው። ይህን የኢትዮጵያዊነት ባሕርይ የያዘው ሰብአዊ ዘር፡ በምድር ላይ መበተኑና እየተራባ መኼዱ፡ በመጨረሻ፡ የራስ ወዳድነትን፡ የዕብሪት ስሜትንና የዘረኝነት ጠንቅን፡ እንዲሁም፡ በእምነት፥ በፍልስፍናና በርእዮተ ዓለም አስተሳሰብ፡ የአምባገነንነት መጠናወትን፡ ለመቼውም ጊዜ፥ ከአንድ አገር ብቻ ሳይኾን፡ ከመላውም ዓለም አስወግዶ፡ ጠላትነትና ጦርነት የጠፋበትን፡ ሰላምና ፍቅርም የሰፈነበትን ሕይወት፡ "ለሰው ልጆች ያቀዳጃል!" ተብሎ ይታመናል።

ያም ጊዜ፡ በኢትዮጵያ ምድር ላይ፡ ጥንት፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡ በአዳምና በሔዋን፡ በመጨረሻውም ዘመን፡ በዘለዓለማዊው ካህንና በሰላማዊው ንጉሥ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ በንግሥት እናቱም፡ በድንግል ማርያም የተገለጠችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በመንፈሳዊው ሕይወት ብቻ ሳይኾን፡ በሥጋዊውም ዓለም ቈምር፡ በምልዓትና በገሃድ መስፈን የምትጀምርበት ዘመን ይኾናል።

እነሆ፡ በብሉይ ኪዳኑ መልከ ጼዴቅ የተከሠተው ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ ትውልዱና ማንነቱ፡ በአዲስ ኪዳኑ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በግልጽ ታውቆ፡ ከፍጹምነት ስለደረሰ፡ በዚህ "ኢትዮጵያዊነት"፡ የሰው ልጅ፡ በግለሰብም ኾነ፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ፡ ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ ህልውናው፡ ሲመኘው የኖረውን ብቅዓት፡ ለማግኘት ችሏል።

ድንግል ማርያም እና ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአካለ ሥጋ፡ ወደኢትዮጵያ ስለመምጣታቸው።

ጥያቄ፡- ቅድስት ድንግል ማርያምና ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እንዲህ ኢትዮጵያውያን ከኾኑ፥ ቀደም ብለህ እንደገለጥህልን፡ ምንም እንኳ፡ በአባታቸው በመልከ ጼዴቅ ምክንያት፡ ኢየሩሳሌምም አገራቸው ብትኾን፡ አዳምና ሔዋን የተፈጠሩባት፥ የቀደሙት አባቶቻቸውና እናቶቻቸውም የተወለዱባት፡ ዓፅመ ርስታቸው ወደኾነችው፡ ወደዛሬዪቱ ምድረ ኢትዮጵያ፡ በአካለ ሥጋ መጥተው ኖርዋልን?

መልስ፡- እናትና ልጇ፡ በተለይ፡ ከሕፃኑ ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላና ከጥምቀቱ በፊት፡ ወደኢትዮጵያ መጥተው የመቆየታቸውን ነገር አበክረው የሚያመለክቱ እውነታዎች፡ በኢትዮጵያዊው ትውፊት ውስጥ፡ በብዛት ተመዝግበው ይገኛሉ።

ይህንኑም፡ በሕያውነት ሲነገር ከሚኖረው፡ ከሊቀ መላእክት፡ ቅዱስ ሩራኤልና ከሌሎች ድርሳናት ጋር፡ በመላዋ የኢትዮጵያ ምድር፡ በስፋትና በምልዓት የሚገኘው፡ ግዙፍና ቁሳዊ የኾነው የማስረጃዎች ክምችት ያረጋግጠዋል። *"ልጄን ከግብፅ ጠራሁት!"* የሚለውን ትንቢት ለመፈጸም፡ ወደግብፅ ከመኼዳቸው በፊት፡ "ድንግል ማርያምና ሕፃኑ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከዮሴፍና ሰሎሜ ጋር ወደአገራቸው፡ ወደኢትዮጵያ መጥተው፡ ቆይታ አድርገዋል" የሚለውን፡ ከላይ የተጠቀሰውን፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ትውፊት የሚያጠናክሩ፡ ግልጽ የኾኑ የዘመናት ምልክቶች አሉ።[፻፳] "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግሮቹን መረገጫዎች ያሣረፈባት ናት፡" ተብሎ የሚታመንባት፡ ለአኵስም ጽዮን ቤተ መቅደስ ትይዩ ኾና፡ ከበስተምሥራቅ የምትገኘው የኰረብታ አናት፡ ሌሳዪቱ ናት። እርሷም፡ ለዚሁ የተሰጣትን መታሰቢያነት በማጽናት፡ እስከዛሬ "መከየደ እግዚእ" ማለትም፡ "የጌታ መቆሚያ" ተብላ የምትታወቅበትን ስም እንደያዘች እነሆ ትኖራለች።

ከዋና ዋናዎቹ ምልክቶች መካከል አንደኛው፡ ያ፡ የእናትና ልጇ የስደት ዘመን፡ በኖኅ ተጀምሮ፡ ሳይቋረጥ የቀጠለው፥ ኢትዮጵያውያንም፡ በአባታቸው በመልከ ጼዴቅ በተቈረቈረችው፡ በኢየሩሳሌምና በእናት አገራቸው፡ በኢትዮጵያ መካከል፡ ያደርጉት የነበረው፡ የተለመደው ሃይማኖታዊ ጉዞ፡ በላቀ ደረጃ የተካኼደበት ጊዜ መኾኑ ነው።

ምዕራፍ ፭፤ ስባቱ ቅዱሳት ኪዳናት፤ ስድስተኛው ቃል ኪዳን፦ ኪዳነ ጻዊት፤ ድንግል ማርያም እና ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአካለ ሥጋ፡ ወደኢትዮጵያ ስለመምጣታቸው።

ኹለተኛው ደግሞ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከአሥራ ኹለት ዓመት ዕድሜው በኋላ፡ እስከጥምቀቱ ድረስ፡ ምን ያደርግ እንደነበረ ወይም የት ይኖር እንደነበረ፡ በወንጌላውያን ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ ጨርሶ ያልተመሳ ሲኾን፡ ስለዚያ የዝምታ ጊዜ፡ ኢትዮጵያውያን ባልኾኑ ክርስቲያኖችና በሌሎች ወገኖች ዘንድ ጭምር፡ እስካኹን ምንም ዓይነት መግለጫ ያልተሰጠበት፡ ባዶ ሰሌዳ ኾኖ መገኘቱ ነው። በዚህ ረገድ፡ አንዳንድ ፍንጭ ቢኖርም፡ እናትና ልጇ፡ በኢትዮጵያ ያደረጉትን ቆይታ አይቃረንም።

ኢትዮጵያ፡
የእግዚአብሔር መንግሥት፡
የመኾኗ ምሥጢር።

ጥያቄ፡- በኢትዮጵያ፡ ሰፍና ስለኖረችው የእግዚአብሔር መንግሥት አቋምና አሠራር፡ በሚበቃ አልተረዳነውምና፡ ብታብራራልን?

መልስ፡- "በኢትዮጵያ ሰፍና ስለኖረችው፡" ስትሉ፡ ዛሬ የሌለች ማለታችሁ እንዳይደለ አምናለሁ። የእግዚአብሔር መንግሥት፡ *"ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ፡ ለእውነተኞች ሰዎች የተዘጋጀች ኾና፡ እስከዛሬ የኖረች፡ ዛሬም፡ ያለች፡ ለዘለዓለምም የምትኖር መኾኗን"* እንደተገነዘባችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። እርሷም፡ በኢትዮጵያ፡ ሰፍና የምትሠራው፡ በሦስቱ ቃለአገልግሎት ዘርፎች አማካይነት ነው። እነዚህም፡ ቤተ ሕዝብ፡ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና ይባላሉ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት የታነጸበት፡ ይህ የሦስትነት ባሕርይ ምሥጢር፡ *"ሲሦ ለአንጋሽ፡ ሲሦ ለአጋሽ፡ ሲሦ ለቀዳሽ"* በሚለው ሃይማኖታዊና ኪዳናዊ ሥርዓት፡ የበለጠ ጕልቶና ተተርጕሞ፡ ታውቆና በተግባር ላይ ውሎ ኖርዋል።

ይህም ማለት፡ በማናቸውም ረገድ፡ የመንግሥቱ አንድ ሦስተኛ የኾነው ድርሻ፡ የቤተ ሕዝቡ፡ ሌላው አንድ ሦስተኛ የኾነው ድርሻ ደግሞ፡ የቤተ ክህነቱ ሲኾን፡ የቀረው አንድ ሦስተኛ የኾነው ድርሻም፡ የቤተ ምልክናው ይኾናል ማለት ነው። የምሥጢሩን ትርጓሜ አግዝፎ ለማስረዳት፡ በሰብአዊው ተፈጥሮ፡ ቋሚ የኾነችው፡ ዋናዋ የነፍስ አካል፡ ኋላ የተላበሰቻቸው፡ ሥጋዊ አካልና መንፈሳዊ አካል እንዳሏት ኹሉ፡ የእግዚአብሔር በኾነችውም መንግሥት፡ እንደነፍስ ለሚቆጠረው፡ ለቤተ ሕዝቡ፡ ቤተ ምልክናው እንደሥጋ፡ ቤተ ክህነቱም፡ እንደመንፈስ አካላት ኾነው ተመድበው ያገለግላሉ፡ ይሠራሉ።

እንግዲህ፡ ግንዱ አካል ለኾነው፡ ለቤተ ሕዝቡ ሥጋዊ ህልውና፡ የሚያስፈልጉትን የአስተዳደርና የአገልግሎት ተግባራት ለማበርከት፡ የኃላፊነቱ ዘርፍ፡ የቤተ ምልክናው ሲኾን፡ ለቤተ ሕዝቡ መንፈሳዊ ህልውና፡ የሚያስፈልጉትን የአገልግሎት ተግባራት ለማበርከት ደግሞ፡ የኃላፊነቱን ዘርፍ የያዘው፡ ቤተ ክህነቱ ነው ማለት ይኾናል።

በምድራዊው ሥልጣኔ የተራመደው፡ ሥጋዊው ዓለም፡ "የመጨረሻው የሥነ መንግሥት ብቅዓት ነው" ብሎ በሚታመንበት ብሔራዊ የአስተዳደር ሥርዓቱ፡ "ሕግ አውጪ፡ ሕግ ፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ" የሚላቸው ሦስት ዘርፎች፡ ይህን መዋቅር የተከተሉ በመኾናቸው፡ የዛሬው የሰው ልጅ እየተጠቀመበት ያለው፡ ያገርና የመንግሥት አስተዳደር ፍልስፍና፡ ምንጩ፡ ማንና ከየት እንደኾነ፡ በቀላሉ መረዳት ይቻላል፤ ይኸውም፡ ከኢትዮጵያውያንና ከኢትዮጵያ መኾኑን ነው።

ኢትዮጵያውያን፡ ህልውናቸውን ከጀመሩበት ጊዜ አንሥቶ፡ እነዚህ ሦስት ቤቶች የሚያበረክቷቸው የጸጋ ሥልጣናት፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተሰጡ መብቶች ኾነው፡ በእያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ሰውነት ውስጥ ተዋሕደውና ሰፍነው የሚገኙ ኾነዋል። ይህም የኢትዮጵያውያን የብቅዓት ማዕርግ፡ በኢየሱሲ ክርስቶስ ሰው ኾኖ ወደዚህ ዓለም መምጣትና እነርሱም፡ ለእርሱ ባደረጉት፡ የሃይማኖት አቀባበል፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ታትሞላቸዋል። ይህም፡ እንዲህ ብሎ በተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ተፈጽሟል፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ማንነቱን አውቀው <u>*"ለተቀበሉት ኹሉ፥ በስሙ ለሚያምኑት፡ ለእነርሱ፡ የእግዚአብሔር ልጆች ይኾኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው። እነርሱም፡ ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፡ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።"*</u> እንዲሁም፡ *"ዳግመኛ፡ የተወለዳችሁት፡ ከሚጠፋ ዘር አይደለም፤ በሕያውና ለዘለዓለም በሚኖር፡ በእግዚአብሔር ቃል፡ ከሚያጸና ዘር ነው እንጂ!"* ደግሞም፡ *"ታርደሃልና፥ በደምህም፡ ለእግዚአብሔር፡ ... ሰዎችን ዋጅተሃ፡ ለአምላካችን፡ መንግሥትና ካህናት ይኾኑ ዘንድ አደረግሃቸው፤ በምድርም ላይ ይነግሣሉ።"* እንዲሁም *"የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይኾናሉ፥ ከእርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።"*[ደ፩፩]

ይህ የእግዚአብሔር ቃል፡ ያስገኘው የብቅዓት ደረጃ፡ እውነተኛውን ኢትዮጵያዊ፡ በሦስቱም ቤቶች ውስጥ ለሚኖረው ለማንኛውም የመጨረሻ ዝቅተኛ፥ ወይም የመጨረሻ ከፍተኛ የአገልግሎት ኃላፊነት ቦታ፡ እኩል፥ ብቁና ተገቢ ኾኖ ሊታጭ እንዲችል አድርጎታል። ከዚህም በላይ፡ ይኸው የብቅዓት ደረጃ፡ ማንኛውም "እውነተኛ" ኢትዮጵያዊ፡ በቤተ ክርስቲያን ተቀብቶና ዘውዱን ጭኖ፡ ወይም ማንኛዪቱም "እውነተኛ" ኢትዮጵያዊት፡ ተቀብታና ዘውዱን ጭና፡ በመንበረ ዳዊቱ ዙፋን ላይ በመቀመጥ፡ የንጉሠ ነገሥቱ፡ የኢየሱስ ክርስቶስና የንግሥተ ንግሥታቱ፡ የድንግል ማርያም እንደራሴ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ዋና አገልጋይና የሦስቱ የአገልግሎት ቤቶቿ፡ ባለአደራ ተመልካች ለመኾን፡ የሚያስችለውንም ጸጋ፡ ለኢትዮጵያውያን አጐናጽፏል። ይኸውም፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" ወይም "ሥይምተ እግዚአብሔር"፡ ሲተረጐም፡ "በእግዚአብሔር ተመርጠ የተሾመ" ወይም "በእግዚአብሔር ተመርጣ የተሾመች" ማለት በኾነው፡ "አጼ" ወይም "ንግሥት"፡ በሚል የማዕርግ ስም የሚከብረው የመጨረሻው ሹመት ነው።

ይህ መሠረታዊ እምነት፡ የኢትዮጵያ ህልውና ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ፡ በተለይም ከክርስቶስ ልደት ወዲህ፡ መደበኛ ሥርዓት ኾኖ፡ በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ የተቀመጡት ኢትዮጵያውያን ኹሉ፡ የተመረጡበትንና የተቀቡበትን ወግ እየደነገገ ሲመራና ምንጊዜም ሲያስፈጽም ኖርዋል። በዚህ መልክ የተመረጡት፡ አጼው፡ ወይም፡ ንግሥቲቱ፡ የቤተ ሕዝቡ፡ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው ባለመንበሮችና ባልደረቦች፡ ተራው ሕዝባዊና ካህኑ፡ ሠራተኛውም ጭምር፡ በቅዱሱ ቃል ኪዳን፡ ከመሪዎቻቸው፡ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከድንግል ማርያም፡ ለተቀበሉት የኢትዮጵያዊነት መብትና ግዴታ፡ ታማኞች ኾነው በሚገኙበት ጊዜ፡ በአገሪቱ ላይና በሕዝቡ መካከል፡ ሰላምና ፍቅር፡ ልማትና ብልጽግና ይሰፍናል፡ "የጥጋብ ዘመን"፡ ማለትም፡ መልካም ዘመን ይኾናል።

ለዚህም፡ የቅርቡን ዜና መዋዕል፡ በምሳሌነት መጥቀስ ቢያስፈልግ፡ ከነአጼ ላሊበላና ከነአጼ ይኵኖ አምላክ በኋላ፡ በሺ፬፻፬ ዓመተ ምሕረት፡ በአጼነቱ ሥልጣን ተቀብቶ፡ በእግዚአብሔር እውነት እየተመራ፡ ቤተ ሕዝቢን፡ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን አዋሕዶ፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነት ጸንታ የኖረችውን፡ ኢትዮጵያን፡ እንደመልክ ጼዴቅ፡ ያገለግልና ያስተዳድር የነበረውን፡ የአጼ ዳዊትን ልጅ፡ ቀዳማዊ ቴዎድሮስን ማውሳት ይቻላል። ወደፊት፡ እንዲህ ያለው፡ መልካም ዘመን የመጣ እንደኾነ፡ በዚያን ጊዜ፡ የሚቀባው "አጼ"፡ ይህን፡ የቴዎድሮስን ፈለግ ተከትሎ፡ በዚሁ፡ የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና ምግባር የሚሠራ ስለሚኾን፡ ግብሩ ብቻ ሳይኾን፡ ስሙም፡ "ቴዎድሮስ" ይባላል ተብሎ፡ ከዚያ ወዲህ፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ፡ በለሚሰሰ የሚሰማ "ንግር" አለ። ምናልባት፡ እናንተም፡ ድንገት ወይም በአጋጣሚ፡ ይህንኑ ቃል ብትሰሙት፡ ነገሩ፡ እንግዳ እንዳይኾንባችሁ፡ መነሻው ምክንያት፡ ይህ መኾኑን፡ አስቀድማችሁ ብታውቁት ይጠቅማችኋል።

ወደዋናው ቁም ነገር ልመልሳችሁና፡ ይኹን እንጂ፡ በዚህ፡ በቅዱሱ ኪዳን የዘውድ ሥልጣን ላይ፡ ከመደበኛው ሥርዓት ውጪ፡ የተካኼዱና የሚካኼዱ፡ የክህደት፡ ወይም፡ የዓመፅ፡ ወይም ሌላ የኃይል ተቃውሞዎች፡ በየዘመናቱ መከሠታቸው እንዳልቀረ፡ በግልጽ ይታወቃል። ነገሩን በሃይማኖታዊ ዓይን ሲመለከቱት፡ እነዚህን አሳዛኝ ኹኔታዎች ለማስከተል፡ ምክንያት የኾኑት ጠንቆች፡ ምን እንደኾኑ ለመረዳት ከቶ አያዳግትም። ይኸውም፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያሉት፡ ሦስቱ የአገልግሎት ቤቶች፡ አንዳቸው ወይም ኹሉም፡ የእግዚአብሔርን ቅዱሳት ኪዳናት፡ በክህደት በሚያፈርሱበት ጊዜ፡ ይህ ድርጊታቸው፡ መርገምን የሚያስከትል፡ ርኵሰት ስለሚኾንባቸው ነው፤ ይህን የመሰለውም ርኵሰት፡ ጽዋው ሲሞላ፡ ከዚህ የተነሣ የሚመጣውን፡ መለኮታዊቲን የቅጣት ቁጣ የሚያቀጣጥሉ፡ የጥፋት ጠንቆች፡ ይፈጠራሉ። ያ ዓመፅ ወይም የኃይል ተቃውሞ፡ የእነዚህ የጥፋት ጠንቆች ውጤት ነው።

ጥያቄ፡- የእግዚአብሔር ቅዱሳት ኪዳናት፡ በክህደት በሚፈርሱበት ጊዜ፡ ይህ ድርጊት፡ መረገምን የሚያስከትል፡ ርኵሰት ስለመኾኑ፥ ይህም ርኵሰት፡ ጽዋው ሲሞላ፡ መለኮታዊዉን የቅጣት ቁጣ የሚያቀጣጥል ስለመኾኑ፡ ከዚህ የተነሣ የሚፈጠሩት የጥፋት ጠንቆች፡ የሕዝብ ዓመፅን ወይም የኀይል ተቃውሞን ስለማስገኘታቸው፡ በማስረጃ የተደገፈ ማብራሪያን ብትሰጠን፡ እውቀታችንን የበለጠ የሚያሚላልን ይመስለናል።

መልስ፡- ስላለፉት ዘመናት በሚናገረው፡ በአገራችን ዜና መዋዕል የተመዘገቡት፡ የየጊዜያቱ ድርጊቶች፡ እንዲሁም፡ በቅርቡ የተከሠቱት እውነታዎች፡ ዛሬም በአገሪቱ ውስጥና በእየአህጉሩ ተሠራጭተው በሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ሕይወት ላይ የሚታዩት ኹኔታዎች፡ በዚህ ጥያቄያችሁ ውስጥ የተካተቱትን እውነታዎች፡ በይፋ ያረጋግጣሉ።

ለዚህ ማስረጃ እንዲኾኑን፡ "አያድርስ!" ከሚያሰኙት፡ ከቀደሙት ተመሳሳይ የመከራ ዘመናት መካከል፡ "አሠቃቂዎች ናቸው" የተባሉትን ጥቂቶቹን እጠቅሳቸዋለሁ። እኒህም፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ሕያዋን ዝክሮች ኾነው ሲታመሱ የሚኖሩት፡ ባለፉት አሠርተ ምዕት ዓመታት ውስጥ፡ አልፈው አልፈው እየተነሡ፡ አገሪቱን ያጥለቀለቁት የዓመፅ ማዕበሎችና ከእነርሱ በኋላ፡ በሚያስፈራ መጠን የተከተሉት ታላላቅ የድምሳሴ እልቂቶች ናቸው።

በዚህ የጥፋት ዝርዝር ውስጥ፡ ኅልታና ቀዳሚ ኾና የምትታየው፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፡ በ፲ኛው ምዕት ዓመት፡ ማለትም፡ እንደትንቢቱ፡ "በሺሁ ዓመት" ፍጻሜ ላይ የተነሣችው "ጉዲት" ወይም "እሳቶ" የተባለችው፡ ስመጥፋዋ ይሁዲት ስትኾን፡ ከእርሷ ቀጥሎ፡ በ፲፮ኛው ምዕት ዓመት የተነሣው ጨካኙ አስላም፡ አሕመድ ግራኝ ይገኛል፤ እርሱም፡ በአገሪቱ ላይ ካደረሰው፡ ወደር ከሌለው ጥፋት የተነሣ፡ በቅድሚያ ከተካኼደው የአረማውያን ወረራ ቀጥለው፡ ካቶሊካውያን ልዑካን፡ ኃይል አግኝተው፡ ወዲያው በማከታተል፡ በሕዝቡ መካከል በቀሰቀሱት የሃይማኖት መለያየት ምክንያት፡ የእርስ በርስ ጦርነት ተነሥቶ፡ አያሌ የንጹሓን ደም ሊፈስስ ችሏል። ከዚያም፡ በ፲፱፻፳፯ ዓ. ም. የተነሣው የቅርቡ ግፈኛው የዘር ጠላት፡ ካቶሊካዊው ሩሺስት መሪ፡ ሙሶሎኒ ይጠቀሳል። በመጨረሻም፡ በዛሬው ትውልድ ላይ ለደረሰው፡ የበቀል ቅጣት፡ በመሣሪያነት ተመድበው፡ "እግዚአብሔር የለም" በሚል የስንፍና እምነት፡ ተልእኳቸውን በመፈጸም ላይ የሚገኙት፡ "ኮሚዩኒስት ነኝ" ባዩ፡ የትናንቱ የደርግ መሪ፡ አብዮታዊው (ዓመፀኛው) መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እና የዛፊው፡ መለስ ዜናዊ ይገኛሉ። (በግእዝ፡ "አበየ"፡ ዐመፀ ማለት ነው።) ከዚህ ጥቂት ቀደም ብሎ፡ በ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. በክብር ዘበኛው ጦር አዝማች መንግሥቱ ንዋይ፡ የተፈጸመው፡ የብዙዎች ደም የፈሰሰበትና ውጤት-አልባ የነበረው የአልጋ ማፍረስ ሙከራም፡ እዚህ ላይ ሳይወሳ የሚታለፍ አይደለም።

እኒህ ኹሉ የጥፋት ጠንቆች ተነሥተው፡ ያን ያህል እልቂትንና ድምሳሴን ለምን ፈጸሙ? ይህስ ኹሉ፡ ከጥንስሱ፥ ከመሠረቱ ጀምሮ ያለእግዚአብሔር ፈቃድ ኾነ ይባላልን? አይባልም።

እንደኢትዮጵያውያን እምነት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ክህደት+ ዓመፅና አመንዝራነት የፈጸመው አንዱ ትውልዳቸው፡ የኃጢኣቱ ጽዋ ሲሞላ፡ የእግዚአብሔርን ጸጋና ረድኤት ይገፈፍና፡ የዲያብሉስ የጥፋት ኃይል ይተካል። ለዚህም፡ በዘመናችን የኾነው፡ ለአብነት ቢጠቀስ ይበቃል። ይኸውም፡ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚመራውና የሚካኼደው፡ በንግሥቲቱ እናት፡ በድንግል ማርያምና በንጉሠ ነገሥት ልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለመላው ዓለም፡ እንደገና በይፋ አረጋግጠ ለማሳወቅ፡ እግዚአብሔር፡ "መንግሥቱ፡ የማርያም ኃይል ነው" የሚል መጠሪያ ስም ያለውን÷ ነገር ግን፡ ለጥፋቱ አበጋዝ፡ ተስማሚ መሣሪያ የኾነውንና ርኅራኄ የሌለውን፡ ተራ ሰው አስነሥቶ÷ ለእርሱ የሚገባው፡ ሌላ የተሻለ ቦታ ሳይጠፋ፡ "ታዕካ ነገሥት" በተባለችው፡ በአዲስ አበባ "በዓታ ለማርያም" ዓፀደ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ አስቀምጦ፡ ምን ዓይነቱን የቀጣ ድርጊት እንዳስፈጸመ፡ በኹሉም ዘንድ የታወቀ ስለኾነ፡ ተጨማሪ ሓተታ አያስፈልገውም። ያም፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው መጽሓፌ ውስጥ በሚበቃ ተገልጿል።

ከዚህም ቀደም ብሎ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ "የማርያም ኃይል" የተባለው፡ ይህኛው መንግሥቱ፡ ሊያደርስበት ከተዘጋጀው ታላቅ ዩቅጣት ፍርድ ለመዳን ይችል ዘንድ፡ በጊዜው፡ በቶሎ ንስሓ እንዲገባ፡ እግዚአብሔር፡ የድንግል ማርያምን የቃል ኪዳን የምሕረት አማላጅነት አስቦ፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ፡ እንደጽኑ ማስተማሪያ÷ ማስጠንቀቂያና ተግሣፅ÷ እንዲሁም፡ እንደመጨረሻ የማንቂያ ደወል አድርጎ እንዲያገለግለው፡ በስምም÷ በግብርም፡ የዚህኛው ሞክሼ የነበረውን፡ "የማርያም ንዋይ (ሀብት)" የተባለውን፡ ያኛውን መንግሥቱን በመላክ፡ ያደረገለትን አምላካዊ ቸርነት፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይዘነጋውም።

እዚህ ላይ፡ አኹንም፡ ጥቂት ወደኋላ ራቅ ብለን፡ ደርሶ የነበረውን ብንመለከት፡ ኢትዮጵያን በዕብራት ለመውረር÷ ኢትዮጵያውያንንም በግፍ ለመጨፍጨፍ፡ የመጡት ባዕዳን ጠላቶች፡ እንዴት ድል ተመትተው እንደጠፉ÷ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንም፡ ከእነዚያ ወረራዎችና እልቂቶች ድነው፡ እንዴት ሊተርፉ እንደቻሉ፡ በተለይ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን፡ ራሳቸው፡ በቀላሉ ተረድተው፡ ለሌላው ለማስረዳት አያዳግታቸውም። ይኸውም፡ ይህ ኹሉ የኾነው፡ ***ከቅዱሱ ቃል ኪዳን የተነሣ መኾኑን፡ በፍጹም ስለሚያምኑ ነው።***

ለዚህም፡ በቅድሚያ፡ በ፲፰፻፷ ዓ. ም. በዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ የፍጻሜ ዘመን የኾነው ተአምር፡ ሊጠቀስ ይገባዋል። በዚያን ጊዜ፡ ያለእንዳች ተቀናቃኝ፡ የዓለሙ ብቸኛ ኃያል መንግሥት በመኾን፡ ለቅኝ ግዛት፡ የጋለ ጥማት የነበረው፡ የእንግሊዝ፡ የዘውድ መንግሥት፡ ታላቅ የኾነውን፡ የጦር ሠራዊቱን፡ ከከባድ የጦር መሣሪያው ጋር፡ ወደኢትዮጵያ አዝምቶ ሣለ፡ በተከላካዩ ቆራጥ የአገሪቱ መሪ፡ በአጼ ቴዎድሮስ ዕረፍት፡ የመጨረሻውን ድል የተቀዳጀ መኾኑ ይታወሳል።

በዚህ ጊዜ፡ ይኸው የእንግሊዝ መንግሥት፡ እንደዛሬው ዅሉ፡ ለገናንነቱና ለተስፋፊነቱ፡ "ማሰናከያ ድንጋይ" ኾናበት የኖረችውን ኢትዮጵያን፡ ከእጁ ለማስገባት ችሎ ነበር ማለት ነው፤ ነገር ግን፡ "ልዋል፤ ልደር!" ሳይል፡ ያለአንዳች ሰብአዊ ግዳጅ፡ እንደጉንዳን ሠራዊት፡ በመጣበት እግርና ጎዳና፡ ሰተት ብሎ፡ ከኢትዮጵያ ምድር ወጥቶ፡ ወደአገሩ ተመለሰ። ታዲያ፡ ይህ ነገር፡ ዕፁብ ድንቅ አይደለምን? ቀጥሎ፡ በአጼ ዮሐንስ ዘመን የተፈጸመው ሌላው ተአምር፡ ሳይወሳ አያልፍም። በዚያን ጊዜ፡ በሠለጠኑ አሜሪካውያንና በሌሎች ነጮች የጦር አበጋዞች እየተመሩ፥ በተጧሳም የጦር ትጥቅ እየታገዙ፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ፡ ለአያሌ ጊዜያት ተመላልሰው የዘመቱት፡ የቱርክ፥ የግብፅና የሱዳን እስላማውያን አልፍ አእላፉት የጦር ሠራዊቶች፡ ድል እየተመቱ መመለሳቸው፡ ዕፁብ ድንቅ አይደለምን? ከዚያ ወዲህ ተከታትሎ፡ በአጼ ምኒልክ ዘመን የተፈጸመውን ተአምር ሲያነሡት ደግሞ፡ ሌላ ዕፁብ ድንቅ የሚያሰኝ ኃይል ተደርጎ ይታያል። ይህም፡ ቀደም ብለው ለተጠቀሱት ተአምራት ጭምር፡ ማብራሪያ ይኾን ዘንድ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ጋር የሚያያዝበት ሃይማኖታዊው ምሥጢር ታክሎበት፡ እንዲህ በሚል ቃል ቀርቧል።

ዳግማዊ አጼ ምኒልክ፡ በ፲፰፻፹ ዓ. ም. በአድዋ ጦርነት፡ በካቶሊካዊው የጣልያን ሠራዊት ላይ፡ የድል አክሊልን ተቀዳጅተው እንደነበረ፥ ከ፵ ዓመታት በኋላ ደግሞ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በማይጨው ጦርነት፡ በዚያው፡ የጣልያን ተመሳሳይ ሠራዊት፡ በሽንፈት ተባርረው እንደነበረ ይታወቃል። ኢትዮጵያውያን፡ የዅለቱንም ጦርነቶች ዕድሎች ምክንያት፡ በቀጥታ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ጋር ያያይዙታል። ይኸውም፡ "እንዲህ ወይም እንዲያ የኾነበት ምክንያት፡ እነዚህ ዅለቱ አጼዎች፡ እያንዳንዳቸው፡ በቅዱሱ ኪዳን ውስጥ የተመለከቱትን ግዳጆቻቸውን፡ በእውነት አክብረው፡ በትክክል ከመፈጸማቸው ወይም በእውነት ሳያከብሩ፡ በትክክል ካለመፈጸማቸው የተነሣ መኾን አለበት" ከሚለው ሃይማኖታዊ አቋም፡ የሚመነጨው አስተሳሰብ ነው።

አዎን! አጼ ምኒልክ፡ ከቤተ ሕዝባቸው፥ ከቤተ ክህነታቸውና ከቤተ ምልክናቸው ጋር፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ማለትም፡ በቃል ኪዳን አምላካቸው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በቃል ኪዳን ንግሥታቸው፡ በድንግል ማርያም ላይ፡ ፍጹም እምነትና ሙሉ ትውክልት ስለነበራቸው፡ እነሆ፡ ያን ኃያል የነበረውን፡ የጣልያን ወራሪ ጦር፡ ያለአንዳች፡ የባዕዳን አጋርና እርዳታ፡ እጅግ በሚያስገርም ዅኔታ ድል አደረጉት። በዚህ አንጻር ደግሞ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በ፲፱፻፶ በነበረው፡ የመንግሥታት ማኅበር ላይ፡ ፍጹም እምነትን በመጣል፡ በማኅበሩ ቃል ኪዳን በመማጸናቸውና በእርሱ ብቻ በመታመናቸው፡ ይህ አድራጎት፡ ቅዱሱን ኪዳን እንደመካድና እርሱን እንደማርከስ ተቆጥሮባቸው፡ እነሆ፡ በካቶሊካዊው ሙሶሎኒ በሚመራው፡ የጣልያን ፋሺስታዊ ጦር ሠራዊት፡ ድል ተመትተው፡ ከመዋረድ ደረሱ።

በቤተ ሕዝቡና በቤተ ክህነቱ÷ በቤተ ምልክናውም መናብርት ላይ ተቀምጠው÷ በክህደት መርገምም ተወግዘውና ተይዘው በሚገኙ፡ ያገር ተወላጆች ተባባሪነት፡ ዛሬ በኢትዮጵያ፡ ሥልጣን በጨበጠውና "ሕዝባዊ አገዛዝ" በተባለው መንግሥት፡ የሚወጠነው ሥር ነቀል የኾነው ኹለንተናዊ አመራርና የሚካኼደው የሥራ አፈጻጸም፡ ባሁኑ ጊዜ ሰፍኖ የሚታይ ሌላው እውነታ ነው።

በዚህ ላይ የቀረበው ሓተታ፡ እንዲህ በሚለው አገላለጽ ይጠቃለላል፡- በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት፡ በቤተ ክርስቲያን ተቀብተውና ዘውድ ጭነው፡ በኢትዮጵያ መንበረ ዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጡ ኢትዮጵያውያን "አጼዎች"፡ ለሕዝቡ በጐነትና ደኅንነት ሲል፡ እግዚአብሔር መርጦና ሹሞ እንደላካቸው እረኞች ተቆጥረው፡ በእውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ተገቢውን እውቅናና ተቀባይነት ያገኛሉ። የቅዱሱ ኪዳን ቤተ ሕዝብ÷ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና፡ አንዳቸው ወይም ኹሉም፡ በቅዱሱ ቃል ኪዳን ላይ፡ ጽኑ የኾነ የድፍረት ወይም የክህደት በደልን በሚያደርሱበት ጊዜ ደግሞ፡ እኒያ፡ መንግሥታዊዉን ሥልጣን፡ በዓመፅና በኃይል የሚይዙት፡ የቁጣ መሣሪያዎች፡ ያ፡ የሕዝቡና የአገልጋዮቹ በደል ያስከተለውን የመርገም ቅጣት ለመፈጸምና ለማስፈጸም እንደተላኩ ተቆጥረው፡ እኒያ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን በትዕግሥት ይቀበሏቸዋል።

በዚህ ረገድ፡ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ በፊት የነበሩት፡ በጣም የቅርቦቹ "አጼዎች" ወይም "የእግዚአብሔር ሹሞች"፡ ዳግማዊ ቴዎድሮስ÷ ተክለ ጊዮርጊስ÷ ዮሐንስ አራተኛ÷ ዳግማዊ ምኒልክና ንግሥት ዘውዲቱ ሲኾኑ÷ "አብዮተኞቹ" ደግሞ፡ አማን÷ ተፈሪ÷ መንግሥቱ÷ ተስፋዬ እና መለስ ናቸው።

እንግዲህ፡ ቅርብ በኾነው ዘመናችን የነበሩትን ለመጥቀስ ያህል፡ እነአጼ ቴዎድሮስ÷ እነአጼ ዮሐንስ÷ እነአጼ ምኒልክ÷ እነብፁዕ አባ ጴጥሮስ÷ እነብፁዕ አባ ሚካኤል፡ እነእቴጌ ጣይቱ÷ እነራስ ጎበና÷ እነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስና እነደጃች ባልቻ÷ እነርሱንም የመሰሉት እውነተኞች ኢትዮጵያውያን፡ ለእርሷና እርሷ ለቆመችለት ዘለዓለማዊ ዓላማ ሲሉ፡ በሰላማዊው መስክ የፊሊጥ ትግልና በጦር ሜዳው ተጋድሎ፡ ሕይወታቸውን የሠዉላት፡ *"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት"፡ ይሀች ናት።*

እኒህ፡ የቀደሙትና ዛሬም በሕይወተ ሥጋ እየተጋደሉ ያሉት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እስከዚች ቀን ድረስ፡ ይህችኑ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በእውነት ለማገልገል÷ በፍቅር ለመጠበቅና በሕያውነት ለማስተላለፍ፡ የተቀበሉትን ኪዳናዊ አደራ፡ እስከመጨረሻው አክብረው ኖረዋል። ዛሬና ወደፊትም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጸሎታቸውን ተቀብሎ፡ በዘለዓለማዊ ሕይወት ሰፍናና ገዝፋ በምትኖረው፡ ገናና መንግሥቱ፡ ከቅድስት ድንግል እናቱ ጋር፡ በድል አድራጊነት እስከሚገለጽባት፡ እስከዳግም ምጽዓቱ ድረስ፡ ይህንኑ የፈቃድ ግዳጃቸውን ቀጥለው፡ ከግብ ለማድረስ፡ እንደገና ቃል ገብተው፡ ይኸው ህልውናቸውን ቀጥለዋል።

ጥያቄ:- *"ታዲያ፥ እኛስ: በኢትዮጵያዊነታችን: ይህን ቃል ኪዳን አክብረን ፈጽመናልን?"*

መልስ:- ይህም: እናንተው ራሳችሁ: ለእየራሳችሁ: የምትመልሱት ጥያቄ ነው::

ሰባተኛው ቃል ኪዳን፤
ኪዳነ ምሕረት::

ጥያቄ:- *"ኪዳነ ምሕረት" የተባለው: ሰባተኛው ቃል ኪዳን: የመጨረሻው መኾኑ ነውና: ስለእርሱ የምታሳውቀንን ሓተታ ልንሰማው: ተዘጋጅተን እንጠብቃለን::*

መልስ:- እግዚአብሔር: ፍጥረቱ ኹሉ: ለዘለዓለም እየታደሰ ይኖርበት ዘንድ: ከሰው ጋር ያደረገው: የመጨረሻውና ሰባተኛው ቃል ኪዳን: <u>*የምሕረት*</u> ነው:: እርሱም: እውን የኾነውና የተፈጸመው: ዳግማዊው አዳም ተብሎ: ከዳግማዊቷ ሔዋን: ከድንግል ማርያም በተወለደውና የእግዚአብሔር ልጅ በኾነው በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በዚህም: *"እስመ ትቤ ለዓለም: አሐንፅ ምሕረተ፤ በሰማይ: ጸንዓ ጽድቅከ፤ ኪዳነ ተካየድኩ: ምስለ ኅሩያንየ!"* ማለትም: *"'ኪዳኔን: ከመረጥኋቸው ጋር አደረግሁ! ምሕረትን: ለዘለዓለም: እመሠርታለሁ!' ብለሃልና፤ እውነትህ: በሰማይ ጸናች::"* የሚለው: እግዚአብሔር: ለሰው ልጆች የሰጠው የተስፋ ቃሉ ተፈጸመ::

የዚህ ቃል ኪዳን መሠረት: *"ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር: ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም!"* ማለትም: *"የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ: የእግዚአብሔር በግ እነሆ!"* የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ: ፍጥረቱን የሚያድነው: በበነጋታው ዓርብ: በእንጨት ላይ ተሰቅሎ÷ ሥጋውን ቆርሶና ደሙን አፍስሶ መኾኑን በማስረዳት: *"ንብስቱን አንሥቶ÷ ባርኮና ቆርሶ: 'ይህ ሥጋዬ ነውና: እንካችሁ ብሉ!'÷ ጽዋውንም አንሥቶ: 'ስለብዙዎች: ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ: የአዲስ ኪዳን ደሜ: ይህ ነውና: ኹላችሁ: ከእርሱ ጠጡ!'"* ብሎ: በዋዜማው ሐሙስ ማታ ያቀበላቸው ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ነው::[ደ፲፩]

በመስቀል ምልክትነት: የመጨረሻው የቃል ኪዳን ማኅተም እንዲኾናቸው: ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸውን: ይህን የቅዱስ ቁርባን ምሥጢር: ኢትዮጵያውያን: በያሉበት: በሥርዓተ ቅዳሴ አክብረው: ከዓመት እስከዓመት: ዘወትር እያዘጋጁ: ሲፈጽሙት ይኖራሉ::

የቅዱስ ቁርባን፡ የመጨረሻ ማኅተምነት።።

ጥያቄ፡- ሰባተኛው ቃል ኪዳን የኾነው፡ "ቅዱስ ቍርባን"፡ ለሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት የመጨረሻ ማኅተምነቱ፡ እንዴት እንደኾነ፡ ብታብራራልን?

መልስ፡- ኪዳነ ልቡናና ኪዳነ አሪት በተባሉት፡ የቅዱሱ ኪዳን ክፍላት ተጠቃልለው የነበሩት፡ ስድስቱ የብሉያቱ ቃል ኪዳናት የታደሱበት፡ ይህ አዲሱ የምሕረት ቃል ኪዳን፡ ለዘለዓለም ሲታሰብና ሲከበር ይኖራል። እንዲህ ሲታሰብና ሲከበር የሚኖረውም፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ይኾን ዘንድ፡ በምሥጢረ ቁርባን፡ ሥርዓተ ቅዳሴ በሚለወጠው፡ ኅብስትና ወይን ገዝፎ በሚቀርበው፡ ቅዱስ መሥዋዕት ነው።። አዎን! ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት እናቱ፡ ከድንግል ማርያም በወረሰው የነፍስና የሥጋ አካል፡ እግዚአብሔር፡ ፍጹም ሰው በመኾኑና እርሱም፡ በዚያ በለበሰው ሰውነቱ፡ በመስቀል ላይ ራሱን በመሠዋቱ፡ ለፍጥረቱ፡ ዘለዓለማዊ ደኅንነትን ስላስገኘ፡ እነሆ፡ አዲሱ የምሕረት ቃል ኪዳን በር ተከፈተ!

የሰባተኛው ቃል ኪዳን ሕያው ምልክት የኾነው፡ ይህ ምሥጢረ ቁርባን፡ ከላይ ቀደም ብለው ለታተቱትና ለዚህኛው÷ ባጠቃላይ ለሰባቱም ቅዱሳት ቃል ኪዳናት፡ የመጨረሻው ማኅተምና ዘውድ ነው።። እግዚአብሔር፡ ከሰው ጋር የሚያደርገው፡ ሌላ ቃል ኪዳን፡ ከዚህ በኋላ የለም፤ ይህ፡ የመጨረሻው ነው።። ይህም የእውነት ጒልላት የኾነው ድምጻሜ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የዕለተ ዓርብ መከራ መስቀሉን ለመቀበል፡ ከደቀ መዛሙርቱ ከመለየቱ፡ ጥቂት ሰዓታት በፊት፡"*እኔ መጥቼ ባልነገርኋቸውስ፡ ኃጢአት ባልኾነባቸውም ነበር፤ አሹን ግን፡ ለኃጢአታቸው፡ ምክንያት የላቸውም፤*" ሲል በተናገረው የጕዛዜ ቃል ተረጋግጧል።።[ዮሐ፲፭፥፳፪]

እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን፡ ፈጣሪያቸውንና እናቱን፡ ቀንና ሌሊት፡ በውዳሴ÷ በዝማሬ÷ በቅኔና በቅዳሴ በማመስገን÷ ስለእነርሱም ሓሜት በማድረግ፡ በየዕለቱ በሚያካኺዱትና በሚፈጽሙት ቋሚ ሥርዓታቸው፡ ቅዱስ ቁርባንን፡ ያለማቋረጥ ይቀበላሉ።። በዚህም አድራጎታቸው፡ ለአምላካቸውና ለመድኀኒታቸው÷ ለዘለዓለማዊው ሊቀ ካህናታቸውና ንጉሠ ነገሥታቸው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ÷ እንዲሁም፡ ለዘለዓለማዊት ንግሥታቸውና ቅድስት እናታቸው፡ ድንግል ማርያም ያላቸውን፡ የሃይማኖት ታማኝነትና የምግባር ግዳጅ፡ ዘወትር እያጸደቁና እያረጋገጡ ይኖራሉ።።

ኢትዮጵያውያን፡ ራሳቸውን፡ እንዲህ፡ ባልተቋረጠ ንስሓ እያነጹና እያጸደቁ፡ ይህን ቅዱስ ቁርባን፡ ዘወትር ስለሚቀበሉ፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊነታቸውን፡ ለመለኮታዊው የዘውድ መሪያቸውና ለንግሥት እናቱ÷ እንደዚሁም፡ ለእየራሳቸውና ለሰብአውያን ወገኖቻቸው ያረጋግጣሉ።። እውነተኞቹ የእግዚአብሔር፡ የቃል ኪዳን ልጆች መኾናቸውን፡ ለራሳቸውም ኾነ ለአምላካቸው÷ ለሌላውም ሰብአዊ ፍጡር፡ እንዲህ፡ አረጋግጠው ለማስታወቅ፡ የሚፈጽሟቸው ብዙ ምግባራት አሏቸው።።

ከእነዚህ መካከል: ቀድሞ: በዘመነ አሪት: "የፋሲካ በግ" እያሉ: በሌሊት ይበሉት የነበረውን የእንስሳ መሥዋዕት: ዛሬ: በእየቤታቸው: ለጸማቸው: ሥጋዊ መፈስኪያ ብቻ በማድረግ: እውነተኛው የፋሲካ በጋቸውና ዘለዓለማዊው የምሕረት ቃል ኪዳን ማኅተማቸው የኾነውን: የመድኃኒታቸውን: የኢየሱስ ክርስቶስን: ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም: ብቤተ ክርስቲያን: በእውነተኛ ንስሓ፥ በታላቅ ፍርሃትና በፍጹም ትሕትና የሚቀበሉበት: አዲሱ ሥርዓታቸው: አንዱ ነው::

ትምክህት እንዳይኾንባቸው: ራሳቸው ባይናገሩትም: ኢትዮጵያውያን: ለፈጣሪያቸው ባላቸው ፍቅር ምክንያት: "የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳናት: ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ተቀብለን የፈጸምን በመኾናችን: እኛ እኮ: ለእግዚአብሔር: 'የቃል ኪዳን ሕዝቦቹ' ነን፣ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነትና መሢሕነት፥ መድኃኒትነትና ንጉሥነት አምነን በመቀበላችንም: 'እውነተኞቹ እስራኤላውያንም' ነን!" ብለው: በትሑት ልባቸው ውስጥ ሠውረው ያኖሩት እምነት አላቸው፣ ይህንም: ራሳቸው: የእስራኤል ነቢያት ሳይቀሩ: ገና: በቀድሞው ዘመን: በእግዚአብሔር መንፈስ ተመልተው: በትንቢታቸው: ይፋ አውጥተውታል:: ከእነዚህም መካከል: ነቢዩ አሞጽ: *"የእስራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ: ለእኔ: እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?' ይላል እግዚአብሔር!"* ብሎ የተናገረውን ይጠቅሱታል::[ደ፰፱]

ለዚህ የእግዚአብሔር ምርጫና ድንቅ ሥራ: እስካኹን ከተጠቀሱት: የብሉዩ ዘመን ምስክሮች ጋር: ስሙና ሙያው: በመልካም የተወሳው ካህኑ ዮቶር (ራጉኤል) ይገኛል:: ሴት ልጁን: ሲጻራን: ለሙሴ የዳረለት: ይህ ኢትዮጵያዊ ካህን: አምልኮተ እግዚአብሔርንና የመሥዋዕት አቀራረብን፥ እንዲሁም: የመንግሥታዊ አስተዳደር ሥርዓትን: በአማቹ: በሙሴ አማካይነት: ለእስራኤል ሕዝብ ማስተማሩን፤ ቀደም ብዬ ገልጨላችኋለሁ::

በብሉዩ ኪዳን ውስጥ: አብርሃምን ከባረከው: ከመልከ ጼዴቅ በኋላ: ለመጀመሪያ ጊዜ: የእግዚአብሔር "ካህን" ተብሎ የተነገረለት ግለሰብ: ይኸው: ኢትዮጵያዊው ዮቶር ብቻ ስለኾነ: ቀደም ባለው ዘመን: የህልውናው ብርሃን: ለጥቂት ጊዜ: ቦግ ብሎ ታይቶ የተሠወረውን: የመልከ ጼዴቅን ማንነት: በእርሱ (በዮቶር) አማካይነት ለማወቅ ተችሏል::

በአዲሱ ኪዳን ዘመነ ምሕረት ደግሞ: "አቤሜሌክ" የተባለው: የዚያ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ: ሃይማኖታዊ ምግባር: ልዩ ዜና ኾኖ ይተረካል:: ይህ ሰው: በዓለም ላይ ከተበተኑት አይሁድ መካከል: ለበዓለ ሃምሳ (ለጰንጠቆስጤ): በኢየሩሳሌም ከተሰበሰቡት ተለይቶ: ታሪኩ: በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ: ለብቻው ተንግሮለታል፤ ሐዋርያው ፊልጶስም: በተለይ በእግዚአብሔር መልአክ ታዝዞ: አጥምቆታል:: ይህ ኹሉ ለምን ኾነ?

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡
የአዲስ ኪዳኑ "አቤሜሌክ"።

ጥያቄ፡- ለሰባተኛውና ለአዲስ ኪዳኑ የምሕረት ቃል ኪዳን ወደኢትዮጵያ መምጣት ምክንያት ስለኾነውና ስም-አልባ ይመስል፡ "ኢትዮጵያዊው፡ ጃንደረባ" እየተባለ ስለሚጠራው ደግ ሰው፡ ልናውቀው የሚገባንን እውነተኛ ዜና ብትነግረን?

መልስ፡- ሰባተኛውን ቃል ኪዳን፡ ከዜና መዋዕል ሥፍራው አግጣጫና በተለይ፡ ለኢትዮጵያውያን ካለው አግባብነት ጋር አያይዘው ሲመለከቱት፡ ዕፁብ ድንቅ ያሰኛል! አዎን! ያ፡ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ፡ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ያዘጋጀለትን መንገድ በመከተል፡ ከኪዳነ አሪት፡ ወደኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ በጥምቀት ተሸጋግሮ፡ ሉዓላዊት ለኾነችው፡ ለክርስትና እምነት የበቃባት ያች ዕለት፡ እጅግ አስደናቂ ድርጊት የተከናወነባት ታላቅ ቀን መኾኗ፡ ሊታበል ከቶ አይቻልም። ምክንያቱም፡ ያ፡ በመልከ ጼዴቅ ቃል ኪዳን የተገኘው ኢትዮጵያዊነት፡ ከአዲሱ ኪዳን የጥምቀት ጸጋ የተነሣ፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አዲስ ሰውነት፡ እንደገና ታድሶ ለፍጹምነት የበቃው፡ በዚያች ዕለት፡ በመንፈስ ቅዱስ በተካሄደው ተአምራዊ ክዋኔ በመኾኑ ነው። ይህም፡ በሌላ መልክ ሲገለጽ፡ በዚያች ዕለት፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሕይወት ላይ የታየው፡ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ለውጥ፡ ያን፡ በመለኮታዊው ዕቅድ መሠረት፡ "ምሉዕ ኢትዮጵያዊ" ለመኾን የሚያበቃውን፥ ማለትም፡ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና የተባሉት፡ እኒህ የእግዚአብሔር መንግሥት ሦስት የአካል ዘርፎች ተዋሕደው፡ በአንድ ሕያው ሰውነት ውስጥ እንዲያድሩ የሚያደርገውን የዕድገት ሥርዓት፡ ከፍጹምነት ደረጃ አደረሰው ማለት ይኾናል።

በዚያ ዅኔታ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ የአዲሱ ኪዳን ሃይማኖትና ምግባር፡ አቅኚና መሪ የኾነው ይህ፡ የተባረከ ኢትዮጵያዊ፡ መጠሪያ ስም ያለው መኾኑ እየታወቀ፡ "ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ" እየተባለ፡ በግብር ስሙ ብቻ ሲጠቀስ መኖሩ፡ አግቡብ አይኾንም። በኢትዮጵያኛ፡ "ጃን ደረባ" ማለት፡ በፍጹም ታማኝነቱ፡ "የንጉሥ ባለሟል፥ የቤተ መንግሥት በኾሮንድ፥ ወይም፡ በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ በቤተ ምልክናው ዘርፍ፡ ጠቅላይ ምሉክ" ማለት ነው፤ *"'ሕንደኬ' የተባለች፡ የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ፡ በገንዘቧም ኹሉ የሠለጠነ"* የሚለው የመጽሐፍ ቃል፡ ይህን በሥጋዊዉ ዘርፍ በኩል ያለውን ከፍተኛ ሥልጣን ያመለክታል። "ጎጃው" ከሚለው፡ ከግእዙ ቃል የተነሣ ግን፡ ታማኝነቱና ባለሟልነቱ፡ በተፈጥሮው፡ ወይም በራሱ ወይም በሌላ ሰው፡ "ስልብ" ከመኾን ጋር የማ ይ የገዘበት ገዢም አለ።

ስለዚህ፡ "እንደትውልድ ሐረግ፡ ተወራራሽ ኾኖ፡ ከእርሱ በደረሰው፡ 'አቤሜሌክ' በሚለው፡ በመደበኛው የማዕርግ ስሙ ሊጠራ፡ ፍጹም ተገቢነት አለው!' ቢባል ትክክለኛ አስተያየት ይኾናል። ምክንያቱም፡ ከእርሱ ቀደም ብሎ፡ በእውነተኛ ኢትዮጵያዊነትና በፍጹም አርአያነት ተገልጾ የታየ፡ ምሳሌውና ጥላው የኾነው፡ የብሉዩ ኪዳን ኢትዮጵያዊ፡ በዚሁ፡ "አቤሜሌክ" በሚለው ስም ይታወቅ ስለነበረ ነው። ይህ፡ የፊተኛው "አቤሜሌክ"፡ በይሁዳው ንጉሥ፡ በሴዴቅያስ ቤተ መንግሥት ባለሟል ኾኖ፡ በኋለኛው፡ ማለትም፡ የንግሥት ሕንደኬ ቤተ መንግሥት አዛዥ በነበረው፡ በ'ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ' ተመሳሳይ ሥልጣን፡ የሚያገለግል ነበረ። እርሱም፡ ቀደም ብሎ፡ ገልፈጭላችሁ እንደነበረው፡ በነቢዩ ኤርምያስ ላይ የተሰጠውን የግፍ ፍርድ፡ ወዲያው ከንጉሡ አግልዶ፡ በምሕረት ለማስለወጥ በመቻሉ፡ ኢትዮጵያዊነት ምን እንደኾነ፡ በምግባር አረጋግጦ ለማሳየት የበቃ ስመጥር ኾኗል። ስለዚህ፡ የኹለቱም "ጃንደረቦች" ኢትዮጵያዊ ሕይወት፡ በአካልና በግብር ብቻ ሳይኾን፡ "አቤሜሌክ" በሚለው ስምም እንደሚመሳሰል፡ በሃይማኖት በማረጋገጥ፡ "ስመ-ሞክሼነታቸውና ቡሩክነታቸው፡ ለኹለቱም ሊጸድቅላቸው የሚገባ ነው" ያስኛል። "አቤሜሌክ"፡ በግእዝ፡ "የንጉሥ አባት"፡ "ኤቤድሜሌክ" ደግሞ፡ "የንጉሥ አገልጋይ"፡ ማለት ነው።[ደ፰፫]

እንግዲህ፡ "ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ" እየተባለ በሚጠራው፡ በአዲሱ ኪዳን "አቤሜሌክ" መጠመቅ፥ በእርሱም አማካይነት፡ ኢትዮጵያውያን፡ የክርስትና ጥምቀትን በመቀበላቸው ምክንያት፡ ይህን ከመሰለው፡ ከመጨረሻው ሃይማኖታዊ ብቅዓት ስለደረሱ፡ ከዚህ በኋላ፡ "ቢቀ! ተመለሱ! ውጡ!" ወደማይባሉባት፡ በምድር ላይ፡ በዘለዓለማዊ ፍጹም ፍሥሓ ወደሚኖሩባት፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት "ግቡ!" ለመባል በቅተው፡ እነሆ! ህልውናቸውን፡ በእርሷ ሕይወት ውስጥ ቀጥለዋል። በዚህም፡ ዘለዓለማዊው ንጉሥ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"እውነት እውነት እልሃለሁ! ሰው፡ ከውኃና ከመንፈስ፡ ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይችልም"* ሲል ለኒቆዲሞስ አረጋግጦ፡ እጅግ በሚያስተማምን ኹኔታ፡ ባሰማው አዋጅ ተፈጽሞላቸዋል።[ደ፰፬]

በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ከአዳም ጀምሮ እስከንግሥተ ሳባ ዘመን ስፍኖ የነበረው፡ የኪዳነ ልቡና አምልኮ፡ በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ፡ በኪዳነ አራት ከጸና በኋላ፡ "ሕንደኬ" በተባለችው፡ የኢትዮጵያ ንግሥት ዘመን ደግሞ፡ እነሆ፡ ያ፡ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ፡ አቤሜሌክ፡ እንደኪዳነ አራቱ ሥርዓት፡ ሊሰግድ፡ ወደኢየሩሳሌም ኼደ። ከኢየሩሳሌም ወደአገሩ ሲመለስም፡ ገና ወደጋዛ በሚመለደው መንገድ ላይ ግለ፡ ሰውብ ድንቅ የኾነውና ከሐዋርያት ሥራዎች ኹሉ የተለየው፡ ታላቁ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ቸርነት፡ ለኢትዮጵያውያን ተደረገ።

ጥያቄ፡- *ለኢትዮጵያውያን የተደረገው፡ ዕውብ ድንቅ የሽነውና ከሓዋርያት ሥራዎች ጕሉ የተለየው፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ቸርነት፡ ምንድር ነው?*

መልስ፡- ይህ ታላቅ፡ መለኮታዊ ቸርነት፡ በሚከተሉት ኹነታዎችና ድርጊቶች ተከሥቷል፤ እነዚህም፡-

፩ኛ፡- ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አቤሜሌክ፡ ከኪዳነ ልቦና ወደኪዳነ አራቱ የተሸጋገረበት እምነትና ይዞት የኖረው እውቀት፡ እውነተኛ በመኾኑ፡ *ሣጓም መምህር ሳይመራው፡ መንፈስ ቅዱስ ብቻ* በገለጠለት፡ ስለኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገረውን፡ የኢሳይያስን ትንቢት አውጥቶ *መመልከቱ*÷

፪ኛ፡- ሓዋርያው ፊልጶስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተነጥቆ፡ ኢትዮጵያዊው መንገደኛ አለበት ሠረገላ ድረስ መጥቶ፡ ለብቻው እንዲያነጋግረውና እንዲያጠምቀው፡ በእግዚአብሔር መልአክ *መታዘዙ*÷

፫ኛ፡- ሓዋርያው፡ ወደኢትዮጵያዊው፡ ድንገት ቀርቦ፡ በተገናኘውና ስለሚያነብበው መጽሓፍ በጠየቀው ጊዜ፡ ወደሠረገላው ወጥቶ፡ ከእርሱ ጋር ይቀመጥ ዘንድ÷ ስለመጽሓፉም ያስረዳው ዘንድ፡ ኢትዮጵያዊው፡ ሓዋርያውን *መለመኑ*÷

፬ኛ፡- ሓዋርያው፡ የመጽሓፉ የትንቢት ቃል መፈጸሙን፡ ለኢትዮጵያዊው ባበሠረው ጊዜ፡ ፊልጶስ፡ "*ይህን ታምናለህን?*" ብሎ ሳይጠይቀው፡ ራሱ፡ አቤሜሌክ፡ "*ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ኾነ አምናለሁ!*" ማለቱ÷

፭ኛ፡- ኢትዮጵያዊው፡ እመንደር÷ ወይም፡ እከተማ÷ ወይም፡ እማረፊያው እስኪደርስ፡ "ልጠብቅ!" ሳይል፡ ገና፡ በሠረገላው እየተጓዙ ሣሉ፡ በመንገዳቸው ዳር፡ ውኃ ያለበት ሥፍራ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያጋጥመው፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት የሚያስገባውን ሥርዓተ ጥምቀት ለመፈጸም የሚያስፈልገው ነገር ውኃ ከኾነ፡ "*እነሆ ውኃ! እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው?*" ብሎ፡ እንደገና፡ ራሱ፡ ሓዋርያውን መጠየቁ÷

፮ኛ፡- ኢትዮጵያዊው፡ "*በፍጹም ልብህ ብታምን፡ ተፈቅዷል!*" የሚለውን መልስ፡ ከሓዋርያው ሲያገኝ፡ እምነቱ፡ ፍጹም በመኾኑ፡ ሠረገላው፡ ወዲያው እንዲቆም አዘዘ፡ ኹለቱም፡ ወደውኃው ወርደው፡ መጠመቁ÷

፯ኛ፡- ከውኃው ከተመለሱ በኋላ፡ ሓዋርያው ፊልጶስ፡ የተላከበትን ተግባር ስለፈጸመ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳመጣው፡ ነጥቆ ሲወስደው፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ ከደስታው ብዛት የተነሣ፡ የሓዋርያውን ከአጠገቡ በድንገት መሠወር ሳያስተውል፡ ወደአገሩ የጀመረውን ጕዞ መቀጠሉ ናቸው።።

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አቤሜሌክ፡ ይህን ኹሉ እውቀት፡ አስቀድሞ፡ ከወዴት አገኘው? ይህንስ ተቀዳሚ ዝግጅት ለማድረግ፡ እንዴት ቻለ? የመጽሐፉን ቃልና የሐዋርያውን የፊልጶስን ትምህርትስ፡ ያለጥያቄና መልስ፡ በቀላሉ ለመቀበል፡ ለምን የበቃ ኾነ?

እግዚአብሔር፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በልቦናው ጽፎ ካስተማረው ጋር፡ ራሱም፡ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ፡ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት፡ አስቀድሞ ያወቀውና በቅድሚያ የተሰናዳበት፥ ከበፊት የተረዳውና የተማረው ነገር ቢኖር አይደለምን? ይኸውም፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ኢትዮጵያዊነት ማለት ነው። ደግሞም፡ *"ትውልዱንስ ማን ይናገረዋል?"* የሚለውን፡ የነቢዩን ቃል፡ ኢትዮጵያዊ በኾነው ሰውነቱ ላይ ያደረው መንፈስ ቅዱስ፡ ተርጒሞና ሕያው አድርጎ ማናገሩ አይደለምን? በዚህ ጊዜ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እነዚያን፡ ከትንሣኤው በኋላ፡ አይተውት ያመኑበትን ደቀ መዛሙርቱን እንኳ ሳያመሰግን፡ *"ሳያዩ የሚያምኑብኝ፡ ብፁዓን ናቸው!"* ያለው ቃሉ፡ እነሆ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ በዚህ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ላይ፥ በእርሱም ምክንያት፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ፥ ወደፊትም፡ እስከዓለም ፍጻሜ፡ በመላዎቹ ኢትዮጵያውያን ላይ ተፈጻሚ ኾኖ ሊገኝ በቃ።[፻፰፯]

ለብፅዕና የሚያበቃው፡ ኢትዮጵያዊው ሃይማኖትና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን።

ጥያቄ፡- *ኢትዮጵያዊው ሃይማኖት፡ "ሳያዩ የሚያምኑብኝ፡ ብፁዓን ናቸው!" ለሚለው መለኮታዊ ጸጋና ክብር፡ "የሚያበቃ ኾነ!" ማለትህ ነውን?*

መልስ፡- አዎን! ኢትዮጵያውያን፡ ማናቸውንም መከራ፡ በትዕግሥት ሥቃቅመው፡ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ድረስ ያሉትን፡ ሰባቱን ቅዱሳት ኪዳናት፡ በሕይወታቸው በመግለጥ፥ በመጠበቅና ከትውልድ ወደትውልድ በማስተላለፍ ያሳዩት ያልተበገረ ጽናት፡ ምንጊዜም ሳይናወጽ እንደነበረ ቀጥሏል። በረኻሙ ህልውናቸው ጉዳና ላይ የገጠማቸውንም፡ እያንዳንዱን የፈተና ዘመን፡ እያሸነፉ ሊያልፉ የቻሉት፡ ለብልሃቱም ኾነ ለመፍትሔው፡ ሰብአዊው ጥበብ በፈለሰፈው፡ በረቂቁና በግዙፉ የኃይል መሣሪያና ሀብት በመጠቀም ሳይኾን፡ በእግዚአብሔር መንፈሳዊ ጥበብ፥ ሀብትና ኃይል በመተማመን ብቻ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ ሲሉ የፈጸሙት፡ ይህን የመሰለው፡ ሃይማኖታዊ ምግባራቸው፡ እንዲህ፡ እንደብረት ሰንሰለት ተጠናክሮ ሳይቋረጥ ሊቀጥል የቻለበት ምክንያት፡ ሥውር አይደለም፤ *"ካላየሁትና ካልዳሰስኩት አላምንም"* ላለው ለደቀ መዝሙሩ፡ ለቶማስ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"አንተ ስላየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ፡ ብፁዓን ናቸው!"* ብሎ የተናገረው ቃሉ፡ ይህን እውነታ ገልጾና አረጋግጦ ያስረዳል።

ይህ የጌታ ቃል፡ እውን ኾኖ ሲፈጸም ለማየት፡ ረዥም ጊዜን አልወሰደም። ይህም፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ "አቤሜሌክ"፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ቀደም ብሎ አስተምሮት ካገኘው እውቀት÷ በእርሱም መሪነት፡ ስለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከመጽሓፍ ካነበበውና ከፊልጶስ አንደበት፡ በቃል ተነግሮት ከሰማው በቀር፡ በአካል ገዝፎ ያየውና የተመለከተው አንዳች ነገር ሳይኖር፡ በፈጸመው፡ ትንግርታዊ የሃይማኖት ምግባር ተከሥቷል። ይኸውም፡ *"ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ኾነ አምናለሁ"* ሲል የሰጠው ፈጣን የሃይማኖት መልስና የጥምቀቱ ሥርዓት፡ እዚያው እመንገዱ ላይ እንዳሉ እንዲፈጸምለት፡ ለሓዋርያው ፊልጶስ፡ ወዲያው ያቀረበው ጥያቄ፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ የጌታ ቃል፡ በገሃድ ለመድረሱ፡ ፍጹም ማስረጃ መኾኑ ነው።

ደግሞም፡ ይህ ኢትዮጵያዊ፡ እግዚአብሔር እንደቃል ኪዳኑ፡ ለሚያምኑበት በሰጠው ጸጋ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ሲያያዝ የደረሰውንና ይዞት የኖረውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖቱን፡ አኹን፡ የራሱ፡ ኢትዮጵያዊ ወንድሙ የ'ኾነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ባስገኘለት አዲስ ኪዳን አድሶና አጽንቶ ሊቀጥል የቻለው፡ በሰው ትምህርትና ኃይል ሳይኾን፡ በመንፈስ ቅዱስ አስተማሪነትና አጋዥነት መኾኑን፡ ይኸው ኹናቴ ያረጋግጣል። ይህ እውነታ የማይታበል መኾኑንም፡ ያን የመሰለው የመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ሥራ፡ እንኳንስ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት፡ ከእግዚአብሔር ጋር ተሣሥረው ለኖሩት ኢትዮጵያውያን ቀርቶ፡ ለአሕዛብ ጭምር የተፈጸመላቸው መኾኑን፡ *"ከጴጥሮስ ጋር የመጡት ኹሉ፡ ከተገረዙት ወገን የኾኑ ምእመናን፡ በአሕዛብ (በእነቆርኔሌዎስ) ላይ ደግሞ፡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለፈሰሰ ተገረሙ!"* የሚለው የመጽሓፍ ቃል ያስረዳል።[፻፳፰]

ከዚህም በላይ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በምድር ላይ እየተመላለሰ፡ ገና በማስተማር ላይ እያለ፡ *"ሰዎች፡ እኔን፡ ማን ይሉኛል?"* ብሎ፡ ደቀ መዛሙርቱን ጠይቋቸው፡ *"'ከነቢያት፡ አንዱ ነው!' ይሉሃል፤"* ባሉት ጊዜ፡ *"እናንተስ፡ ማን እንደኾንሁ ትላላችሁ?"* ብሎ፡ መልሶ ላቀረበላቸው ጥያቄ፡ ከእነርሱ፡ አንዱ ከኾነውና አብሮት፡ በአጠገቡ ከነበረው፡ ከቅዱስ ጴጥሮስ ያገኘው መልስ፡ *"አንተ፡ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ!"* የሚለውን ነበር። በዚህ ጊዜ፡ ጌታችን፡ በሰጠው መልስ፡ *"የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ! በሰማያት ያለው፡ አባቴ እንጂ፡ ሥጋና ደም፡ ይህን አልገለጠልህምና፡ ብፁዕ ነህ! እኔም እልሃለሁ፤ 'አንተ ዓለት ነህ፤ በዚችም ዓለት ላይ፡ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ፤'"* የሚለውን መለኮታዊ ቃል ኪዳን አግኝቷል።

እንደዚሁ ኹሉ፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አቤሜሌክ፡ *"ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ኾነ አምናለሁ!"* ብሎ በተናገረ ጊዜ፡ በዚያች ቅጽበት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ሳያዩ የሚያምኑብኝ፡ ብፁዓን ናቸው!"* ካለው የበረከት ቃሉ ጋር፡ አይቶት ላመነበት፡ ለቅዱስ ጴጥሮስ፡ የሰጠው ቃል ኪዳን፡ ሳያዩት ላመኑበት ኹሉ፤ በተለይም፡ ቀደም ብሎ ለኢትዮጵያውያን፡ በበለጠ ተፈጻሚ ኾነ።[፻፳፱]

እንዲህ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ለምልሞና አብቦ የኖረውን፡ የዚህን ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ፡ ሕያው ሰውነት መድረክ አድርጎ፡ እግዚአብሔር፡ ለዘለዓለም ፍሬ ያበቃውን፡ ሃይማኖታዊ ምግባር፡ ከሓዋርያው ቶማስና ከአይሁድ የሃይማኖት ምግባራት ጋር ሲያነጻጽሩት፡ በምንም መልኩ፡ ሊመዝኑት ያዳግታል፤ ይኹን እንጂ፡ እጅግ የራቀና የከፋ ከኾነው፡ ከአይሁድ ይልቅ፡ የቶማስ ሃይማኖት፡ የተሻለ ኾኖ ይገኛል።

ቀደም ብሎ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ በአዳምና በሔዋን፡ በኪዳነ ልቦና ተመሥርታና በኪዳነ አሪት ተጠናክራ፡ በመጨረሻ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለኪዳነ መንፈስ ቅዱስ የበቃችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው ኢትዮጵያ፡ በዚህ፡ ፍጹም በኾነው፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ የሃይማኖትና የምግባር ፍሬ፡ በቤተ ሕዝብነቷ÷ በቤተ ክህነቷና በቤተ ምልክናዋ አቋምና ሥርዓት፡ እነሆ፡ ከፍጹምነት ደረሰች። ይኸውም፡ እስከዚያን ጊዜ ድረስ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በኪዳነ ልቡናና በኪዳነ አሪት ጸንታ የቆየችው፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት፡ በዚያች አፍታ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ተፈጽማና ስሟን፡ በአዲሱ የኪዳነ ምሕረት ለጋሽ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ አድሳ፡ ቤተ ክህነቷን፡ "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን" አሰኘች ማለት ነው።

ስለዚህ፡ ኢትዮጵያ፡ በዚች የቤተ ክህነት ዘርፏ አማካይነት፡ ዘመነ አበውንና ዘመነ ነቢያትን፡ አልፋ÷ እንዲህ እያደገች መጥታ፡ ከዘመነ ሓዋርያት ከደረሰች በኋላ፡ ጥንት፡ በኪዳነ ልቡና የመሠረታት መሪዋ÷ ባለቤቷና ሊቀ ካህናቷ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በራሱና በእናቱ ኢትዮጵያዊ ቤተ መቅደስነት፡ ከፍጹምነት ደረጃ ያበቃት፡ የመጀመሪያዋና እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ናት። እንዲህ ናት እንጂ፡ አንዳንዶች እንደሚሉት፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፡ በ፬ኛው ምዕት ዓመት የተቋቋመች አይደለችም።

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ "የአብርሃም ልጆች ነን!" የሚሉት አይሁድ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመካከላቸው ተወልዶ፡ ነቢያት የተናገሩለት፡ እርሱ መኾኑን በማረጋገጥ እያስረዳቸውና ትምህርቱን ከአንደበቱ እየሰሙ÷ እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርግ የሚችለውንም ተአምራትና ኃይል፡ በቃሉ በመፈጸም፡ በገሃድ እያሳያቸው፡ አብሩዋቸው የኖረ ሲኾን፡ በእርሱ አለማመናቸው ብቻ ሳይኾን፡ *"ራሱን፡ የእግዚአብሔር ልጅ አድርጓልና፡ እንደሕጋችን፡ ሊሞት ይገባዋል!"* ብለው፡ ይዘው፡ እንዲገድለው፡ ለአረማዊው፡ ለጲላጦስ፡ አሳልፈው ሰጡት። ጲላጦስም፡ *"ንጉሣችሁን ልስቀለውን?"* ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ፡ *"ለእኛ፡ ከቄሣር በቀር፡ ንጉሥ የለንምና፡ ስቀለው! ...ደሙ፡ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይኹን!"* ብለው፡ እንዳስገደሉት፡ ወንጌላውያን ጽፈዋል።[፱፭]

ኢትዮጵያውያን ግን፡ ገና ቀድሞ፡ እግዚአብሔርን፡ በኪዳነ ልቡና፡ እያመለኩ ሣሉ፡ አባታቸው መልከ ጼዴቅ በቄረቄራት፡ በኢየሩሳሌም፡ እግዚአብሔር፡ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ያነገሠው፡ "ሰሎሞን" የተባለ ንጉሥ፡ ለእግዚአብሔር፡ ቤተ መቅደስን እያሳነጸ መኾኑን ሰሙ።

በዚያን ጊዜም፡ በመንፈሳዊ ደስታ ተመልተው፡ ያ ዜና፡ እውነት መኾኑን ለማረጋገጥና ሥራውን ለማየት፡ ዝናዋን፡ ራሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረላት ንግሥታቸው፡ ማክዳ ሳትቀር፡ በጋዛ በኩል፡ ወደዚያ፡ ወደምድረ ከነዓን ተጓዙ። እዚያም ደርሰው፡ ባዩት ቁም ነገርና ባገኙት የሥራ ፍሬ፡ የተሰማቸው መንፈሳዊ ደስታ፡ የቱን ያህል ጥልቅና ጽኑ እንደነበረ፥ የዚያን ጊዜዎቹ ኢትዮጵያውያንም፡ ምን ዓይነት ሃይማኖት የነበራቸው ሕዝብ እንደነበሩ፥ ለምንስ፡ እስከኢየሩሳሌም ድረስ እንደተጓዙ፥ ራሳቸው፡ እስራኤላውያን፡ ስለንግሥተ ሳባ ጉዞ የጻፉት፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቀዳማዊው ክፍል የኾነው፡ ብሉዩ ኪዳን፡ በሚበቃ መዝግቦታል።

እርሱም፡ እንዲህ ይላል፡- *"የሳባም ንግሥት፡ በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን፡ የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ፡ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች። ...ሠርቶት የነበረውን ቤት፥ ...በእግዚአብሔርም ቤት የሚያሳርገውን መሥዋዕት ባየች ጊዜ፡ ነፍስ አልቀረላትም።*

"'...አንተን የወደደ፥ በእስራኤልም ዙፋን ያሰቀመጠህ፡ አምላክህ እግዚአብሔር፡ የተባረከ ይኹን! እግዚአብሔር፡ እስራኤልን ወድዶታልና! ስለዚህ፡ ፍርድና ጽድቅ ታደርግ ዘንድ፡ ንጉሥ አድርጎ አስነሣህ።'"

በዚያን ዘመን፡ በጣያትና በልዩ ልዩ ባዕድ አምልኮ ተውጠ ከነበረው የአካባቢያቸው ዓለም ተለይተው፡ በእግዚአብሔር የሚያምኑና እርሱን ብቻ የሚያመልኩ፥ በክህነትም የሚያገለግሉት፡ ካህኑን ዮቶርን የመሰሉት፡ የመልከ ጼዴቅ ልጆች የኾኑት ኢትዮጵያውያን ብቻ ስለነበሩ፡ ስለንጉሥ ሰሎሞን የሰሙት ዜና፡ እውነት መኾኑን ለማጣራትና ለማረጋገጥ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጠው፡ ራሷ ንግሥቲቱ ማክዳ፡ ወደኢየሩሳሌም ተጉዛ፡ ራሱን፡ ንጉሥ ሰሎሞንን፡ በተለያየ ዘዴና ስልት፡ በቃል ጥያቄ፡ ሃይማኖቱን መረመረችው፤ *"በእንቆቅልሽ ፈተንኾው!"* ማለት፡ ትርጉሙ ይህ ነውና። ከዚያ በኋላ፡ ሰሎሞን የሠራቸውን የቤተ መንግሥት ሕንፃዎች፡ እየተዘዋወረች ጎበኘች፤ የደነገጋቸውንም ሥርዓቶች፡ በሥራ ላይ ሲውሉ ተመለከተች፤ አደነቀችም። ባሳነፀው ቤተ መቅደስ ተገኝታ፡ ለእግዚአብሔር የሚያሳርገውን መሥዋዕት ባየች ጊዜ ግን፡ ከተሰማት ኹለንተናዊ ደስታ የተነሣ፡ ልትሞት ደረሰች፤ *"ነፍስ አልቀረላትም!"* ማለት፡ ትርጉሙ፡ "በደስታ ሞትሁ!" ወይም፡ "ነፍሴ ጠፋ!" እንደሚለው የአነጋገር ዘዬ ዓይነት መኾኑ ነውና። ንግሥቲቱ ማክዳ፡ ባየችውና ባገኘችው ኹሉ ስለተደሰተች፡ ንጉሡን ሰሎሞንን አሞገሰችው፤ የወሰደችለትንም ስጦታ አበረከተችው።

በመጨረሻም፡ ለምታመልከው ፈጣሪዋ፡ ለልዑል እግዚአብሔር፡ ምስጋናዋን አቀረበች፤ እንደእርሷና እንደሕዝቧ፡ በእግዚአብሔር የሚያምን ንጉሥና ሕዝብ መኖሩን አሳይቷታልና፤ በእርሷና በንጉሡ አማካይነት፡ ኹለቱን የሕዝብ ወገኖች አገናኝቷቸዋልና። እንዲህ አድርጎ፡ የመጣችበትን ዓላማዋን አስፈጽሞ፡ ደስ ስላሰኛት፡ እግዚአብሔርን አመሰገነች።[ደ፻፴፭]

ይህች ንግሥት ማክዳ፡ ወደአገርዋ፡ ወደኢትዮጵያ ከተመለሰች በኋላ፡ እግዚአብሔር፡ ለንጉሡ ለቅዱስ ዳዊት፡ የሰጠውን ቃል ኪዳኑን ጠብቆ፡ እንዲፈጸም የሚያደርግበትን ጥበብ፡ በእርሷና በልጁ፡ በሰሎሞን ግንኙነት ምክንያት፡ አከናውኖት ኖሮ፡ እነሆ፡ ንግሥቲቱ ማክዳ፡ በኢየሩሳሌም ሣለች፡ ከንጉሡ ከሰሎሞን የፀነሰችውን ሕፃን ወለደች። እርሱም፡ ወንድ ልጅ ስለነበረ፡ ስሙ፡ "ምኒልክ" ("ምን ይልክ"፡ "ምን ይልቅ" ፡ ወይም፡ "የንጉሥ ልጅ" ለማለት፡ "አብነ መለክ") ተባለ። ይኸው ልጇ፡ አካለ መጠን ባደረሰ ጊዜ፡ አባቱን አይቶ የሚመለስ መኾኑን፡ ቃል አስገብታው፡ ወደኢየሩሳሌም ላከችው። ልጇ ምኒልክም፡ ቃሏን ጠብቆ፡ የእስራኤል በኵራትና ምርጦች ከኾኑት ወገኖች ጋር፡ ወደእናቱና ወደአገሩ ተመለሰ።

በዚያን ጊዜ፡ ኢትዮጵያውያን፡ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካይነት ወደአገራቸው ያመጡት፡ የዳዊትን የቃል ኪዳን "ሥጋዊ ዘር" ብቻ ሳይኾን፡ ለኪዳኑ አሪት ሃይማኖት፡ መሠረት የኾነችውን፡ "ታቦተ ጽዮን"ን ጭምር እንደነበረ፡ ቀደም ብሎ ተገልጧል። አስቀድሞ በነበረው፡ በኪዳኑ ልቡና አምልኳቸው ላይ ጸንቶ በቀጠለው፡ በዚህ፡ በኪዳኑ አሪቱ ሥርዓተ አምልኳቸው፡ የነቢያት ትንቢት የሚፈጸምበትን ጊዜ፡ በታላቅ ጉጉት ይጠባበቁም ነበረ።

ይህ ተስፋ የደረሰ መኾኑን፡ የአዲስ ኪዳኑ "አቤሜሌክ" በተባለው፡ በኢትዮጵያዊ ጀንደረባ ወገናቸው አማካይነት፡ ዜናውንና እርሱ፡ ለብፅዕና የበቃበትን ጥምቀቱን ጭምር ሲሰሙ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ መኾኑን፡ በመልክ ጸያጌ ሽመትም፡ ዘለዓለማዊ ሊቀ ካህናትነቱንና ንጉሠ ነገሥትነቱን፡ ያለአንዳች ማመንታትና መዘግየት፡ ወዲያው፡ በሃይማኖት ተቀበሉ።

ኢትዮጵያውያን፡ እንዲህ አድርገው፡ በቅዱሱ ኪዳን የክርስትና ሃይማኖታቸው ጸንተው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናትነትና ንጉሠ ነገሥትነት፡ በቅድስት ድንግል ማርያምም ቤተ መቅደስነትና ንግሥትነት፡ "ሥዩመ/ሥይምተ እግዚአብሔር" እያሉ፡ በሚቀቧቸው አጼዎችና ንግሥቶች መሪነትና በአኵስም ጽዮን ንቡረ እድ፡ ቋሚ ተጠሪነት፡ ለቤተ ሕዝቡ፡ ቢትወደዱን፡ ለቤተ ክህነቱ፡ አጨጌውን፡ ለቤተ ምልክናውም፡ ጸሓፌ ትእዛዙን፡ በእየዘርፉ መንበሮች ላይ፡ በእልቅና እየመረጡና እየሾሙ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው አገራቸው፡ በኢትዮጵያ፡ ህልውናቸውን ቀጠሉ። የኋላ ኋላም፡ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት፡ ብቁና የተሟላ ለማድረግ፡ የሚረዷቸውን "ጳጳሳት"፡ ስጦታና ገጸ በረከት እየላኩ፡ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሲያስመጡ ኖሩ።

የክርስትና እምነት መሠረት የኾነው፡ ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ ወደኢትዮጵያ መጥቶ፡ ኢትዮጵያውያን የተቀበሉት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወርኃ፡ መንፈስ ቅዱስ በወረደበት፡ በመጀመሪያው ዘመን መኾኑ፡ እንዲህ፡ ተረጋግጦ እየታወቀ፡ ክርስትና፡ ወደኢትዮጵያ የገባው፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፡ በ፴፫ው ምዕት ዓመት እንደኾነ ለማስመሰል፡ የሚደረገው ሙከራ፡ ሕያው ከኾነው፡ ከእውነተኛው የኢትዮጵያ ዜና መዋዕል የራቀ፡ ታላቅ ስሕተት መኾኑን፡ ራሱ፡ የአዲሱ ኪዳን ቅዱስ ቃል ይመሰክራል።

ያ ዘመን ግን፡ በእኹት ጊዜ፡ በኢትዮጵያ ሰፍኖ እንደሚገኘው ዓላዊ (የክህደት) ሥርዓት፡ በ፲፱፻፬ ዓመተ ምሕረት ግድም፡ በአገሪቱ ይገዛ የነበረው አረማዊ መንግሥት፡ ይህን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት፡ በይፋ ተቀብሎ ያወጀበትና በግብዕ ቤተ ክርስቲያን የተሾመው የመጀመሪያው ጳጳስ፡ ወደኢትዮጵያ የገባበት ብቻ ነበር። ይህ የጠላትነት ሙከራ፡ "ኢትዮጵያ" የሚለውን፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተጽፎ የሚገኘውን፡ የታወቀ ስያሜ፡ በእኹት ጊዜ፡ በተለያየ ትርጓሜ ለማዛባትና በሌላ አገር ስም ለመተካት፡ ከሚፈጸመው ደባ ጋር ይመሳሰላል።

ስለዚህ፡ እግዚአብሔር፡ ጥንት፡ በዘመነ ብሉይ፡ በመልከ ጼዴቅ፡ የእውነትና የሰላም ሰውነት ላይ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ በኪዳነ ልቡና፡ የተከለው፡ የማዕርገ ክህነት ተክል፡ በእነዮቶር ሥልጣነ ክህነት፡ ለምልሞና በኪዳነ አሪቱ ሥርዓት፡ በእነለዒ ካህናት አዛርያስ፡ አብዞ ከቆየ በኋላ፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ በአቤሜሊክ ሃይማኖትና ጥምቀት፡ ለኪዳነ መንፈስ ቅዱስ በቃ። ከዚያም፡ ኢትዮጵያዊነትን የተቀበለውን፡ "ፍሬምናጦስ"ን፡ ወደእስክንድርያ ልኮት እስከነበረው፡ እስከሊቀ ካህናት እንበረም ድረስ ቀጥሎ፡ በአኮስም ንዑራነ እድና ኢትዮጵያውያን እጨጌዎች አማካይነት፡ እስከዘመናችን ደርሷል። በዚህም፡ ኢትዮጵያውያን፡ እንደሌላው ይዘታቸው ኹሉ፡ ለአዲስ ኪዳኑ ሥልጣነ ክህነትም ባለቤትነት፡ የሚቀድማቸው፡ ሌላ ተወዳዳሪ ሕዝብ አለመኖሩን አረጋግጠዋል።

ይህ፡ የቅዱሱ ኪዳን አካል የኾነውና በሊቀ ካህናትነት ደረጃ፡ ከትውልድ ወደትውልድ ሲተላለፍ፡ የኖረው "ማዕርገ ክህነት"፡ እነሆ፡ ያለማቋረጥ፡ ሲያያዝ መጥቶ፡ በእግዚአብሔር ቸርነት፡ ለዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ሕያው ውርስ ሊኾን ችሏል።

በእነዚህ ኹሉ ምክንያቶች በቂ ማስረጃነት፡ የኢትዮጵያ "ቤተ ክርስቲያን"፡ ከቀሩት የዓለም አብያተ ክርስቲያን ጋር፡ ኋላ፡ በዘመነ ሐዲስ፡ እንዲያውም፡ በ፩ኛው ምዕት ዓመታት የተቋቋመች ለማስመሰል ተብሎ፡ በባዕዳን የተሰጣት፡ "አርቶዶክሳዊት" የሚለው መለያ ስያሜ፡ ለእርሷ ሊኾን አይገባም። ካስፈለጋት፡ "ተዋሕዶ" የሚለው ቃል ይበቃታል። በዘመነ አበው፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከዘመነ አሪት፡ ከዚያም፡ እስከዘመነ ሐዲስ፡ ባሉተቋረጠ ሀልውና፡ የኖረች በመኾኗ፡ "<u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን</u>" ተብላ፡ እውነተኛውንና ሕያው የኾነውን መጠሪያ ልትይዝ ይገባል።

እንግዲህ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በእናቱ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ምክንያት፡ በሥጋዊ ዘሩ፡ በሥልጣነ ክህነቱና በሥርወ መንግሥቱ፡ ከእነርሱ፡ ከኢትዮጵያውያን ጋር፡ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ፡ እንዲህ፡ የተሣሠረ ዝምድናና ግንኙነት ያለው ወገናቸው መኾኑን፡ ለራሳቸው፡ በሃይማኖት ተቀብለው፡ ለሌላውም ኹሉ አሳውቀዋል።

በዚህ መሠረት፡ ኢትዮጵያውያን፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ካህኑ ለዓለም፥ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ፣ ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ::" የሚለውን ቃለ ዓርማ፡ ለእርሱ ሰጥተው፡ አምላካቸውና መድኃኒታቸው ብቻ ሳይኾን፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ፥ ምድራዊና ሰማያዊ፥ የዛሬና የዘለዓለም ሊቀ ካህናታቸውና ንጉሠ ነገሥታቸው ሥምር መኾኑን፣ ለእናቱም፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀቡ እግዚአብሔር፣ ድንግል ማርያም፥ እሙ ወእምነ፣ ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ::" የሚለውን ቃለ ዓርማ ሰጥተው፡ እናታቸውና እመቤታቸው ብቻ ሳትኾን፡ ሥጋዊትና መንፈሳዊት፥ ምድራዊትና ሰማያዊት፡ የዛሬና የዘለዓለም አገራቸውና ንግሥታቸው ሥምር መኾኗን፡ ለራሳቸው በሃይማኖት፥ ለዓለምም በይፋ፡ አረጋግጠው ማኅተማቸው፡ ፍጹም ተገዢነት ያለው አድራጎት ኾነ::

በምድር ላይ ከሚኖሩ ሕዝቦች መካከል፡ በዘመነ ብሉይ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ የተገለጹትን፡ ስድስቱን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳናት፥ በዘመነ ሐዲስም፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከፍጻሜ የደረሰውን፡ ዘለዓለማዊዉን ቃል ኪዳን፡ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ፡ በገዛ ፈቃዳቸውና ፍላጎታቸው፥ ምርጫቸውና ውሳኔያቸው፡ በሙሉ ተቀብለውና አስካኹን፡ በጽኑ ፍቅር ጠብቀው ለመገኘት የበቁ፡ ኢትዮጵያውያን ብቻ በመኾናቸው፡ ነቢዩ አሞጽና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተናገሩዋቸው ቃሳት፡ የተገቡ መኾናቸውን አስመስክረዋል::

ጥያቄ፡- *"ታዲያ፥ እኛስ፡ በኢትዮጵያዊነታችን፡ ይህን ቃል ኪዳን አለብረን ፈጽመናልን?"*

መልስ፡- ይህም፡ እናንተው፡ ለእየራሳችሁ፡ የምትመልሱት ጥያቄ ነው::

ምዕራፍ ፮

"ኢትዮጵያዊነት" ተከሥቶበት የኖረው፡ ስምና ህልውና።

ጥያቄ፡- "ኢትዮጵያ" ከሚለው ስም ጋር የተዘምዶ ግንኙነት አላቸው ከተባሉት፡ ቀደም ብለህ ከጠቀስህልን ቃላት መካከል፡ በመጨረሻ ስለተወሳው፡ "ዐምሐራ" ስለሚለው መጠሪያ ቃል፡ በዝርዝር ማወቅ ስለምንፈልግ፡ ተገቢውን ማብራሪያ፡ ሳትቆጥብ ብትሰጠን?

መልስ፡- ይህ፡ "ዐምሐራ" የሚለው፡ ሕዝባዊ የመጠሪያ ቃል፡ ከ"ኢትዮጵያዊነት" ጐን፡ አገር-በቀል ኾኖና ረዥም ዕድሜ ባለው፡ የህልውና ሓረግ ተሣሥሮ የኖረ በመኾኑ፡ አዎን፡ ለተነሣንበት አርእስት፡ በእርግጥ፡ የበለጠ አግባብነት አለው። አግባብነቱም፡-

፩ኛ፡ ስለ"ኢትዮጵያዊነት" ምንነትና ባሕርይ፡ በቀላሉ ለማስረዳት÷ ስለዕድገቱም አካኼድና የመጨረሻ ብቅዓት፡ በተጨባጭ ለማስገንዘብ፡ የማያፈናፍን ምስክርነት ያለው በመኾኑ ነው።

፪ኛ፡ "ኢትዮጵያዊነት" የቆመለትን እምነት የሚጻረሩ፡ አንዳንድ ባዕዳንና የአገር ተወላጆች፡ በዛሬው ዘመን÷ በቅርቡም፡ እስካለፈው ምዕት ዓመት ድረስ፡ በሕዝቡና በአገሪቱ ላይ ሊጭኑ ያቀዱትን፡ የእየራሳቸውን የገዢነት ቀንበርና የግል ጥቅም ፍላጎታቸውን ዓላማ፡ እውን ለማድረግ ሲሉ፡ ስለዚሁ፡ "ዐምሐራ" ስለሚለው አገር-አቀፍ የሕዝብ መጠሪያ ስም፡ ኾን ብለው የፈጠሩት፡ እጅግ የረቀቀ÷ የስሕተትና የቅራኔ ትርጓሜ ስላለ ነው። ስለዚህ፡ እዚህ ላይ የተለየ ትኵረት ተሰጥቶት፡ የቃሉን ምንጭና እውነተኛ ትርጉም በሚመለከት፡ በቂ ማስረጃዎችን ከማቅረብ ጋር፡ ስለቃሉ ዓቢይ ቁም ነገር፡ መተንተንና ማብራራት፡ ግዴታ ይኾናል።

"ዐምሐራ" የሚለው ቃል፡ መልእክትና ትርጉም ባለው ምክንያት፡ በኢትዮጵያ ምድር ለሚኖረው፡ ለአብዛኛው የአገሪቱ ነባር ሕዝብ የተሰጠ ትውፊታዊ ስያሜ ነው። ቃሉ፡ ከግእዝ ተገኝቷል። በግእዝ፡ "ዐም" ማለት፡ "ሕዝብ"÷ "ሐራ" ማለት ደግሞ፡ "ነጻ" ማለት ነው። ስለዚህ "ዐምሐራ" የሚለው ስያሜ፡ የቃል ለቃል ትርጉሙ፡ "ነጻ ሕዝብ" ማለት ሲኾን፡ ይኸው ትርጉም፡ የእውነተኛ ኢትዮጵያዊን ማንነት ከሚገልጹት ዓበይት ባሕርያት መካከል፡ አንዱ መኾኑን፡ በግልጽ ያመለክታል። ይህ ስያሜ፡ በአዳምና ሔዋን ልሳንነቱ፡ የነጻ ሕዝብነት መታወቂያ የኾነውን፡ "ግእዝ"ን፡ ቋንቋቸው አድርገው፡ ከዚያ በፊት ይኖሩ የነበሩት ኢትዮጵያውያን፡ ራሳቸውን፡ "አግዓዝያን" ብለው የሚጠሩበትን ስም እንደተካ ይታመናል።[፩፻፱]

የዐምሐራው ኅብረተሰብ፡ መነጋገሪያው ያደረገው ቋንቋ፡ "ዐምሐርኛ" ተብሏል። የዚህ ኅብረተሰብ፡ የቃል ብቻ ሳይኾን፡ የጽሕፈት መገናኛው ጭምር የኾነው፡ ይህ ልሳን፡ ግንዱ፡ ግእዝ ቢኾንም፡ በጋብቻና በልደት እንደተዋሐደውና የቋንቋው ባለቤት እንደኾነው ሕዝብ ኹሉ፡ ዐምሐርኛም፡ ብሔር-አቀፍ ኾኖ፡ በአገሪቱ ውስጥ በሚነገሩት፡ አያሌና የተለያዩ በኾኑ ልሳናት፡ ራሱን ሲያበለጽግ የኖረ ቋንቋ መኾኑ፡ የቃላቱ ቤተ መዛግብት ያረጋግጣል።

"ዐምሐራ" የሚለው ስም፡ ለምሳሌ፡ አገው፥ አርጎባ፥ አፋር፥ አሮሞ፥ ጉራጌ፥ ጋፋት፥ ሐዲያ፥ ወላይታ፥ ከምባታ፥ ኮናማ፥ ወይም ትግሬ እንደሚባሉት፡ በአየኅጣቸውና በአየክልላቸው፥ በአየእምነታቸውና በአየቋንቋቸው፡ ተለያይተውና ተወስነው፡ በአየስማቸው እንደሚታወቁት ብሔሮች፥ ወይም፡ ሴማውያን፥ ካማውያንና ያፌታውያን ተብለው፡ በመላዋ ምድር ላይ ተሠራጭተው እንደሚኖሩት፡ እንደሦስቱ የሰው ዘር፡ የትውልድ ቅርንጫፎች፡ ይህም ኅብረተሰብ፡ "አንድ ነጠላ ጐሣ ወይም ነገድ ነው" ተብሎ፡ ለእርሱ፡ መለያና መታወቂያ ይኾን ዘንድ የተሰጠ ስያሜ አይደለም።

በሌላ አገላለጽ፡ ዐምሐራ፡ የአንድ ጐሣ ወይም የአንድ ነገድ ወይም የአንድ ዘር ወገን አይደለም ማለት ነው። የቃሉ ፍቺ እንደሚያመለክተው፡ ዐምሐራ፡ በኢትዮጵያ ምድር የሠፈሩ፥ ከተለያዩ ጐሣዎች፥ ነገዶች፥ ዘሮች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎች እና/ወይም ሃይማኖቶች የተውጣጡ ወንዶችና ሴቶች፡ እርስ በርሳቸው በመጋባት፡ በሥጋ፡ አንድ የኾኑበት ህልውና ነው፤ በመንፈስም፡ ቀድሞ፡ በኪዳነ ልቦና፥ ቀጥሎ፡ በኪዳነ አሪት፥ በመጨረሻ፡ በኪዳነ ምሕረት፡ የክርስትና ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ከእግዚአብሔር በመወለድ፡ ሥጋቸውና ነፍሳቸው፥ እነርሱም፡ ኹላቸው፡ በአንዱ መንፈስ ቅዱስ፡ ፍጹም አንድ የኾኑበት ሕይወት ነው። በአጠቃላይ፡ "ኢትዮጵያዊነት" የተባለውን፡ ዘለዓለማዊ የህልውና ዓላማ፡ በሕያውነት ከግብ ለማድረስ፡ መለኮታዊዉን ጥሪ፡ በፈቃዳቸው ተቀብለው፡ ለእርሱ፡ በጋራ፡ ቃል ኪዳን የገቡና ለሰውም ኾነ ለዲያብሎስ ተገዢ ከመኾን ነጻ ወጥተው፡ በእግዚአብሔር ሕገ መንግሥት፡ በእኩልነት ፍትሕ በመመራት እየተዳደሩ፡ እንደአንድ ቤተሰብ የሚኖሩበት ሥርዓተ ሀገር ነው።

ዐምሐራው፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ እያንዳንዳቸው፡ የየግላቸውን ብሔረኝነትና ጐሠኝነት፥ አምልኮና ልሳን በፈቃዳቸው ትተው፡ ኢትዮጵያዊነትን፡ ከፍጹም ኹለንተናው ጋር፡ በፈቃዳቸውና በሃይማኖት የተቀበሉ፡ እኒያ፡ የኢትዮጵያ ጥንታውያን ባላገሮች ያቋቋሙት ኅብረተሰብ ስለኾነ፡ ቀጥሎ ባለው ሓተታ እንደሚብራራው፡ ይህ ኅብረተሰብ፡ እውነተኛው ኢትዮጵያዊ ኾኖ ለመገኘት በቅቷል።

እንግዲህ፡ ማንኛውም ግለሰብ፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነት ኦምኖ፡ የዚህ ኅብረተሰብ አባል ለመኾን፡ በፍጹም ነጻነት ፈቃደኛ ሲኾን፡ የሚፈጸምለት ሥርዓት አለ፤ ይኸውም፡ ከመንፈስ ቅዱስ በመወለድ፡ በእግዚአብሔር ሥንግሥት ውስጥ፡ ለአዲሱ ኪዳን ማኅበራዊ ሕይወት የሚያበቃውን ጸጋ የሚጎናጸፍበት ልዩ ሥርዓት ነው።

እርሱም፡ በሃይማኖት እውቀት፥ በእውነተኛ ንስሓ፥ በክርስትና ጥምቀትና በቅዱስ ቁርባን ምሥጢራት ይፈጸማል። ይህ ሥርዓት፡ ለዚያ ግለሰብ፡ እንደተፈጸመለት፡ ወዲያው፡ ያ ግለሰብ፡ "ዐምሐራ ኾነ!" ይባላል፤ "ክርስቲያን ኾነ!" ወይም "ኢትዮጵያዊ ኾነ!" ማለት ነው። <u>*"ዐምሐራነት"፡*</u> ኋላ፡ በሥጋ ጋብቻ ጭምር እስኪዋሃዱበት ድረስ፡ <u>*በቅድሚያ፡ እንዲህ በመንፈስ የሚወለዱበት ስለኾነ፡ ጌታ ወይም ብሔር አለመኾኑ፡ በዚህ ይታወቃል።*</u>

በዚህ ጊዜ፡ ያ ግለሰብ፡ ኢትዮጵያዊነት፡ በሚያስተማምን ቃል ኪዳን፡ ለዘለዓለም የሚያጐናጽፈውን፡ ያን፡ በመለኮታዊ ጸጋ የተገኘውን ሰብአዊ ማዕርግ እንዳይቀዳጅ፡ ከልክሎት ከኖረው፡ ከጠባብ ብሔረኝነትና ከጐሠኝነት፡ ከቋንቋና ከእምልኮ ባዕድ ቁራኝነት፥ ከአንጉል አስተሳሰብም ቀንበር ተላቅቆ፡ የእውቀት ብርሃን የወጣለትና የነጻነትን አክሊል የተቀዳጀው ጎብረተሰብ አባል ለመኾን የበቃ ይኾናል።

ይህ "ዐምሐራ" የመኾን ምሥጢር፡ "ኢትዮጵያዊ" ከመኾን ጋር የሚመሳሰልና እንደ"ኢትዮጵያዊነት" ዅሉ፡ ያልተቋረጠ ትንግርታዊ ሂደት ያለው ኾኖ ኖርዋል። "ዐምሐራ ኾነ" ማለት፡ ከላይ እንደተወሳው፡ "ኢትዮጵያዊ ኾነ" እንደማለት ብቻ ሳይኾን፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በፍጥረተ ዓለሙ ዘንድ፡ በይበልጥ እውቅና እንዳገኘውና በመጨረሻው ዘመን፡ የሰውን ዘር እንደገና አዋሀዶ፡ ፍጹም አንድ እንደሚያደርገው፡ እንደአዲስ ኪዳኑ ስያሜ፡ "ክርስቲያን ኾነ" ማለትም ነው። በዚህ መሠረት፡ ዐይነተኛው (ማለት አማናዊው ወይም እውነተኛው) ዐምሐራ፡ ዐይነተኛው ኢትዮጵያዊ ወይም ዐይነተኛው ክርስቲያን ነው፤ ዐይነተኛው ኢትዮጵያዊ ወይም ዐይነተኛው ክርስቲያንም፡ ዐይነተኛው ዐምሐራ ነው። እንዲህ ከኾነ፡ እነዚህ ሦስት ስያሜዎች፡ ማለትም፡ ዐምሐራነት፥ ኢትዮጵያዊነት እና ክርስቲያንነት፡ በምሥጢርና በትርጓሜ ይዘታቸው፡ አንዱ ሌላውን ሊተካ የሚችል፡ የተመሳሳይነትና የተወራራሽነት ባሕርይ ያላቸው ቃላት መኾናቸው፡ በግልጽ ይረጋገጣል።

ለዛሬው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ የዘር ግንድ የኾነው፡ የጥንቱ የዐምሐራ ጎብረተሰብ፡ የኢትዮጵያ ነባር ባላገሮች ከኾኑት፡ ጎዳጣን (ቁጥራቸው አናሳ የኾነ) እና ብዙኃን (ቁጥራቸው በርካታ የኾነ) ብሔረሰቦች ተውጣጥቶና ተዋሕዶ የተገኘ መኾኑ፡ ከላይ ተመልክቷል። የዚያ ጥንታዊ ጎብረተሰብ አባሎች የኾኑት፡ እንያ አባቶችና እናቶች፡ ለቅዱሱ ኪዳን አምላክ፡ ለልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ፡ ራሳቸውን፡ በሃይማኖት በማስገዛት፡ ዘለዓለማዊዉን በረከትና ጸጋ፡ ለልጅ ልጆቻቸው እንደሚያቀዳጅ የተማመኑበትን፡ የኢትዮጵያዊነትን መሠረት፡ በበለጠ አጽንተው ለመቀጠል፡ በስምምነት የሰጡት ውሳኔና ውሳኔውን በሥራ ላይ በማዋል፡ የፈጸሙት ገድል፡ ለዚህ ግዳጃቸው ከከፈሉት መሥዋዕትነት ጋር፡ እጅግ ብልሆች፥ አርቆ አስተዋዮችና ቆራጦች ለመኾናቸው በቂ ማስረጃ ኾኗቸዋል።

አዎን! የዐምሐራው ኅብረተሰብ: ከአዳምና ሔዋን ተንሥቶ፥ በወንድሙ በቃየል የተገደለው: የልጃቸው የአቤል ምትክ በኾነው: በእሴት፥ ከዚያ: በኖኅና በልጆቹ: በሴም÷ በካምና በያፌት ነገዶች ውሕደት በተገኘው በመልከ ጼዴቅ አማካይነት ሲወርድ ሲዋረድ የቀጠለው: የቅዱሱ ኪዳን ዘር እንደመኾኑ: የዚህ ኅብረተሰብ ጥንታውያን አባቶችና እናቶች: በሥጋ ለመለዩቸው: ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው: በመንፈስ ቅዱስ: የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ክብር: በውርስ እንዲረከቡ በማድረግ: በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም: ከፍጹምነት ለደረሰው: ለቅዱሱ ኪዳን ሕዝብነት አብቅተዋቸዋል::

እስኪ ዛሬ: የትኛው ኢትዮጵያዊ ነው÷ ወይም: ከላይ በጥቂቱ በተወሱትና ከእየራሳቸው ጠባብ ብሔረኝነት ጋር ተቆራኝተው በሚገኙት ጉሣዎች ውስጥ አባል ከኾነው ግለሰብ መካከል እንኳ ሳይቀር: የትኛው ነው: እንኳንስ: ከአንድ ነጠላ ጉሣ ይቅርና: "ከኹለት ወይም ከሦስት ጉሣዎች ብቻ የተወለድኩ ነኝ" በማለት: በሙሉ አፉ ደፍሮ ሊናገር የሚችል? ማንም ሊኖር ከቶ አይችልም:: ምክንያቱም: ያ ኢትዮጵያዊ ወይም የጉሣ አባል: ወንድ ኾነ ሴት: በወላጆቹ የትውልድ ግንድ በኩል: በጥቂቱ ወደኋላ ኼድ ብሎ: የአያቶቹን÷ የቅድማያቶቹንና የምዝላቶቹን የዘር ሐረግ ቢሰብ: ራሱን: የኅብረብሔር ፍሬ: ማለት: አያሌ ጉሣዎች የተዋሐዱበት ቅይጥ ፍጡር ኾኖ ያገኘዋል:: "ዐምሐራ" ወይም "ኢትዮጵያዊ": ከሚያሰኙት ዓበይት ባሕርያት መካከል ደግሞ: ይህ: የኅብረብሔር ፍሬነት: አንዱ: ዓይነተኛው ባሕርይ መኾኑን: በትኵረት መመልከት ነው::

የዚህ እውነታ አማናዊነትና እርግጠኛነት: ባሁኑ ጊዜ: በኢትዮጵያ ምድር÷ እንዲሁም: በአገር ውስጥ በሚኖሩትና በውጭ አህጉር ተበትነው በሚገኙት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ ሰፍኖ ባለው ኹኔታ: ጎልቶና ገዝፎ ይታያል:: ይኸውም: ዓይነተኛው (እውነተኛው) የዐምሐራው ኅብረተሰብ: ኢትዮጵያ: በእግዚአብሔር መንግሥትነት ሥር ተዋሕዳ የኖረች: የማትከፋፈል: አንዲት አካል መኾኗን በማመን: በጉሣ ወይም በዘር መለያየትን የሚቃወም በመኾኑ ነው::

እንዲያውም: ኢትዮጵያዊነት: ከዚህ የበለጠ: የመጠቀና የጠለቀ÷ የሰፋም ባሕርይ አለው፤ ይኸውም: ለኢትዮጵያ÷ እንዲሁም: ላለፉትና ለዛሬዎቹ÷ ለወደፊቶቹም ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብቻ ተለይቶና ተወስኖ የተሰጠ÷ እየተሰጠ ያለና የሚሰጥም አለመኾኑ ነው፤ ነገር ግን: በዘመነ ሐዲስ ኪዳን: ሞክሼው (መሰሉ) እንደኾነው: እንደክርስቲያንነት ኹሉ: የሰው ዘር በመላ ተጠቃልሉና በመለኮታዊው መንግሥት ሥር ተዋሕዶ: አንድ እንዲኾንበት: እግዚአብሔር አምላክ: ለፍጥረተ ዓለሙ ደህንነትና መልካም ሕይወት: አዘጋጅቶ የዘረጋው ዘለዓለማዊ ዕቅድ ነው እንጂ:: ይህም: በምድር ላይ ላለው: ለሰው ልጆች ኾነ ብሎ: የመጨረሻው መፍትሔ እንደሚኾን ይታመናል::

ምዕራፍ ፮፡
"ኢትዮጵያዊነት" ተከሥቶበት የኖረው፡ ስምና ህልውና።

ከዚህ የተነሣ፡ ባንድ ወገን፡ "መላው ዐማራ" በሚል ስያሜ የተቋቋመው ድርጅት፡ በውስጡ፡ "ዐማራ" ከሚያሰኘው፡ ከቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ውጪ የኾኑትን ግለሰቦች ጭምር፡ በአባልነት አጠቃልሎ እንዲይዝ በማድረግ፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በአገር-አቀፍ ደረጃ፡ "የዐማራው ክልል" በሚል ዕቅድ፡ የተጀመረውን የመከፋፈል ዓላማ ከግብ ለማድረስ በመሞከር፡ የሚፈጸመው ድርጊት፡ በእየመልኩ ሊወገዝ ይገባዋል። ምክንያቱም፡ ይህ፡ በኹለቱም ወገኖች የሚፈጸመው ድርጊት፡ ዐምሐራን፡ ከመሠረታዊው፡ የኢትዮጵያዊነት ባሕርዩ አውጥተው፡ እንደጎሣ ለማስቈጠር፡ የኢትዮጵያ የደም ጠላቶች በሚያውጠነጥኑት ሴራና በሚያካኺዱት ዘመቻ ውስጥ ተባባሪ፡ ደጋፊና መሣሪያ መኾንን፡ በግልጽ አረጋግጦ የሚያሳይ፡ የክህደትና የዓመፅ ተግባር በመኾኑ ነው።

ስለዚህ፡ "ዐምሐራ"፡ ኢትዮጵያዊነትን ሕያው ለማድረግ፥ ለመጠበቅና ለማስፋፋት፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱ፡ ቃል ኪዳን የገባ ኢትዮጵያዊ ማለት ስለኾነ፡ ከላይ የተመለከተውን፡ በድርጅቱም ኾነ በብሔራዊው ደረጃ የሚታየውን የተዛባ አሠራር፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ኹሉ፡ በብርቱ አስበውበት፡ ራሳቸውን፡ በንስሓ፥ ድርጊታቸውንም፡ በእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ማስተካከልና ማብቃት ይኖርባቸዋል።

ኢትዮጵያውያን፡ ከጥንት ጀምረው፡ በሥጋ ዘር ብቻ ሳይኾን፡ በነፍስና በመንፈስም፡ ፍጹም አንድ ኾነው፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን፡ ለዘለዓለም ጠብቀው ለመኖር የቻሉት፡ ተስማምተው በተቀበሏቸው፡ ከእግዚአብሔር እውነት በመነጩት፡ የውሕደት ኃይላት መኾኑን፡ እስካኹን እንደተገነዘባችሁት አምናለሁ፤ እነዚህም፡ ጀቱን ኪዳናት የያዘውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖትና አምልኮን፥ ሥርዓተ መንግሥትንና "ኢትዮጵያ" የሚለውን፡ መጠሪያ ስም፥ ለንደቅ ዓላማንና ማኅተምን የመሰሉት ናቸው፤ ከእነዚህ ጋር፡ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍም መኖራቸውን ልታውቁ ይገባችኋል። "ቋንቋ" ስንል፡ ግእዝና ከእርሱ ሠርፆ የተቀነባበረው፡ "ኢትዮጵያኛ" የምንለው፡ ዐምሐርኛ ሲኾኑ፥ "ሥነ ጽሑፍ" ደግሞ፡ የ"አበገደ"ን ሆሀያት መሠረት ያደረገው፡ ኢትዮጵያዊው ፊደልና ሰዋስዉ ናቸው። እነዚህ ኹሉ፡ በውይይታችን፡ ሦስተኛ ክፍል፡ በስፋት ተተንትነው ታገኟቸዋላችሁ።

ኪዳነ ልቦናና ቤተ ሕዝብነት።

ጥያቄ፡- እንግዲህ፡ "ዐምሐራ"፡ ወይም፡ "ክርስቲያን"፡ የሚለው "ማንነት"፡ በ"ኢትዮጵያዊነት" እንደተጠቃለለ፡ እነሆ ተረዳን። በዚህም፡ ያን፡ "እኔ" የምንለውን ማንነታችንን፡ እንዲህ ባለ መልክ፡ በትክክልና በግልጽ ልናውቅ ከቻልንበት ደረጃ ደረስን ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ፡ አኹን፡ በእየውስጣችን እየተሰማን ያለው አስተሳሰብና ግምት፡ በእርግጥ፡ ቀድሞ ከነበረን፡ እጅግ የላቀና የተለየ፥ የመጠቀና የጠለቀ ብሩህ ኾኖ አግኝተነዋል። ታዲያ፡ በዚህ ምንነታችንና ማንነታችን፡ ምን መኾን፥ ምንስ ማድረግ እንደሚጠበቅብን፡ ልትነግረን ትፈቅዳለህን?

መልስ፡- እንግዲህማ፡ "ምንነታችሁንና ማንነታችሁን በማወቃችሁ፡ ምን መኾን እንደሚገባችሁ፡ ይኸው፡ በሚበቃ ተረዳችሁ። ከእግዚአብሔር የተፈጠረችው፡ ረቂቋ ነፍሳችሁ፡ ሥጋን በመልበሷ፡ ምድራዊ ግዘፈትንና ጊዜያዊ ኑሮን እንደማግኘቷ፥ በክርስትና ጥምቀት፡ ከእግዚአብሔር በመወለዷም፡ የነፍስና የሥጋ አካላትን አስማምቶ ባዋሃዳቸው፡ በመንፈሳዊው አካል ምክንያት፡ ለማያዊ ጸጋንና ዘለዓለማዊ ሕይወትን ተጐናጽፋለች።

በፈጣሪያችሁ ጥበብና ቸርነት፡ እንዲህ ኾናችሁ የተሠራችሁት፡ በዚህ ማንነታችሁ፡ <u>*የእግዚአብሔር የኪዳን ልቦናው፡ ማደሪያ፥ የኪዳን አሪቱ፡ ጽላትና የኪዳን ምሕረቱ፡ ቤተ መቅደስ እንድትኾኑ ነው።*</u> በእርሱ ዘንድ፡ ዐምሓራኒታችሁ፡ ወይም፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ የተዋሕዶ ክርስቲያንነታችሁ፥ ወይም ኢትዮጵያዊነታችሁ፡ በእውነት እንጂ፡ በማስመሰል እንዳይኾን፡ ልትጠነቀቁ ይገባል።

የእግዚአብሔር ወልድ አርአያ በኾነው፡ በመጀመሪያው መልክ ጼዴቅ ተገልጾ፡ በመጨረሻውና በአማናዊው መልክ ጼዴቅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመው ቃል ኪዳን፡ ከነፍሳችሁና ከሥጋችሁ፥ ከመንፈሳችሁም ውሕደት የተነሣ፡ አካላዊ ህልውናን ያገኘውን፡ ይህን ኢትዮጵያዊ እኔነታችሁን፡ ከእግዚአብሔር ለተሰጡት፡ የሕዝብነት፥ የምሉክነትና የክህነት ጸጋዎች አብቅቶላችኋል። ይህም፡ ከእግዚአብሔር ለተገኙት፡ ለነፍሳዊው የዘለዓለም ልጅነት፡ ለሥጋዊውና ለመንፈሳዊውም፡ የሕዝብ አገልጋይነት አብቅቶላችኋል ማለት ነው።

በዚህ መሠረት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው፡ ኢትዮጵያ ሥር ባለው፡ በእንዱ፡ የአቋሟ ግንድና ከዚያ በሠረፁት፡ በኹለቱ ቅርንጫፎች ውስጥ፡ በነፍሳዊነታችሁና በሕዝባዊነታችሁ፡ እያንዳንዳችሁ፡ የቤተ ሕዝቡ አባሎች ናችሁ፤ እንደተፈጥሮ ስጦታችሁና ሙያችሁ ደግሞ፡ ወይ፡ በሥጋዊነታችሁና በመለካዊነታችሁ፡ ለቤተ ምልክናው፥ ወይም፡ በመንፈሳዊነታችሁና በካህንነታችሁ፡ የየጸታችሁ መደብ ተጠብቆ፡ ለቤተ ክህነቱ ተመራጭና ተሠያሚ ለመኾን ብቁዎች ናችሁ። ይህን፡ የሥራና የአስተዳደር ሥርዓት በመከተል፡ በእየራሳችሁ ፍላጎትና በወገኖቻችሁ መራጭነት፡ በእግዚአብሔር ፈቃድና ሠያሚነትም፡ በቤተ ሕዝቡ፡ ወይም በቤተ ክህነቱ፡ ወይም በቤተ ምልክናው ውስጥ፡ አገልግሎታችሁን ታበረክታላችሁ።

እንግዲህ፡ የኹሉም መሠረት፡ አንድ እግዚአብሔር ኾኖ፡ ለኪዳነ አራትና ለኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ መነሻው፥ ምንጩና ግንዱ፡ ኪዳነ ልቦና እንደመኾኑ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው መነሻ፥ ምንጩና ግንዱ ደግሞ፡ ቤተ ሕዝቡ እንደመኾኑ፥ ነፍስም፡ "እኔ" የሚለው የእኔነት መነሻና ምንጩ፥ ግንዱም ናት። ራሷ ነፍስ፡ "እኔ" ናት ማለት ነው።

\+ + +

ምዕራፍ ፭

ጸም፡- አምን! ስለጸም።

ጥያቄ፡- ለዚህ ልዕልና የበቃውን፡ ይህን፡ የ"እኔነት" ኹለንተናችንን፡ ታዲያ፡ እንዴት አድርገን ነው፡ አንጽተንና አጽንተን ልንጠብቀው፥ በጤናማ ሀልውናውም እንዲቀጥል ልናደርገው የምንችለው?

መልስ፡- በነፍስና በሥጋ፡ በመንፈስም፡ እንዲህ፡ ተቀናጅቶና ተዋሕዶ፡ ተሟልቶና ተስተካክሎ የተመሠረተውን፥ ጸንቶ የቆመውንና ተከናውኖ የተደመደመውን፡ ይህን ኹለንተናችንንና ሀልውናችንን፡ እንጠብቅበት ዘንድ፡ ከፈጣሪያችን የተሰጠን፡ ረቂቅና ፍቱን የኾነ፡ የድል መሣሪያ አለ። እርሱም፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ በግሉ፡ የሥጋና የነፍስ ጤንነቱንና ዕድሜውን፡ በጠቅላላም፡ ሕይወቱን የሚጠብቅበትና የሚንከባከብበት መሣሪያ፡ የሚያጠራበትና የሚከላከልበት ኃይል ነው፤ መንፈሳዊ "የጦር ትጥቅ" ማለት ነው። የሰውን ዘር፡ ወደተሻለ የሕይወት ደረጃ፡ ከፍ አድርገው ለማሻገር፡ በዘመናት መካከል፡ አልፎ አልፎ የተነሡና ድንቅ የለውጥ ድርጊቶችን የፈጸሙ፡ የተመረጡ ጥቂት ሰዎች፡ ይህን መንፈሳዊ ትጥቅ ተጠቅመውበታል። እርሱም፡ "ጸም" ይባላል፡ ይህ ሥርዓት፡ ከእግዚአብሔር ካገኘናቸው፡ ከሦስቱ አርእስተ ምግባራት አንዱ፡ የመጀመሪያው ሲኾን፡ የቀሩት ኹለቱ ደግሞ፡ "ጸሎት" እና "ምጽዋት" ይባላሉ። ስለእነዚህ፡ ልለቀሩት፡ ኹለት ተከታታይ ምግባራት፡ በሚቀጥሉት፡ ኹለት የመጽሐፉ ዋና ዋና ክፍሎች ውስጥ ለያይተን እንነጋገርባቸዋለን።

እንግዲህ፡ "እናንተ፡ ለዚህ ልዕልና የበቃችሁበትን፡ የእኔነታችሁን ኹለንተና፡ አንጽታችኹና አጽንታችሁ ልትጠብቁት፡ በጤናማ ሀልውናውም፡ እንዲቀጥል ልታደርጉት የምትችሉበት ፍቱን መሣሪያና ረቂቅ ኃይል፡ 'ጸም' የሚባለው ምግባርና ሥርዓት ነው።" ብዬ መልሱን፡ በአጭር ቃል አጠቃልልላችኋለሁ።

ጥያቄ፡- እንግዲያ፡ የእኔነታችንን ኹለንተና ለመጠበቅ፡ ስለሚያስፈልገን፡ "ጸም" ስለሚባለው፡ ስለዚህ ፍቱን መሣሪያና ረቂቅ ኃይል፡ እስኪ፡ እባክህ፡ በሚበቃ አስረዳን?

መልስ፡- ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ "ጸም"፡ አንድ ግለሰብ፡ የራሱን ምንነትና የፈጣሪውን ማንነት የሚያውቅበት መንገድ ከመኾኑ ጋር፡ ነፍስ፡ ከፋ፡ የኾነውን እንዳታስብ፥ ሥጋ፡ ከፋ የኾነውን እንዳያደርግና መንፈስ፡ ክፋ በኾነው እንዳይበከል፡ አንድ ሰብአዊ ፍጡር፡ ኹለንተናውን የሚጠብቅበትና የሚከላከልበት መንፈሳዊ መሣሪያና ኃይል ነው። ቃሉ፡ ከግእዝ የተገኘ ሲኾን፡ "ጸዊም" የሚለው፡ ጥሬ ዘሩ፡ "ሰውነትን፡ ከሚጎዳ መብልና መጠጥ፥ ከሌላውም ክፋ ነገር ኹሉ መከልከልና መጠበቅ" ተብሎ ይተረጐማል።

ይህም ሲዘረዘር: የሰውነትን አባላት: በተናጠል÷ ሦስቱንም አካላት: በድምር÷ በጠቅላላ: ነፍስን÷ ሥጋንና መንፈስን የያዘውን መላ ኹለንተናን: በአሳብም ኾነ: በንግግር÷ ወይም: በተግባር: ማለትም: በምልክት÷ በጽሑፍ÷ በሥዕልና በቅርፅ÷ ወይም በማናቸውም ዓይነት ድርጊት ከሚያሳድፉና ከሚጎዱ÷ እንደዚሁም: ራስን: ከተፈጥሮ ሥርዓትና ቁጥጥር ውጭ ከሚያደርጉ÷ ለክፉት አሳብም ምንጭ ከኾኑ: ከሚበሉና ከሚጠጡ÷ ከሚቃመሩና ከሚጎረሱ÷ ከሚታኘኩና ከሚዋጡ÷ ከሚቀመሱና ከሚተነፈሱ÷ ከሚጤሱና ከሚሸተቱ÷ ከሚነኩና ከሚዳሰሱ÷ ከሚታዩና ከሚገለጡ÷ ከሚሰሙና ከሚደመጡ÷ ከሚጠለቁና ከሚለበሱ÷ ከሚነገሩና ከሚጻፉ÷ ከሚሣሉና ከሚቀረጹ÷ ከመሳሰሉ ነገሮች ኹሉ: ራስን መከልከልና መለየት ማለት ይኾናል:: የጾም: ሌላ ስሙ: "ትሕርምት" የሚባለው: ለዚህ ነው: "ትሕርምት" የሚለው የግእዝ ቃል: "የሚጎዳውን ክፉ ነገር: 'ዕርም!' ብሎ መተው÷ ወይም: "ራስን: ከሚጎዳ ክፉ ነገር 'ማረም"" ማለት ስለኾነ: የጾምና የትሕርምት ቃላትና ትርጉማቸው ተወራራሽ መኾኑ በዚህ ይታወቃል::

"ጾም": በመጀመሪያ ነገር: ከጸሎትና ከምጽዋት ጋር: የሃይማኖት መገለጫ እንጂ: ራሱ: ሃይማኖት አይደለም: በሃይማኖትና በምግባር ለመጽናት÷ በሥጋና በነፍስም: የጤና ዕድሜ ለማግኘት የሚጠቅም ረቂቅ ኃይል ነው:: "ጸሎት": ሰው: ከፈጣሪው ጋር በመንፈስ የሚገናኝበት÷ "ምጽዋት": ባልንጀራውን: እንደራሱ መውደዱን የሚገልጽበት ምግባር ሲኾን: "ጾም" ግን: ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ: ሰው: ራሱን የሚመረምርበት: የሚቆጣጠርበትና የሚጠብቅበት ፍቱንና ኃይለኛ መሣሪያ ነው:: "ሃይማኖት": እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር: በግል ፈቃዱ ተቀብሎ: የሚያምንበትና የሚሠራበት እንደመኾኑ: "ጾም"ንም: በዚሁ መልክ: በግል ፈቃደኛነት ተቀብሎ: ዓቅሙ በሚችለው መጠን: በተገቢው ጊዜና ቦታ: ነፍስንና ሥጋን ከሚጎዱ ነገሮችና ግብሮች: ራሱን በመለየት: የሚፈጽመው: የመንፈስ ምግባር ነው::

ጥያቄ:- *"ጾም" እንዲህ: በግል የሚፈጸም ምግባር ከኾነ: ታዲያ: በመታሰቢያነትና በማኅበር የምንጠማቸው አጽዋማት አጠባበቅና አደራረግ: እንዴት ሊካሄድ ነው? ይህን ነገር: ከዚሁ ርእስ ጋር አያይዘህ ብታብራራልን!*

መልስ:- በመታሰቢያነትና በማኅበር ስለምንጠማቸው አጽዋማት: በዚሁ ርእስ ሥር: የሚሰጡትን ሓተታዎች: ወደፊት: በቦታቸው ታገኟቸዋላችሁ:: በመሠረቱ ግን: "ጾም": በግልም ኾነ: በማኅበር÷ ወይም ለመታሰቢያነትና በየትኛውም ኹኔታ የሚጠም ቢኾን: ባሕርዩ÷ ዓላማውና አፈጻጸሙ: ቀደም ብሎ እንደተገለጸው: ያው: አንድ ብቻ ነው:: ከዚያ የተለየ መልክና ግብር የለውም:: ይኸውም: <u>ከራስ ፈቃደኛነት መንጭቶ÷ በራስ ተካኺዶ÷ ለራስ የሚፈጸም ምግባር መኾኑ: ሊታወቅ ይገባል::</u>

ጥያቄ፦ *እንዲያ ከሾነ፡ ይህንኑ፡ የ"ጸም"ን ግላዊነት ሓተታ፡ እንደጀመርክ ቀጥልልና!*

መልስ፦ መልካም! ለጸም እውነተኛ ምንነት፡ መሠረቱም፡ ግድግዳውም፡ ገላላቱም የሾነውን አምላካዊ ቃል፡ በቅድሚያ ልጥቀስላችሁ! ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ፡ በመንፈስ፡ ወደምድረ በዳ ተወሰደ፤ አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ጦሙ ተራበ። ፈታኝም ቀርቦ፡ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሾንህ፡ 'እነዚህን ድንጋዮች፡ እንጀራ ይሹ!' በል!" አለው። እርሱም መልሶ፡ "'ሰው፡ ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሹሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም፤' ተብሎ ተጽፎአል" አለው።"* የሚለውን ቃል፡ እርሱ ራሱ ከፈጸመ በኋላ፡ ለተከተሉት ደቀ መዛሙርቱ (ተማሪዎቹ)፡ እናንተ *"ስትጸሙ፡ እንደግብዞች አትጠውልጉ! በሰዎች ዘንድ፡ እንደጠመኛ ሊታዩ፡ እነርሱ ፊታቸውን ያጠፋሉና፤ በዚህም፡ እውነት እላችኋለሁ፡ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጦም፡ በሥውር ሳለው አባትህ እንጂ፡ እንደጠመኛ ለሰዎች እንዳትታይ፡ ፊትህን ታጠብ! ራስህንም ተቀባ! በሥውር የሚያይ አባትህ፡ በግልጥ ያስረክብሃል።"* እያለ ያስተማራቸው ትምህርትና የሰጣቸው መመሪያ ነው። ደግሞም፡ *"ለሚጠፋ መብል አትሥሩ! ነገር ግን፡ ለዘለዓለም ሕይወት ለሚኖር፡ የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ መብል ሥሩ! ...ሕይወትን የሚሰጥ፡ መንፈስ ነው፤ ሥጋ፡ ምንም አይጠቅምም። እኔ የነገርኋችሁ ቃል፡ መንፈስ ነው።"* [ዮሐ] የሚለውንና ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን የመሪያቸውን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል በመከተል፡ የቅዱሱ ኪዳን ልጆች የሾኑት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ጸምን፡ ሃይማኖታዊ ባህላቸውና ሕይወታቸው አድርገውት ኖረዋል። በዚህ ዓለም የሚኖሩትም፡ በሥጋዊው መብል ብቻ ሳይሾን፡ በይበልጥ፡ በመንፈሳዊው ጸም መሾኑን፡ በዓመቱ ውስጥ የሚጾሟቸው፡ ከዚህ በኋላ፡ በዕድሜ ሳይ ፡ስንደርስ የምዘረዝርላችሁ፡ የአጽዋማት ብዛትና መጠን ያስረዳሉ።።

ይህንኑ አምላካዊ ቃል መሠረት በማድረግ፡ ቀደም ብዬ፡ "ጸም"፡ ግላዊ ምግባር መሾኑን ገልጬላችኋለሁ። እንዲህ እንደመሾኑ፡ እውነተኛ በሾነ፡ በማናቸውም ሃይማኖታዊ ምእመን የግል ሕይወት ላይ የሚያስከትለውን ተለምራዊ ለውጥ፡ በሰባት ፍሬዎች መድቤና አጠቃልዬ አቅርቤላችኋለሁና፡ በማስተዋል ተመልከታችሁ፡ በግብር ላይ ብታውሉት ይጠቅማችኋል።።

የጸም ኃይሉና ጥቅሙ።።

ጥያቄ፦ *"ጸም"፡ እውነተኛ በሾነ፡ ሃይማኖታዊ ምእመን የግል ሕይወት ላይ የሚያስከትለውን ተለምራዊ ለውጥ የሚያሳዩት ሰባት ፍሬዎች፡ ምንና ምን እንደሾኑ ማወቅ፡ ለእኛ፡ በእርግጥ ይጠቅመናል፤ በተለይ፡ በእሹት ዘመናችንና ዕድሚያችን፡ በጣም ያስፈልገናልና፡ ልንሰማው እንጓጓለን።።*

መልስ፡- ሠልካሃ! እነዚህ፡ ሰባት የጸም ፍሬዎች፡ ያ፡ ምእመን፡ በተፈጥሮው ወርሷቸው፡ በሰውነቱ ውስጥ የሚገኙትን፡ ኹለት ተጻራሪ (እርስ በርሳቸው የሚቀዋወሙ) ፍላጎቶች፡ ማለትም፡ የነፍስና የሥጋ ፈቃዳትን፡ በጥምቀት ከተወለደበት፡ ከክርስትና ልጅነቱ ለሚሠርፀው፡ ለመንፈስ ቅዱሳዊው ፈቃድ በማስገዛት፡ በዚህ ዓለም ህልውናው፡ ፍጹም ሰላምንና ጸጥታን÷ ደስታንና ዕረፍትን የሚያገኝባቸው በረከቶች ናቸው፡ እነርሱም ሲዘረዘሩ፡-

ፅኛው፡- ከእግዚአብሔር በቀር፡ ለማንም ወይም ለምንም፡ የበላይ ኃይል፡ ባርያ÷ ተገዥ ወይም አገልጋይ አለመኾኑን የሚያረጋግጥበት፡

፪ኛው፡- በውስጡ ያሉትን፡ የክፉው ወገን የኾኑትን የኃጢአት ጠንቆች አዳክሞ፡ የበጎው ወገን የኾኑትን ጸጋዎች የሚያሰፍንበት÷

፫ኛው፡- ማናቸውንም ዓይነት፡ የነፍስ ፈተናና የሥጋ መከራ ተቋቁሞ የሚያሸንፍበት÷

፬ኛው፡- ሃይማኖቱንና ምግባሩን የሚያጠናክርበት፡ ፣

፭ኛው፡- የፍጹም ትእግሥትና ተስፋ ባለቤት ለመኾን የሚበቃበት፡

፮ኛው፡- ከመጨረሻው መሥዋዕትነትና ሰማዕትነት ደረጃ የሚደርስበት፡

፯ኛው፡- የሥጋና የነፍስ አካላቱን፡ ኹለቱንም፡ በእውነተኛው ጤንነት የሚጠብቅበት ኾነው ይከሠታሉ።

ጥያቄ፡- *ይህን የመሰለውን ከሥተት፡ ማለትም፡ "ጸም"፡ ይህን ኹሉ በረከት ለማስገኘት ስለሚችልበት ምሥጢር፡ መቼም፡ በሚበቃ ሓተታ፡ ሳታብራራልን እንደማታልፍ እርግጠኞች ነን።*

መልስ፡- እንኳንስ፡ ፍላጎቱ እንዳላችሁ፡ እንዲህ ገልጣችሁልኝ ይቅርና፡ ያም ባይኾን፡ ማብራራቱ፡ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ መኾኑ፡ አሌ አይባልም።። የማብራራላችሁም፡ እውነተኛ ጸሚ የኾነ፡ አንድን ግለሰብ፡ በምላሌነት በማቅረብ ነው፣ ይህ ሰው፡ እነዚህን ሰባት የጸም በረከቶች፡ ማለትም፡ ከጸሙ ምግባር፡ ሰባት ጥቅሞችን ማግኘት እንዴት እንደቻለ÷ ወይም፡ እንደሚችል÷ ወይም፡ የሚችልበትን ኹኔታ፡ በእርሱ ምግባር አማካይነት እንመለከታለን።

፩ኛ፡- ይህ ግለሰብ፡ ሰውነቱን ሊጎዳ የሚችል፡ አንድ ዓይነት የተለየ ምግብ፡ ወይም መጠጥ፡ በጣም ያምረዋል፣ ወይም፡ ዝሙትን የመሰለ፡ የፍትወተ ሥጋ ጦር ይነሣበታል፣ ወይም፡ "ሌላው ሰው፡ በጥቅሜ ላይ ተጻራሪ ወይም እንቅፋት ኾኖ ቀርቦብኛል፣" በማለት፡ ስለጥቅሙ ሲል÷ ወይም፡ እንዲያው ዝም ብሎ፡ በቅንዓት ብቻ፣ ወይም፡ በምቀኝነት ብቻ፡ ወይም፡ በጥላቻ ብቻ፡ በዚያ፡ በሌላው ሰው ላይ፡ በነገር ኾነ በግብር፡ ከሕግ ውጭ የኾነ አንድ ዓይነት ድርጊትን፡ በግልጽ ኾነ በሥውር ለመፈጸም÷ ወይም፡ ሊያደርግ የማይፈልገውን፡ ክፉ ሥራ እንዲፈጽም፡ አሳቡ፡ በክፋት መንፈስ፡ በግለት ይነሣሣል።

በእነዚህ ጊዜያት፡ ይህ ግለሰብ፡ ራሱን፡ በጸም፡ በእውነት ያነጸ ከሆነ፡ ሰውነቱን፡ አስቀድሞ፡ በሥርዓት ቀጥቶ፡ አሠልጥኖታልና፡ እነዚያን፡ የክፋትና የሕገወጥ ድርጊቶች አሳቦች ኹሉ፡ "አላደርግም!" ብሎ፡ በቁርጥ መወሰንና ከመፈጸም መታቀብ ይችላል። በዚህም፡ የራሱን፡ ማለትም፡ የነፍስና የሥጋ ፍላጎቱን፡ ወይም ሰብአዊ ፈቃዱን፡ ለመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ማስገዛቱን ያረጋግጣል። በጸም ምግባር የታነጸ ካልኾነ ግን፡ በቀጥታ፡ የማናቸውም ዓይነት ክፉ ፍላጎትና ፈቃድ ተገዥ ኾኖ፡ ያንን ክፉ ፍላጎትና ፈቃድ፡ እንደእንስሳ፡ ወይም እንደሰው ሠራሹ መኪና ተነድቶ፡ ወይም፡ መድኃኒት እንዳቀመሱትና "ሊባ ሻይ (ፈልጎ የሚያገኝ) " ይባል እንደነበረው አብሷም ተመርቶ፡ ከመፈጸም ወደኋላ አይልም፡ በራሱም ኾነ፡ በሌላው ላይ፡ ጥፋትንና ጉዳትን ለሚያስከትል ክፉ ፍላጎትና ፈቃድ ምርኮኛ ይኾናል ማለት ነው።

፪ኛ፡ ይኸው እውነተኛ ጸሚ ሰው፡ ራሱን፡ በፈቃዱ፡ ረዛብተኛና ተጠሚ፡ ችግረኛና መከረኛ ስላደረገ፡ ፍላጎቱንም፡ ለመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ያስገዛ ስለኾነ፡ ከላይ የጠቀስኋቸውን፡ እነዚያን፡ በግለት የተነሣሡበትን፡ የጥፋት ኃይላት፡ ሌሎቹንም፡ "መልካሙን ትተህ፡ ክፉውን አድርግ!" የሚሉትን የክፋት ጠንቆች፡ ከቁጥጥሩ ሥር አውሎና አሸንፎ፡ በሥጋዊዉም ኾነ በመንፈሳዊው በኩል፡ የበጎ ወገን የኾኑትን፡ ለተራበ ማብላትን፡ ለተጠማ ማጠጣትን፡ ለታረዘ ማልበስን፡ የታመመውን፡ የታሠረውንና የተቸገረውን ኹሉ፡ መጠየቅንና እንዳስፈላጊነቱ፡ በተቻለ ዓቅም መርዳትን፡ መጻተኛውን፡ ስደተኛውንና ከርታታውንም ተቀብሎ፡ ባማባቡ ማስተናገድን፡ ከተቻለውም፡ ቋሚ መኖሪያን እንዲያገኝ ማድረግን፡ እነዚህን የመሰሉትን፡ መልካም ምግባራት ኹሉ "መፈጸም ይገባል!" ብሎ በማመንና ሌላውን ሰው እንደራሱ በማየት፡ የበኩሉን ድርሻ፡ በምንም ሳይቆጥብ፡ ያከናውናል።

፫ኛው፡- የነፍስ ፈተናና የሥጋ መከራ፡ በማናቸውም ሰው ላይ፡ በሕይወቱ ሳያደርስ አይቀርምና፡ በዚያን ጊዜ፡ ራሱን በጸም ያነጸው ሰው፡ ይህንኑ፡ የሚጠብቀውን ጽዋ፡ አስቀድሞ ፡ አውቆ፡ ለምሳሌ፡ ወድያው እንደሚቀበሉት፡ ፈተናና መከራ የሚቆጠረውን፡ "ጸም"ን በመሰለ ትሕርምት አማካይነት፡ የነፍስ ፈተናንና የሥጋ መከራን፡ በፈቃዱ፡ በራሱ ላይ በመጋበዝ፡ ራሱን፡ ከፈተናና ከመከራ፡ ነጻ ስላደረገ፡ በየጊዜው፡ ከውጭ በአፍአ፡ ማለትም፡ ከዲያብሎስና ከሰዎች የሚደርስበትን፡ ማናቸውንም ዓይነት ፈተናና መከራ፡ ከምንም ባለመቊጠር፡ ድል ይነሣል።

፬ኛ፡- ራሱን በጸም አንጾ የኖረ ሰው፡ መንፈሳዊዉን የኃይል ትጥቅ የተላበሰ ከመኾኑ የተነሣ፡ ሃይማኖትን ለማድከምና ምግባርን ለማበላሸት፡ ቀንደኞች አዘማኞች የኾኑትን፡ የክፋትና የኃጢአት ወገኖች ኹሉ፡ በዚህ፡ አስነኩን በገለጽኋቸው መንገዶች በመጠቀም፡ ሊቈጣጠራቸውና ድል ሊያደርጋቸው ችሎታ ስለሚኖረው፡ የነፍስና የሥጋ ፍላጎቱንም፡ ለመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ስላስገዛ፡ በዚህ ኃይሉና ሥልጣኑ፡ ሃይማኖቱን፡ ከድክመት፡ ምግባሩንም፡ ከብልሽት ማዳን ብቻ ላይኾን፡ የበለጠ እንዲጠነክሩ ያደርጋቸዋል።

፩ኛ፡- ሰው፡ ራሱን፡ በሕይወተ ሥጋ ለማኖር፡ ከእስትንፋሱ ቀጥሎ፡ የሚያስፈልገው፡ የመጨረሻው ሲሳይ ቢኖር፡ ውኃ ወይም እህል ነው፤ እነዚህን ሲሳያት፡ ከተወሰነ ዓቅም በላይ ለኾነ ጊዜ ሲያጣ፡ በእርግጥ፡ በሥጋው ይሞታል። እንግዲህ፡ በማስተዋል ተመልከቱት! በጸም መኖርን፡ በቁርጥ የተቀበለ ሰው፡ በፈቃዱ፡ "እኔ" እህል ውኃ የምቀምሰው፡ ከአንድ ቀን፥ ወይም፡ ከሦስት፥ ወይም፡ ከሰባት፥ ወይም፡ ከአሥር፥ ወይም፡ ከአርባ ቀኖች በኋላ፥ ወይም፡ እንዲኾን የምፈልገው ነገር፡ በኾነ ጊዜ ነው!" ብሎ መወሰን፥ ከዚህም በላይ፡ ይህንኑ የወሰነውን አላቡን፡ በሥራ ላይ አውሎ መፈጸም ይችላል። እንዲህ ከኾነ፡ ይህ ሰው፡ እህል ውኃ ላይቀምስ፡ ከዚያ ከወሰነው ጊዜ እስኪደርስ፡ ለመቆየት፥ ያሰበውንም ለመፈጸም እስኪችል ለመጠበቅ፡ በሰውነቱ ውስጥ፡ ራሱ ኮትኩቶ ያሳደገውና ያጎለበተው ጽኑ ችሎታ አለው ማለት ነው። *"ወዘአዝለፈ ትእግሥቶ፡ ውእቱ ይድኅን!"* ማለትም፡ *"በትእግሥቱ፡ እስከመጨረሻው የሚጸና፡ እርሱ ይድናል!"* በሚለው የጌታ ቃል መሠረት፡ ይህ ጸሚ፡ የትእግሥትና የተሰፋ ባለቤት መኾኑ ይረጋገጣል። ከዚህ የተነሣ፡ ይኸው ግለሰብ፡ ከእርሱ ቁጥጥር ውጭና ከዓቅሙ በላይ የሚኾነውን ማናቸውንም ነገር፡ በፍጹም ትእግሥትና ተስፋ ለመጠባበቅ፡ በቂ ኃይል ይኖረዋል።[ያ፻፸]

፪ኛ፡- ራሱን በጸም ያነጸው ይህ ሰው፡ እስካኹን መላልሼ እንደጠቀስሁላችሁ፡ ምሥጢሩን በማወቅ፡ በራሱ ፍላጎትና ፈቃድ፡ የነፍሱንና የሥጋውን ፈቃዳት፡ ለመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ስላስገዛ፡ አግባብነትና ተገቢነት ያለውን ማናቸውንም ነገር፥ ራሱን ጭምር፥ ለአመነበት ዓላማ ማዋልና ከማይፈልጋቸው ድርጊቶች፡ ራሱን መከልከል የሚችል መኾኑ ግልጽ ነው፤ በዚህ ዓይነት፡ የራሱን ክፉ ፈቃድ፡ በራሱ ፈቃድ፡ ለመለኮታዊው ፈቃድ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ለማስገዛት፡ ራሱን በራሱ ማዘዝን፡ አስቀድሞ እንዲህ ከቻለና ይህንኑም የተለማመደው ከኾነ፡ ለሌላው ሰውም ኾነ፡ ለማናቸውም ለአመነበት ነገር፡ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ፡ ቆራጥነቱ አያጠራጥርም።

፯ኛ፡- በጸም መኖርን የለመደው ይህ ሰው፡ አንዱ ፍላጎቱና ዓላማው፡ በእውነተኛው የሥጋና የነፍስ ጤንነት ኾኖ፡ በደስታና በፍቅር ለመኖር ከኾነ፡ ይህንኑ ፍላጎቱንና ዓላማውን፡ በሥራ ላይ አውሎ ሊፈጽመው ይችላል ማለት ነው፡ ይኸውም፡ ይህ ሰው፡ በአንድ ወገን፡ የነፍስንና የሥጋን አካላት ከሚጎዱ ነገሮች ኹሉ፡ ራሱን ለመከልከልና ለመጠበቅ፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ ለነፍስና ለሥጋ ጠቃሚ የኾኑትን ነገሮች ኹሉ ለመጋበዝና ለመቀበል፡ ኃይል ያለው ኾኖ፡ በመልካም ጤንነት፡ ደስታና ፍቅር ይኖራል ማለት ነው።

የዚህ ኹሉ ሓተታ ማጠቃለያው፡ አንድ እውነተኛ ጸሚ፡ የጸሙ ዓላማና ተግባር፡ ራሱን፡ ጎጂ የኾኑ ዕፀዋትን ከሚጨምረው፡ ከግዙፉ ሥጋዊ መብልና መጠጥ በመከልከል ብቻ ሳይወሰን፡ በይበልጥ፡ ከረቂቁ የነፍስ አስተሳሰብ በኩል ከሚነሣሡት ኃይላትም፡ ራስን በመጠበቅ ላይ የተመሠረተ የኾነ እንደኾነ፡ ግቡ የሠመረና ውጤቱም ያማረ ይኾናል።

ምክንያቱም፡ ከክፉ ድርጊት እና/ወይም ንግግር መታቀብ ብቻ ሳይኾን፡ ለእነዚህ፡ ለኹለቱም ዓይነቶች የምግባር ገጻት ምንጭ በኾነው፡ በረቂቁ ኅሊናም ላይ የመቆጣጠር ሥልጣን ስለሚኖረው ነው።።

ስለዚህ፡ ጸም፡ ራስን፡ ከጎጂ ዕፀዋት፥ ከእህል ውኃም ሳይቀር መከልከል፡ ወይም፡ የመብልንና የመጠጥን ልክና ዓይነት መምረጥና መወሰን ብቻ ኻይኾን፡ ሌሎች፡ የሰውነት አካልንና ሰብአዊ ሕይወትን የሚጎዱና የሚያጠፉ፡ ግዙፋንና ረቂቃን ኃይላት ስላሉ፡ ራስን፡ ከእነዚህ ኹሉ በመከልከልና በመጠበቅ፡ ኹለንተናን፡ ከጉዳትና ከጥፋት ማዳን የሚገባ መኾኑን አውቆ፡ "ጸም"ን፡ በእውነተኛ አቋሙ መጠቀም ያስፈልጋል።።

በዚህ ረገድ፡ መላውን የሰውን ዘር ሕይወት፡ በመልካም እየቀረጹ፡ ይህንኑ፡ ከትውልድ ወደትውልድ በማሸጋገር፡ በእምነት የመሩና የሚመሩ፡ በዓለም ላይ በየጊዜው የተነሡት ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች፡ ዓይነተኛ የገድል (የትግል) መሣሪያቸውና ኃይላቸው የነበረው፡ ይኸው "ጸም" መኾኑ፡ በኹሉ ዘንድ እንዲታወቅ ተደርጓል።። ለዚህም፡ ከሰው ልጆች መካከል፡ በእየዘመናቱ ከተነሡት፡ ኄኖክንና የአሪቱን ሙሴን ከመሰሉት፡ ጥንታውያን አበውና መንፈላውያን ነቢያት፥ እንዲሁም፡ ከሌሎቹ፡ ከብዙዎቹ ስመጥሮች ፈላስፎች በቀር፡ ዛሬ፡ በምድር ላይ ዓበይት የኾኑትን ልዩ ልዩ ባዕዳን እምነቶች የመሠረቱትን ሰዎች መጥቀስም ይቻላል።። ሰው የኾነው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳ፡ ሰውነቱን፡ ለመለኮታዊ ፈቃዱ፡ ፍጹም እንዲገዛ ያደረገውና የክፉት አበጋዝ የኾነውን ዲያብሎስን ድል የነሣው፡ አንዱ፡ በዚሁ በጸም ኃይል መኾኑ የተገለጸበትን የመጽሓፍ ቃል፡ ቀደም ብለን ሰምተናል።።

እዚህ ላይ፡ ከጸም ጋር አብሮ የሚካኼደው፡ "ስግደት"፥ እንዲሁም፡ የጸምና የስግደት ፍሬ የኾነው፡ "ንስሓ"፡ ኹለቱም ምግባራት ሊወሱ ይገባልና፡ ወደፊት ከአጽዋማቱ ተጥለን፡ እያከታተልን እናነሣቸዋለን።።

አጽዋማት

ጥያቄ፡- *አሰላኹን ተንትነህ ባስረዳኽን መልክና ሥርዓት የሚፈጸመው፡ ይህ የጸም ምግባር የሚካኼድባቸው የተወሰኑና የተመደቡ ጊዜያት ስላሉ፡ እነዚህ፡ ከላይ፡ አውስተሃቸው የነበሩት፡ በመታሰቢያነትና በማኅበር የምንጠማቸው አጽዋማት፡ ስንት እንደኾኑ ብትነግረን?*

መልስ፡- ኢትዮጵያውያን፡ ቀደም ብሎ በተብራራው ኹኔታ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው መሠረት እንዲጾሟቸው የተሠሩላቸው የዓመት አጽዋማት (ጾሞች)፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

፩ኛ. ጸመ ስደት፡
፪ኛ. ጸመ ነቢያት፡
፫ኛ. ጸመ ኢትዮጵያ (ጸመ ነነዌ)፥
፬ኛ. ጸመ አርብዓ፥

፫ኛ. ጸመ ድኅነት÷
፮ኛ. ጸመ ሐዋርያት÷
፯ኛ. ጸመ ፍልሰታ÷
፰ኛ. ጸመ ጳጉሜ ናቸው::

ጥያቄ:- *ታዲያ: እነዚህን አጽዋማት: እኛም አውቀናቸው: እንጾማቸው ዘንድ: መቼ መቼ እንደሚጾሙ አስታትለህ ልትገልጽልን ያስፈልገናል!*

መልስ:- የማወቅ ፍላጎታችሁ: እንዲህ እየላቀ በመኼዱ ደስ እያለኝ: ስለእነዚህ አጽዋማት የሚያስረዳውን ሓተታ: እንደሚከተለው አቀርብላችኋለሁ:-

፩ኛ. ጸመ ስደት÷

ኢትዮጵያውያን: መስከረም ፩ ቀን ከሚውለውና ለጊዜ አቈጣጠራቸው መነሻ ከኾነው: ከጌታና ከእመቤታችን ልደት በኋላ: የሚቀጥለው: የመጀመሪያ ጾማቸው: በወርኃ ጽጌ: ከመስከረም ፳፮: እስከኅዳር ፮ ቀን ድረስ ያለው: ቅድስት ድንግል ማርያምና ሕፃን ልጇ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበሉትን ቀጳሚ መከራ በማስታወስ: በእነርሱ ቅዱስ መንፈስ ኾነው የሚጾሙት: የስደት ጾም ነው:: ይህን ጾም የሚጾሙበት ምክንያት: እንዲህ በሚለው: በብሥራቱ (በምሥራቹ) ቃል ተጽፎ ይነበባል:-

"ኢየሱስም: በይሁዳ ቤተ ልሔም: በንጉሥ በሄሮድስ ዘመን በተወለደ ጊዜ: እነሆ: ሰብአ ሰገል: 'የተወለደው: የአይሁድ ንጉሥ: ወዴት ነው? ኮከቡን: በምሥራቅ አይተን: ልንሰግድለት መጥተናልና!' እያሉ: ከምሥራቅ: ወደኢየሩሳሌም መጡ::

"ንጉሡ ሄሮድስም ሰምቶ ደነገጠ፤ ኢየሩሳሌምም ኹሉ: ከእርሱ ጋር፤ የካህናትንም አለቆች÷ የሕዝቡንም ጸፎች ኹሉ ሰብስቦ: ክርስቶስ: ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው::

"እነርሱም: "'አንቺ ቤተ ልሔም! የይሁዳ ምድር! ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሽም፣ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን: ከአንቺ ይወጣልና!' ተብሎ: በነቢይ: እንዲህ: ተጽፏልና: የሚወለደው: በይሁዳ ቤተ ልሔም ነው፣ " አሉት::

"ከዚህ በኋላ: ሄሮድስ: ሰብአ ሰገልን: በሥውር ጠርቶ: ኮከቡ የታየበትን ዘመን: ከእነርሱ: በጥንቃቄ ተረዳ፤ ወደቤተ ልሔምም: እነርሱን ሰድዶ: 'ሺዱ! ስለሕፃኑ: በጥንቃቄ መርምሩ! ባገኛችሁትም ጊዜ: እኔ ደግሞ: መጥቼ እንድሰግድለት: ንገሩኝ!' አላቸው::

"እነርሱም: ንጉሡን ሰምተው ኼዱ፤ እነሆም: በምሥራቅ ያዩት ኮከብ: ሕፃኑ ባለበት ላይ መጥቶ እስኪቆም ድረስ: ይመራቸው ነበር፤ ኮከቡንም ባዩ ጊዜ: በታላቅ ደስታ: እጅግ ደስ አላቸው፤ ወደቤትም ፭ብተው: ሕፃኑን: ከእናቱ: ከማርያም ጋር አዩት፤ ወድቀውም ሰገዱለት፤ ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው: እጅ መንሻ: ወርቅና ዕጣን÷ ከርቤም አቀረቡለት:: ወደሄሮድስም እንዳይመለሱ: በሕልም ተረድተው: በሌላ መንገድ: ወደአገራቸው ኼዱ::

"እነርሱም ከኼዱ በኋላ፡ እነሆ፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ በሕልም፡ ለዮሴፍ ታይቶ፡ 'ሄሮድስ፡ ሕፃኑን፡ ሊገድለው ይፈልገዋልና፡ ተነሣ! ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ፡ ወደግብፅ ሽሽ! እስክነግርህም ድረስ፡ በዚያ፡ ተቀመጥ!' አለው።። እርሱም፡ ተነሥቶ፡ ሕፃኑንና እናቱን፡ በሌሊት ያዘና፡ ከጊታ ዘንድ፡ በነዚያ፡ 'ልጄን፡ ከግብፅ ጠራሁት!' የተባለው፡ እንዲፈጸም፡ ወደግብፅ ኼደ፡ ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ፡ በዚያ ኖረ።።

"ከዚህ በኋላ፡ ሄሮድስ፡ ሰብአ ሰገል እንደተሣለቁበት ባየ ጊዜ፡ እጅግ ተቈጣና ልኮ፡ ከሰብአ ሰገል እንደተረዳው ዘመን፡ በቤተ ልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን፡ ኹለት ዓመት የኾናቸውን፡ ከዚያም የሚያንሱትን ሕፃናትን ኹሉ አስገደለ።። ያን ጊዜ፡ በነቢዩ፡ በኤርምያስ፡ 'ድምፅ በራማ ተሰማ! ልቅሶና ብዙ ዋይታ! ራሔል፡ ስለልጆቿ አለቀሰች፡ መጽናናትም አልወደደችም፤ የሉምና!' የተባለው ተፈጸመ።።

"ሄሮድስም ከሞተ በኋላ፡ እነሆ፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ በግብፅ፡ ለዮሴፍ፡ በሕልም ታይቶ፡ 'የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና፡ ተነሣ! ሕፃኑን፡ እናቱንም ይዘህ፡ ወደእስራኤል አገር ኺድ!' አለ።። እርሱም ተነሥቶ፡ ሕፃኑንና እናቱን ያዘና፡ ወደእስራኤል አገር ገባ።።" ፪፻፫

ፍኖ፡- ጸመ ነቢያት (እና ስለጸመ ገሃድ)።።

ሀ፡ ጸመ ነቢያት፤

የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ቀን፡ ከእውነተኛው ዕለቱ፡ ከመስከረም ፩ ወደታኅሣሥ ፳፱ ቀን ባዛወረውና እስካኹን ሲሠራበት በቆየው የባዕዳን ሥርዓት፡ ጸመ ነቢያት፡ በኅዳር ፲፯ ተጀምሮ፡ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን እያበቃ ሲጸም ቆይቷል።። መኾኑም፡ ነገሩ፡ "ሃይማኖት" ስለኾነ፥ "ሃይማኖት"ም፡ ለሰው፥ ያውም፡ ለባዕዳን ተብሎ፡ ሊለወጥ ወይም፡ ሊሻሻል ስለማይቻል፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን፡ የጌታን የልደቱን በዓል፡ በጥንተ ዕለቱ፡ በመስከረም ፩ ቀን ማክበራቸው የጸና ኾኖ፡ ይህን፡ የነቢያትን ጸም፡ አኹን ባለበት፡ በዚሁ መልኩ፡ በእውነተኛው ኢትዮጵያዊ ሃይማኖትና መንፈስ፡ መጾማቸውን ይቀጥላሉ፤ ምክንያቱም፡ ጸሙ፡ <u>ታኅሣሥ ፩ ቀን ከሚውለው፡ ከብሥራቱና ከዕለተ ትስብእቱ</u> ቀደም ብሎ፡ በኅዳር ፲፯ ቀን ስለሚጀምር፡ ይኸው ጸም፡ "የነቢያት ጸም" ተብሎ፡ የጥምቀት ዋዜማ እስከኾነውና "ከተራ" እስከሚባለው፡ እስከጥር ፯ ቀን ድረስ እንዲቀጥል አግባብ ስለሚኾን ነው።። ጸሙ ያስገኘውም፡ ፍጹሙ ሕያው ፍሬ የኾነው፡ <u>የብሥራቱና የትስብእቱ ቀን፡ በጥር ፲፩</u> ቀን፡ ከሚከበረው ከ"ጥምቀት" በዓል ጋር፡ "አስተርእዮ" ተብሎ፡ <u>በዓቢይ በዓልነት፡</u> በታላቅ ሥርዓት አብሮ ይከበራል።። ታኅሣሥ ፩ ቀን የሚውለው፡ "ብሥራቱና ትስብእቱ"፡ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል የምሥራች ቃል፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን፡ ሰው ኾኖ የተጸነሰበት ዕለት መኾኑን እንድታውቁት ያስፈልጋል።።

ለጥምቀት ብቻ የተመደበው፡ "የገሃድ ጸም"፡ ለልደትም፡ በልማድ ተመሥርቶ ስለነበረ፡ ቀድሞውኑም ቢኾን፡ ይህ መደረጉ ተገቢ አለመኾኑ፡ እዚህ ላይ፡ ሊወሳ ይገባል። ራሱ፡ የነቢያት ጸም፡ ስላለ፡ ፈጽሞ የማያስፈልግ ስለነበረ ነው፤ የነቢያት ጸም ደግሞ፡ ከሰባቱ አጽዋማት መካከል፡ አንዱ መኾኑ እየታወቀ፡ በዚህ መልክ፡ ቀስ በቀስ፡ እንዲሻር ማድረግ አግባብ አልነበረም፤ አይቻልምና። ማሻሻል ቢያስፈልግ እንኳ፡ ሥርዓቱን ተከትሎ መፈጸም፥ ውሳኔውንም፡ በይፋ ማስታወቅ ይገባ ነበር። ያ፡ የልደት የ"ገሃድ ጸም" ልማድ፡ በሥራ ላይ በመዋሉ፡ ጸመ ነቢያት እንደተሻረ መቆጠሩን፡ ኹሉም ያውቀዋል። ያም ዘዴ፡ ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት፡ በተግባር ላይ ውሎ ከነበረው፡ ከዲያብሎስና ከባዕዳኑ ረቂቅ ዕቅድ ጋር የተያያዘ መኾኑን፡ ልትገነዘቡት ይገባል።

አኹን፡ የነቢያት ጸም፡ እውነተኛውን ኢትዮጵያዊ ሥርዓት ተከትሎ፡ እስከጥር ፤ ቀን ስለሚጸም፡ እንኳንስ ለልደት፡ ለጥምቀትም እንኳ፡ "ገሃድ" የሚባለው ጸም፡ አስፈላጊነቱ ቀርቷል፤ ብሥራቱንና ትስብእቱን፥ ጥምቀቱንም የያዘው በዓለ ዕለት፡ "አስተርእዮ" ተብሎ፥ የጌታ በዓል ከመኾኑ የተነሣም፡ ረቡዕና ዓርብ ላይ ቢወድቅ እንኳ፡ የገሃድ ጸም ሳያስፈልገው፡ እንደተለመደው፡ ፍስክ ኾኖ ይከበራል። በመስከረም ፩ ቀን ለሚውለው፡ ለእውነተኛው የጌታ የልደት በዓል፡ ሰሙነ ዋዜማ የኾነችውና እስካኹን፡ በፈቃድ ስትጸም የቆየችው ጳጉሜም፡ አኹን ራሷን ችላ፡ ለጌታ የልደት ቀን፡ እንደጸመ ገሃድ ኾና፡ በአግባቡ ስለምትጸም፡ ለመስከረም ፩ ቀን የልደት በዓል፡ ሌላ የገሃድ ጸም አያስፈልገውም። ስለዚህ አርእስተ ነገር፡ በበለጠ ለመረዳት፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው መጽሓፍ፡ በገጽ ፩፻፴፭-፩፻፺፫ የተሰጠውን ሓተታ መመልከት ያስፈልጋችኋል።

የጌታ የልደቱ በዓል ቀን፡ በአዋጅ፡ ወደጥንተ ዕለቱ እስከሚመለስበትም ጊዜ ድረስ፡ እናንተ፡ በእየበኩላችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት ካበቃችሁ፡ ነገሩ፡ ከላይ እንደተመለከተው፡ ሃይማኖትን የሚመለከት ከባድ ጉዳይ ስለኾነ፡ እናንተን የሚመስሉ፡ እውነተኞች ኢትዮጵያውያን ሞምር፡ በግልና በኅብረት፡ በጥንቱ ዕለቱ መሠረት፡ ይህንኑ የነቢያትን ጸም፡ እንደጥንቱ፡ ከኅዳር ፲፮ ቀን፡ እስከጥምቀት ዋዜማ፡ እስከጥር ፤ ቀን ድረስ ልትጸሙት፥ በዚያም ቀን፡ የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን፥ የሊቀ ካህናታችንንና የንጉሠ ነገሥታችንን፡ የብሥራቱንና የትስብእቱን በዓላት፡ ከጥምቀቱ በዓል ጋር፡ "አስተርእዮ" ብላችሁ፡ በተለመደው፡ የደመቀ ሥርዓት ልታከብሩት ይገባችኋል።

ይህ፡ የነቢያት ጸም፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ለሯሺ፲፮ ዓመታት የቆየው፡ የፍዳ ዘመን ያበቃ መኾኑን፡ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፡ የብሥራቱን (የምሥራቹን) ቃል እስከአሰማባት፥ እርሷም፡ "እንደቃልህ ይኹንልኝ!" ብላ፡ የፈጣሪዋን መልእክት፡ በፍጹም ፈቃደኛነት በመቀበሏ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን እስከፀነሰችባት ቀን ድረስ የነበሩት ነቢያት የጸሙት ነው።

አዳምና ሔዋን፡ የፈጣሪያቸውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል አምነው፥ አክብረውና ተከትለው በሞኖር ፈንታ፡ ያን ትተው፡ በገዛ ፈቃዳቸውና ምርጫቸው፡ የዲያብሎስን ቃል፡ አምነው ተከተሉ፤ ይህን በማድረጋቸው፡ በሥጋቸውም ኾነ በነፍሳቸው፡ እጅግ ተሳዱ፤ ተሠቃዩም። ስለዚህ፡ በፈጸሙት ጥፋታቸውና በደላቸው፡ በመሪር ኀዘን ተጸጸቱ፤ ንስሓም ገቡ። ከዚህ የተነሣ፡ ፈጣሪያቸው፡ በቸርነቱና በምሕረቱ ብዛት፡ ከወደቁበት የባርነት ግዛት፥ የኃጢአት ቀንበርና የሞት ፍዳ፡ ነጻ ሊያወጣቸው ወደደ፤ ወድዶም አልቀረ፡ *"በሓሙስ ዕለት መበመንፈቃ ለዕለት፡ እትወለድ፡ እምወለተ ወለትከ፤ ወእድኅከ ውስተ መርሀብከ፡ ወእትቤዘወከ በመስቀልየ መበሞትየ!"* ማለትም፡*"ከአምስት ቀኖችና ከቀን አሡሊታ በኋላ* (አምስት ሽህ አምስት መቶ ዓመታት ሲፈጸሙ)*፡ ከሴት ልጅህ ሴት ልጅ* (ከሔዋን ልጅ፡ ከድንግል ማርያም) *ተወልጄ፡ በቤትህ ምድራህ ድኪ፥ ተሰቅዬና ሞቼ እቤዝሃለሁ (ራሴን ሠውቼ፡ ከዲያብሎስ፥ ከኃጢኣትና ከሞት አድንሃለሁ)!"* ሲል፡ የተስፋን ቃል ሰጣቸው።

ጸመ ነቢያት፡ ያ የተስፋ ቃል የሚፈጸምበትን ጊዜ፡ በሃይማኖት በመጠባበቅ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ "ዳግማዊ አዳም" የተባለው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ዳግማዊት ሔዋን" በተባለችው፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን ተፀንሶ እስከተወለደባት ቀን ድረስ የኖሩት የእግዚአብሔር ወገኖች የጸሙት ጾም ነው። በዚህ ጾም፡ በስማቸው ተለይተው የታወቁ ቅዱሳን አበውና ቅዱሳት አንስት የጸሟቸው አጽዋማት ተካትተውበታል፤ ከእነዚህም መካከል፡ ሙሴ፡ ጽላተ ሕጉን በደብረ ሲና ከመቀበሉ በፊት፡ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት የቆየበት ጾም፥ ኤልያስ፡ በአምልኮ ጣዖት ረክሰው ከነበሩት፡ ከእስራኤሉ ንጉሥ ከአክዓብና ከአረማዊቷ ንግሥት ሚስቱ ከኤልዛቤል ፊት በሦስደደ ጊዜ፡ የጸመው የአርባ መዓልትና የአርባ ሌሊት ጾሙ ይገኛሉ። እንዲሁም፡ የጌታን መወለድ፡ በዕድሜ ልክ ሱባዔ ተወስነው፡ በፍጹም ተስፋ፡ በኢየሩሳሌም ኾነው ይጠባበቁ የነበሩት፡ ተስፋውም ተፈጽሞላቸው፡ የዓለሙን መድኃኒት፡ በቤተ መቅደስ፡ በግዕዘ ሕፃናት (በሕፃናት የተፈጥሮ ጠባይ) ሲያለቅስ የሰሙትና ያዩት፡ ነቢዩ ስምዖንና ነቢይቷ ሐና፥ እነርሱንም የመሰሉት ነቢያት የጸሟቸው አጽዋማት፡ በዚሁ፡ በነቢያት ጾም ተጠቃልለዋል። ከኹሉም በላይ፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራት፡ ጌታን ፀንሳ እስከወለደችበት ጊዜ ድረስ የጸመችው ጾም፡ ከእነዚህ መካከል፡ አንዱ ዋናው ኾኖ ይገኛል።

እኛም፡ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የቀድሞውን የነቢያትን ዘመን፡ ወደኋላ ኼደን በማዘከር፡ ይህን ጾም ስንጸመው፡ መለኮታዊው የተሰፋ ቃል ተፈጽሞልን፡ የዘለዓለማዊው ፍሬ ተጠቃሚዎች በመኾናችን፡ ከእነዚያ፡ ከቀደሙት ነቢያት ይልቅ ምን ያህል የታደልን መኾናችንን አውቀነውና ተገንዝበነው ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ የጀመርነውን መንፈሳዊ የህልውና ጉዞ፡ በእውነተኛው ሃይማኖታዊ ስሜት ቀጥለን፥ ለእኛ ሲል ሰው ኾኖ ካዳነን፡ ከፈጣሪያችን፡ የ"አስተርእዮቱ"፡ ማለትም፡ በብሥራቱና በትስብእቱ፥ በጥምቀቱም ምሥጢር መፈጸም፡ ማንነቱ ከታወቀበትና ገሃድ ኾኖ ከታየበት፡ ከመገለጫው መታሰቢያ ዕለት ደርሰን፡ በዓሉን፡ በፍጹም ደስታ እንድናከብረው ያበቃናል።

ለ፡- ጾመ ገሃድ።

"ገሃድ"፡ በግእዝ፡ "ግልጥ፥ የተገለጠ" ማለት ነው። በመለኮት ባሕርዩ ብቻ ይታወቅ የነበረው፡ የማይታየው፥ ረቂቅና መንፈስ የኾነው የእግዚአብሔር ቃል፡ በሰውነት መፀነሱ የታወቀው፡ የምሥራቹን ዜና ባሰማው፡ ስሙ "ገብርኤል" በተባለ፡ በእግዚአብሔር መልአክና ማርያም በተባለች፡ የአምላክ እናት ለመኾን፡ በፈጣሪ በተመረጠች፡ በአንዲት፡ የሰው ወገን በኾነች ድንግል፥ ከዚያም፡ "እጮኛዋ" ተብሎ፡ በንጽሕና እንዲያገለግላት፡ ከእግዚአብሔር በተሰጣት በዮሴፍ ዘንድ ብቻ ነበር፤ መወለዱም የታወቀው፡ በመላእክት፥ በጥቂት የቤተ ልሔም እረኞችና በሰብአ ሰገል ዘንድ ብቻ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ፡ እውነተኛ ማንነቱ፡ ማለትም፡ የእግዚአብሔር አብ ልጅና ሰው የኾነው አምላክ፡ እርሱ መኾኑ፡ ለዓለሙ በግልጥ የታወቀው፡ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ፡ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በተጠመቀ ጊዜ ነበር፤ በዚያን ጊዜም፡ እግዚአብሔር አብ፡ *"የምወድደው ልጄ፡ ይህ ነውና፡ እርሱን ስሙት!"* ብሎ፡ ከደመና ባሰማው ድምፁ፥ ራሱ እግዚአብሔር ወልድ፡ በሰውነት፡ በዚያ ቆሞ በመጥኘቱ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም፡ በነጭ ርግብ አምሳል፡ በራሱ ላይ በመቀመጡ፡ እውነታው ተረጋግጧል። ለዚህም፡ መጥምቁ ዮሐንስ፡ የመጀመሪያው ምስክር ኾኗል።

ስለዚህ፡ በጥምቀቱ ዕለት በተፈጸመው፡ በዚያ ሥርዓት፡ ይህ የእግዚአብሔር ዕፁብ ድንቅ ምሥጢር፡ እውን ኾኖ በገሃድ ስለታየ፡ ወራቱ፡ "እግዚአብሔር፡ በሰውነት ተገልጦ የታየበት ነው!" ለማለት፡ "ገሃድ" ወይም "አስተርእዮ" ተብሏል። ቀድሞ፡ በጥምቀት ዋዜማ ያለው ዕለት እንዲጸም ሲወሰን፡ ያ የጸም ቀን፡ "ጾመ ገሃድ" የተባለው፡ ከዚህ የተነሣ እንደነበረ ልታውቁት ይገባል።

ቀደም ብዬ፡ እንደገለጽሁላችሁ፡ እስካኹን፡ "ጾመ ገሃድ" ያለው፡ የጥምቀት በዓል ብቻ ነው። ምክንያቱም፡ እንደባዕዳኑ ልማድ፡ እስካኹን ይከበር የነበረው የጌታ የልደት በዓል፡ ጾመ ነቢያትን፥ እንዲሁም፡ የትንሣኤው በዓል፡ ዓቢይ ጾምን አስከትለው የሚውሉ ስለኾኑ፡ ጾመ ገሃድ አላስፈለጋቸውም፤ የጥምቀት በዓል ግን፡ በፍስኩ ወራት ውስጥ ይውል ስለነበረ፡ በዋዜማው፡ የጸም ዕለት የሚያስፈልገው ኾነ፤ የዚህም ምክንያት፡-

፩ኛ፡- ምናልባት፡ በዓሉ፡ ረቡዕ ወይም ዓርብ ዕለት የዋለ እንደኾነ፥ በዓሉ ደግሞ፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በመኾኑ፡ በጸም ሊከበር ስለማይገባ፡ ለዚያ፡ ለውጥ እንዲኾን ነው፤

፪ኛ፡- "ጋድ" ለሚለው ሕዝባዊ አነጋገር፡ "ለውጥ" የሚል ትርጉም የተሰጠው፡ ከዚህ የተነሣ ሲኾን፥ ለውጡም፡ መዘናጋት ደርሶ፡ መጾሙ እንዳይቀር፡ ጸመ ገሃዱ፡ ረቡዕ ወይም ዓርብ በሚውልበት ዓመት ብቻ ሳይኾን፡ በሌሎቹም፡ በማይጸምባቸው ዕለታት ጭምር፡ በየዓመቱ ተጠብቆ፡ እንዲፈጸም ለማድረግ ነው፤

፫ኛ፡- በዓሉ የሚከበርበት ወራት፡ ጸም ባለመኾኑ፡ ለምሥጢረ ቍርባን ዝግጅት የሚፈጸመው ሥርዓተ ቅዳሴ ደግሞ፡ የሚካኼደው፡ እንደትንሣኤ በዓል፡ በእኩለ ሌሊት ስለኾነ፡ ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉ ኹሉ፡ እየራሳቸውን በንስሓ ጸም ለማዘጋጀት እንዲችሉ ነው።

አኹን ግን፡ የጌታ ልደት፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በጥንታዊው ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸው፡ በእውነተኛው ዕለት፡ በመስከረም ፮ ቀን ውሉ እንዲከበር ስለተደረገ፡ ከላይ እንደተመለከተው፡ ከበዓሉ በፊት ያለችው ጻጕሜ፡ እንደ"ጸመ ገሃድ"፡ በሱባዔ ሥርዓት የምትጸም ኾናለች። ብሥራቱንና ትስብእቱን፥ ጥምቀቱንም አዋሕዶ በመያዝ፡ "አስተርእዮ" ተብሎ፡ ጥር ፲፩ ቀን ለሚከበረውም በዓል፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ እንደጥንቱ፡ በጎዳር ፲፪ ቀን ተጀምሮ፡ እስከጥር ፲ ቀን ድረስ እንዲቀጥል የተደረገው፡ የነቢያት ጸም ስላለው፡ የገሃድ ጸም አያስፈልገውም።

፫ኛ፡- ጸመ ኢትዮጵያ - ጸመ ነነዌ።

በዘመነ ብሉይ፡ በመካከለኛው ምሥራቅ ክፍለ ዓለም፡ "ነነዌ" በሚል ስም፡ በታላቅነቷ ትታወቅ በነበረችው ከተማ ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ሰዎች፡ የሠሩት ክፉትና ኃጢኣት፡ እጅግ ከመብዛቱ የተነሣ፡ ጽዋው ሞልቶ፡ መጥፊያቸው ስለደረሰ፡ ለፍጥረቱ ርኅራኄ ያለው እግዚአብሔር፡ ንስሓ ይገቡ ዘንድ፡ በላከላቸው፡ በነቢዩ ዮናስ ስብከት ተጸጽተው፥ ከክፉትና ከኃጢኣት ሥራቸውም ተመልሰው፥ ለሦስት ቀኖች፡ በጸም በጸሎት ተወስነው፥ ሕፃናትና እንስሳት ሳይቀሩ፡ ከእህል ውኃ ተከልክለው፡ የፈጣሪያቸውን ይቅርታና ምሕረት ስለለመኑ፡ ከታዘዘው የጥፋት መዓት ድነዋል።

እኛም፡ ይህን በማዘከር፡ ንስሓ ብንገባ፡ "እንድናለን!" በማለት፡ በየዓመቱ፡ ከዓቢይ ጾም መግቢያ፡ ኹለት ሳምንት አስቀድማ ካለችው ሰኞ ጀምሮ፡ እስከረቡዕ ድረስ፡ ለሦስት ቀኖች የምንጸማት ጾም፡ "ጸመ ነነዌ" እየተባለች ኖራለች። በአኹኑ ጊዜ ግን፡ በተለይ፡ ከ፲፱፻፷፯ ዓመተ ምሕረት ወዲህ፡ በኢትዮጵያ ላይ ከደረሰው አሠቃቂ መከራ የተነሣ፡ ይህችን ጾም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን፡ "ጸመ ኢትዮጵያ" ብለን እየጾምናት እንገኛለን። ይህም ያለበቂ ምክንያት አይደለም።

የነነዌን ጾም፡ "ጸመ ኢትዮጵያ" ብለን እንድንጾማት የማስፈለጉ ነገር፡ በእየኀሊናችን፡ አንዳንድ ጥያቄዎችን ማስነሣቱ አልቀረም። "ለመኾኑ፡ የቀድሞዎቹ የነነዌ ሰዎች፡ ለምን፥ እንዴትስ፡ የንስሓ ጾምን አደረጉ? በዚያ ጾማቸው፡ ፈጣሪያቸውን የለመኑትና የተፈጸመላቸው፡ ከቶ ምን ነበር?

የዛሬዎቹስ የኢትዮጵያ ሰዎች: የነነዌን ጾም: ለምን: በየዓመቱ ይጾሙታል? ምንስ ተደረገላቸው? በተለይ: 'ጾመ ኢትዮጵያ' መባሉ ያስፈለገበት ምክንያት ምንድር ነው?'

ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች: ከዚህ ቀጥሎ: በትንቢተ ዮናስ: ምዕራፍ ፫ እና በማቴዎስ ወንጌል. ምዕራፍ ፲፪+ ቊጥር ፴፮-፵፪ የተጠቀሱት የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት: መሠረታዊዉን ሃይማኖታዊ መልስ ይሰጣሉ::

ሀ. *"'ተነሥተህ: ወደዚያች: ወደታላቂቱ ከተማ: ወደነነዌ ሂድ! የሕዝቡ ክፋት በዝቶ: ከፊቴ ደርሷልና: የምነግርህን ስበክላት!' የሚል የእግዚአብሔር ቃል: ለኹለተኛ ጊዜ: ወደዮናስ መጣ:: ዮናስም: 'በሦስት ቀኖች ውስጥ: ነነዌ ትገለበጣለች!' ብሎ መስበክ ጀመረ:: በዚህ ጊዜ: የነነዌ ሰዎች እግዚአብሔርን አመኑ! "እንዲህም ሲሉ: ለጾም: አዋጅ ነገሩ፤ 'ሰዎችና እንስሶች: አንጻችን አይቅመሱ! ውኃንም አይጠጡ! ወደእግዚአብሔርም: በብርቱ ይጩኹ! ሰዎችም ኹሉ: ከክፉ መንገዳቸውና በእጃቸው ካለው ግፍ ይመለሱ! እኛ እንዳንጠፋ: እግዚአብሔር ተመልሶ ይጸጸት እንደሆነ+ ከጽኑ ቊጣውም ይመለስ እንደሆነ: ማን ያውቃል?' እግዚአብሔርም: ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ: ሥራቸውን አየ፤ ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገውም::"* ይህ: ከብሉዩ ኪዳን የተጠቀሰ ቃል ነው::

ለ. *"መምህር ሆይ! ከአንተ ምልክት እንድናይ እንወድዳለን!"* ብለው: በዘመኑ የነበሩት: የአይሁድ ሊቃውንት: አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን በጠየቁት ጊዜ: የሰጣቸው መልስ: "ክፉና ዓመፀኛ+ አመንዝራም ትውልድ ምልክትን ይሻል፤ *ነገር ግን: ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር: ሌላ ምልክት አይሰጠውም:: ...የነነዌ ሰዎች: በፍርድ ቀን: ተነሥተው: ይህን ትውልድ ይፋረዱታል፤* በዮናስ ስብከት: ንስሓ ገብተዋልና፤ እነሆም: ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ:: ንግሥተ ዓዜብ: በፍርድ ቀን ተነሥታ: ከዚህ ትውልድ ጋር ትፋረዳለች፤ ታሳፍረዋለችም፤ የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ: ከምድር ዳርቻ መጥታለችና፤ እነሆ+ ከሰሎሞን የሚበልጥ: ከዚህ አለ!" የሚል ነበር:: ይህ: ከአዲሱ ኪዳን የተጠቀሰ ቃል ነው::

እንግዲህ: እዚህ ላይ ያለውን ቁም ነገር: በማስተዋል ተመልከቱት! የነነዌ ሰዎች: ለመለኮታዊው ምሕረት ያበቃቸውን: ሃይማኖትና ምግባር አሟልተው እንደተገኙ: ከላይ የተመለከቱት ጥቅሶች ያስረዳሉ፤ ይህም: የነነዌ ሰዎች: ንስሓ በመግባት የጾሙትና የጸለዩት: በእውነትና በመንፈስ እንደነበረ: ራሱ: የንስሓቸው ፍሬ: አጉልቶ አሳይቷል፤ አረጋግጧልም ማለት ነው:: "በእግዚአብሔር አመኑ!" የሚለው ቃል: እግዚአብሔር: የተናገረውን: የሚፈጽም ኃያል አምላክ+ ከለመኑትም: ይቅር የሚል: መሐሪ መኾኑን: ፈጽመው እንዳመኑ የሚያመለክት ስለኾነ: ስለእግዚአብሔር ያላቸውን ትክክለኛ እውቀት ያሳያል:: ይህ: ሃይማኖት ነው::

እንስሳት ጭምር፡ ውኃ እንኳ አለመቅመሳቸው፡ የጾማቸውን ጽኑነት÷ ወደእግዚአብሔር፡ በብርቱ መጮኻቸው ደግሞ፡ የጸሎታቸውን ልባዊነት÷ በመጨረሻም፡ ሰዎች ኹሉ፡ የክፋት መንገዳቸውንና የግፍ ተግባራቸውን ትተው፡ ወደበጎው መመለሳቸው፡ የንስሓቸውን እውነተኛነት ያረጋግጣል። ይህም ምግባር ነው።።

እግዚአብሔር የሚቀበለው የንስሓ ጸም÷ ጸሎትና ምጽዋት፡ እንዲህ ዓይኑን መኾኑን፡ እነሆ፡ ውጤቱ መስክሩዋል። እያንዳንዳችን፡ የእየራሳችንን ሃይማኖታዊ ምግባር፡ መመልከትና መመዘን ያለብን፡ በዚህ መልክ መኾን እንደሚኖርበት፡ ይህ፡ የነነዌ ሰዎች፡ የንስሓ ፍሬ ያስተምረናል። አምን÷ በእግዚአብሔር ስም የሚደረግ ነገር ኹሉ፡ በእውነትና በመንፈስ የሚፈጸም መኾን አለበት።።

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ የነነዌን ጾም ስንጾማት የኖርነው፡ በዚህ መልኳና ይዘቷ ሳይኾን፡ በልማድ ቅርስነቷ፡ ወይም በታሪካዊነቷ ብቻ ከኾነ፡ በተሳሳተው ጎዳና ስንጓዝ ቆይተናል ማለት ነው። በእውነተኛ መልኳና በትክክለኛ ይዘቷ እንዳልጾምናትማ፡ በየዘመናቱ ደርሰው ከነበሩት ጋር፡ ይኸው፡ በጊዜአችን እየሰበሰብነው ካለው፡ የመከራ መከር፡ በሚደርስብን የቅጣት መቅሠፍት ጎልቶ ይታያል። ታዲያ÷ የነነዌና የነዋሪዎቿ ዝክረ ነገር፡ ደብዛው ሳይቀር ጠፍቶ፡ በታሪካዊነት ብቻ እየተወሳ ባለበት፡ በዚህ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ከእነርሱ በፊት የነበርነው÷ በእነርሱም ዘመን የኖርነውና ዛሬም፡ ከእነርሱ ምውትነት በኋላ፡ በሕያዋንነታችን ቀጥለን የምንገኘው፡ እኛ፡ ኢትዮጵያውያንና አገራችን ኢትዮጵያ፡ ዛሬ፡ ተዘፍቀን ከምንሠቃይበት የጥፋት መዓት ለመዳን እንችል ዘንድ፡ ጾመ ነነዌን፡ በእውነተኛ መልኳና በትክክለኛ ይዘቷ፡ በሕያውነት እንጂ፡ እንዴት፡ በልማዳዊ ምውትነትና በታሪካዊ መዘክርነት ብቻ ልንጾማት ይገባናል? ይህም፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በሕይወት ቆመን፡ ሕያው በኾነው ኢትዮጵያዊነታችን፡ የምንቀበለውንና እውን የኾነውን፡ ይህን፡ የመንፈስ ፈተናና የሥጋ መከራ ተቋቊመን ድል ለማድረግ፡ "ጾመ ኢትዮጵያ" ብለን በሕያውነት ልንጾማት ይገባል ማለት ነው።።

ስለዚህ፡ መድኃኒታችን፡ "ንግሥተ ዓዜብ" ብሎ የጠራትና የተናገረላት፡ ኢትዮጵያዊቷ እናታችን ማክዳ እንዳደረገችው ኹሉ፡ እኛም ልጆቿ ኢትዮጵያውያን፡ ከዮናስና ከሰሎሞን የሚበልጠውን፡ የእርሱን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል በመስማትና በመከተል፡ ይህችን ጾም፡ ከንግሥት እናታችን፡ ከማክዳ በምትበልጠው፡ በሰማይና በምድር ንግሥታችንና በዘለዓለም የምሕረት ቃል ኪዳን እናታችን፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም፡ "ጾመ ኢትዮጵያ" ብለን ሰይመን፡ እንጾማታለን። ስንጾማትም፡ "የእኛን የተለየ ፍላጎት ፈጽምልን!" ብለን ሳይኾን፡ "በግልና በአገር ደረጃ የሠራነውን ክፋትና በደል÷ ክህደትና ዓመፅ÷ ኃጢአትና ግፍ" ይቅር ብለህ፡ የአንተን ቅዱስ ፈቃድና ዕቅድ እንድናውቅ አድርገን! በዚያም ፈቃድህና ዕቅድህ ሥር ለመኖር አብቃን!" ብለን ነው።።

እንዲሁ፡ በእግዚአብሔር እውነትና መንፈስ ኾነን፥ በእርሱም ሃይማኖትና አምልኮ ጸንተን፡ የምንጸመው ጸምና የምንጸልየው ጸሎት፥ ደግሞ፡ እርሱ፡ ኃጢኣታችንን ይቅር እንዳለን፡ እኛም የበደልናቸውን ይቅርታ ጠይቀንና የበደሉንን ይቅር ብለን፥ ከፉ መንገዳችንንም ትተን የምንገባው እውነተኛ ንስሓ፡ የእርሱን፡ የፈጣሪያችንን ፈቃድ ለማወቅ ያስችለናል። አለዚያ፡ ጸማችን፥ ጸሎታችንና ምጽዋታችን ከንቱ ኾኖ ይቀራል።

በግልም ኾነ በጋራ ሕይወታችን፡ ማናቸውም፡ የኾነውና የሚኾነው ነገር ኹሉ፡ የእኛ ሳይኾን፡ የእርሱ፡ የአምላካችን ፈቃድና ዕቅድ መኾኑን ማወቅ፡ ሃይማኖት ነው። ብዙውን ጊዜ፡ ሕይወታችን ቅጥ ያጣ፥ ዓላማና ትርጉም የሌለው፥ ግራ የሚያጋባ፥ ውሳጣዊና አፍአዊ ሰላምና ጸጥታ የተለየው፥ ዕረፍት ተነሥቶት የሚባዝን፥ ሥጋትና ጭንቀት የመላበት ኾኖ እናገኘዋለን፤ የዚህ ዋና ምክንያት፡ አስተሳሰባችን፡ በዚህ የሃይማኖት መመሪያ ላይ ባለመመሥረቱ መኾኑንና ይህን የመሰለው ችግር የመነጨው፡ ከእየራሳችን እንጂ፡ ከእግዚአብሔር፡ ወይም ከሌላ አለመኾኑን፡ በዚህ ጊዜ፡ መረዳት ይኖርብናል።

"እግዚአብሔር፡ የነነዌን ሰዎች ጸሎት ሰምቶ፡ የምሕረት መልሱን የሰጣቸው፡ በሦስት ቀናት የንስሓ ጸማቸው ነበር። ዛሬስ፡ የኢትዮጵያ ሰዎች፡ በየዓመቱ ሲጸሙት በመኖራቸው፥ በተለይም፡ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ፡ በስደት ኑሮአቸውና እኹንም በአገራቸው፡ "ጸመ ኢትዮጵያ" ብለው ለሚጸሙት ኢትዮጵያውያን ሳይቀር፡ ምን ተደረገላቸው?" ብለው የሚጠይቁ ይኖሩ ይኾናል፤ ለእኒህ ጠያቂዎች፡ የሚሰጣቸው መልስ፡ "የጸሙን ዓላማ፡ ከላይ በተገለጸው መሠረት፡ እንደገና በጥሞና ሊያስተውሉትና በትክክል ሊገነዘቡት ያስፈልጋቸዋል፤" የሚል ይኾናል። ጸሙ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ እንደነነዌ ሰዎች፡ የምሕረቱን መልስ ሊያስገኝላቸው ያልቻለው፡ ችግሩ፡ ከጸሙ ስያሜ ሳይኾን፡ ከትውልዱ የንስሓ ጉድለት መኾኑን፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን አውቀውት፥ ይኸው፡ የትውልዱ እምቢተኛነት፡ እያስከተለ ያለውን መለኮታዊ ዳኝነት በማድነቅና የየራሳቸውን የንስሓ ድርሻ በማበርከት፡ ይህንኑ ጸም፡ በየዓመቱ፡ በኢትዮጵያዊነቱ፡ እነሆ፡ እየቀጠሉ ይገኛሉ።

እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተነሣ፡ እያንዳንዳችን በግል፥ በጋራም ኹላችን፡ ለእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ፡ መሣሪያዎቹ መኾናችንን አምነን፥ እየራሳችንን፡ ለዚህ አገልግሎት ማቅረብ ይጠበቅብናል። ይህን የተቀደሰ ግዳጅ በመፈጸም ፈንታ፥ ወይም፡ ይህን ማድረግ ሲገባን፡ ነገር ግን፡ እስከትርብ ጊዜ ድረስ፡ በታሪክ የደረሰው ኹሉ፡ መቀጣጫ ትምህርት ኾኖን ሳንጠቀምበት በመቅረታችን፡ እነሆ፡ ዛሬ ሲካኼድና ሲፈጸም ለሚታየው አሳዛኝ ኹኔታ፡ እየራሳችንን ዳርገን እንገኛለን።

ምዕራፍ ፯፣ ጸም፡- አምን! ስለጸም።
አጽዋማት።

ይህም፡ በአገርም÷ በውጭም ያሉት፡ የቤተ ሕዝቡ÷ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው ወገኖች፡ አንድ ኾነው÷ ተስማምተውና ተባብረው፡ ከመሪዎቻቸው፡ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከድንግል ማርያም የተቀበሉትን አደራና ኃላፊነት፡ በአግባቡ፡ በሥራ ላይ ባለማዋላቸው መኾኑ፡ እየሰበሰቡት ያለው መራራ ፍሬ፡ ራሱ ጩኾ ስለሚመሰክር፡ ሊታበል አይቻልም።

እኒህ፡ የዘመኑ ባለአደራዎችና ኃላፊዎች፡ የተሰጣቸውን ሥልጣን፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከሚፈጽሙበት ይልቅ፡ እርስ በርስ በመለያየትና ሌላውን በማለያየት፡ በይፋ በሚያራምዱት ጥላቻና ፀብ፡ ለእየራሳቸው ጠባብ ዓላማና ፍላጎት ማራመጃ አድርገውት ይታያል። እንዲያውም፡ እርሱን እግዚአብሔርን ሳይቀር በመካድ÷ ወይም፡ የእርሱን የተቀደሰ ስም÷ ሃይማኖቱንና የእርሱ የአገልግሎት ተቋም የኾነችውን ቤተ ክርስቲያንን፡ ማለትም፡ የእርሱ አገልጋዮች የኾኑትን ካህናትንና ምእመናንን፡ ለማናቸውም ዓይነት ሰብአዊ ዓላማቸው፡ መሣሪያና መጠቀሚያ በማድረግ በሚያካኺዱት አሠራራቸው፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን÷ በኢትዮጵያዊነትም ላይ ያለው ባለቤትነት፡ የእግዚአብሔር መኾኑ ቀርቶ፡ የየእራሳቸው እንደኾነ÷ ወይም፡ በዚሁ ባለቤትነት ላይ፡ አንዱ ከሌላው የሚበልጥ፡ ቅድሚያና አለቅነት ያላቸው አስመስለውታል።

ይህን የመሰለው ድርጊት፡ በሥጋ ብቻ ሳይኾን፡ በነፍስም፡ ታላቅ ፍዳን የሚያስከትል ስለኾነ፡ ይህን በመሰለ ተግባር ላይ የተሠማሩ÷ ወይም፡ አዝማሚያው እንኳ ያላቸው ቢኖሩ፡ ከዚህ ከተሳሳተ መንገዳቸው፡ በንስሓ ይመለሱ ዘንድ፡ ከዮናስና ከሰሎሞን የሚበልጠው፡ የነቢያት ጌታ÷ የካህናት አለቃና የነገሥታት ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ራሱ፡ በቃሉ እየመከረ ያስጠነቅቃቸዋል።

፩ኛ፡- ዓቢይ ጾም።

መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተጠመቀ በኋላ፡ የመጣበትን የማስተማርና የማዳን ተልእኮውን ከመጀመሩ በፊት፡ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ። እኛም፡ ኢትዮጵያውያን፡ ይህን ጾም፡ "የጌታ ጾም" ብለን፡ በመታሰቢያነት፡ በየዓመቱ እንጾመዋለን።

የዚህም ምክንያት፡ አምላካችን፡ በዚህ ጠሙ አማካይነት፡ የዘር ጠላታችን የኾነው ዲያብሎስ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ የሰውን ልጆች ሲያጠምድበት የኖረውን ረቂቅ ፈተና፡ ለእኛ ሲል፡ በፍጹም ትእግሥትና ትሕትና ተቀብሎ፡ ክፉውን ኃይል ድል ስላደረገልን÷ ለእኛም፡ በዲያብሎስና በሥጋ ፈቃዳት ላይ አሸናፊዎች ልንኾን የምንችልበትን፡ የሃይማኖትን መንፈሳዊ ትጥቅ ስላስታጠቀን፤ የምግባርንም መንፈሳዊ መሣሪያ ስላስጨበጠን ነው።

ስለዚህ፡ ይህን፡ የእርሱን ጾም በምንጾምበት ጊዜ፡ የምንጾመው፡ በክርስቶስ መንፈስ ስለኾነ፡ ኹልጊዜም፡ በፈቃዳችን፡ የእርሱ መከራ ተካፋዮች÷ የክፉውም መንፈስ አሸናፊዎች እንኾናለን።

ጸማችንን ኹሉ የምንጸመው፡ በክርስቶስ መንፈስ ካልኾነ፡ "እውነት እላችኋለሁ፣ ዋጋቸውን ተቀብለዋል!" እንደተባሉት ግብዞች መኾናችን ነውና፡ በአጿጿማችን እውነተኛነትና መንፈሳዊነት፡ አምን፡ በብርቱ ልንጠነቀቅ ይገባናል።

ይህ "የጌታ ጸም"፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በሰውነቱ የጸመው ከመኾኑ ጋር፡ ከአጽዋማቱ ኹሉ በላይ፡ ታላቅና ረዥም ስለኾነ፡ "ዓቢይ ጸም" ይባላል፤ በሕዝባዊ አነጋገርም፡ "ሑዳዴ" በሚል አጠራር ይታወቃል። "ሑዳድ"፡ በምድራዊ ገበሬ፡ በማኅበር እየታረሰ፡ ማለፊያ ሰብል የሚያስገኝ፡ ሰፊ የመንግሥት መሬት ማለት ሲኾን፡ "ሰማያዊው ገበሬ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለዘለዓለማዊ መንግሥቱ እርሻነት ያበቃቸው ካህናትና ምእመናንም፡ ዛሬ፡ በየዓመቱ፡ በኅብረት ኾነው፡ በጸም እያረሱ፡ የንስሓን ፍሬ የሚሰበስብበት ሰፊ መንፈሳዊ እርሻ ስለኾነ፡ ይህ የጌታ ጸም፡ "ሑዳዴ" ይባላል።

ይኸው "ሑዳዴ"፡ "ታላቁ ጸም" የተባለበት ምክንያት፡ አምላካችን ስለጸመው ብቻ ሳይኾን፡ ከዚህ፡ አርባ ቀኖችን ከያዘው የጌታ ጸም ጋር፡ "ጸመ ሕርቃል" የሚባለው፡ የመጀመሪያው ሳምንት ጸምና በጸሙ መጨረሻ ላይ፡ "ሰሙነ ሕማማት" ተብሎ የሚጸመው ጸም፡ እነዚህ፡ ኹለት የጸም ሳምንታት፡ ከዚሁ፡ ከ"ዓቢይ ጸም" ጋር እንዲያያዙ በመደረጉ ነው።

ሀ. "ጸመ ሕርቃል"፡ በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ክርስቲያኖችና የአምላካችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል፡ ከወራሪ አረማውያን እጅ ለማዳን፡ "ሕርቃል" የተባለው፡ ክርስቲያኑ፡ የቢዛንቲን ርእሰ ነገሥት፡ ሠራዊቱን ይዞ፡ በሃይማኖታዊ ቅንዓት ለፈጸመው ተጋድሎና ለተጎናጸፈው የድል አክሊል መታሰቢያ ይኾን ዘንድ፡ በጊዜው ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ በረከት ነው።

ለ. "ሰሙነ ሕማማት"፡ ከዕለተ ትንሣኤ በፊት፡ ከሆሣዕና እሑድ ማታ፡ እስከቅዳሜ ስዑር ማታ ያሉት ዕለታት ናቸው፤ "ሰሙነ ሕማማት"፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለእኛ ሲል፡ በተለይ ከምሴተ ሐሙስ (ከሐሙስ ማታ) ጀምሮ፡ የትንሣኤው ብርሃን እስከበራባት፡ እስከእሑድ ሌሊት ድረስ፡ የተቀበላቸውን ልዩ ልዩ መከራዎች በማሰብ፡ በግልም ኾነ፡ በማኅበር ተወስነን፡ እየራሳችንን፡ በሥጋም÷ በነፍስም÷ በመንፈስም፡ የእርሱ ሥቃይ ተካፋዮች በማድረግ፡ በፍጹም ትሕትናና ንስሓ÷ በጸምና በጸሎት÷ በስግደትና በእርሱ ፍቅር ተጠምደን የምንሰነብትበት "የመከራዎች ሳምንት" ማለት ነው።

ይኸውም፡ እርሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአስቆሮታዊው ይሁዳ መሪነትና ጠቋሚነት፡ በአይሁድና በሮማውያን ወታደሮች ተይዞ÷ የፌጥኝም ታሥሮ÷ በዕለተ ዓርብ፡ በአደባባይ ሲንገላታ ከዋለ በኋላ፡ ተገርፎና ራቁቱን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሲሞት÷ የሾህ አክሊል ከተቀዳጀው ራሱና በጦር ከተወጋ ጎኑ፡ ደሙን ያፈሰሰበት ነው።

በዚያ አካለ ሥጋውም፡ ወደመቃብር ወርዶ፡ ቅዳሜ ስዑርን ሲያሳልፍ፡ በአካለ ነፍሱ ደግሞ፡ ወደሲያል ወርዶ፡ ላመኑበት ነፍሳት፡ ነጻ የመውጣታቸውን ምሥራች የሰበከበት ነው።

ከደስታ በፊት፡ ፈተና መኖሩን÷ እንዲሁም፡ ያለመከራ ጸጋ÷ ያለድካም ዋጋ የማይገኝ መኾኑን እንዳንዘነጋ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ የሕማማትን ሳምንት፡ በተለየ ጥብቅ መንፈሳዊ ሥርዓት እናሳልፈዋለን፤ ፋሲካውን፡ በታላቅ ጉጉት÷ የትንሣኤውንም በዓል፡ በጥልቅ ስሜት እንድንጠብቀው የሚያደርገን ይኸው ይዘታችን ነው። በጸመ ፍልሰታ፡ ለቃል ኪዳን እናታችን፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም÷ በሰሙነ ሕማማት ደግሞ፡ ለቃል ኪዳን አምላካችን፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ የምንገልጸው የፍቅር ስሜት፡ ሰው ለኾነው አምላክና እርሱን ለወለደችው እናቱ ያለን ፍቅር፡ ፍጹም መኾኑን ያስረዳል።

እነዚህ፡ የሰሙነ ሕማማት ቀኖች፡ እያንዳንዳችን፡ ኃጢኣታችንን በማመንና የበደሉንን ኹሉ ይቅር በማለት፡ አምላካችን፡ እኛንም ይቅር እንዲለን፡ ንስሓ የምንገባባቸው÷ በኢትዮጵያ ላሉትና በያለበት ለተበታተኑት ወገኖቻችን፡ ለአገራችንና ወገኖቻችን ለሚኖሩባቸው አህጉር÷ ለመላውም ዓለም ደኅንነትና ሰላም የምንጸልይባቸው÷ ከፈጣሪያችንም ጋር ያለንን ሕያው ቃል ኪዳን የምናጠናክርባቸው ናቸው።

ሰሙነ ሕማማትን፡ ከጸመ አርብዓ ቀጥለን የምንጸመው፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆና የአርባ ቀኖች ጾሙን ፈጽሞ፡ በትምህርቱና በተአምራቱ፡ ማንነቱን ካሳወቀ በኋላ፡ ሰው ኾኖ፡ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን፡ የመጨረሻውን ዓላማ፡ በጭንቀትና በሥቃይ የፈጸመባቸው ዕለታት የሚገኙባት ሳምንት በመኾኗ ነው።

"እኔ፡ ለእውነት ልመሰክር ተወልጃለሁ፤ ስለዚህም፡ ወደዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የኾነ ኹሉ፡ ድምፄን ይሰማል። ...እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ። ...ብርሃን ወደዓለም ስለመጣ÷ ሰዎችም፡ ሥራቸው ክፉ ነበርና÷ ከብርሃን ይልቅ፡ ጨለማን ስለወደዱ፡ ፍርዱ ይህ ነው። ክፉን የሚያደርግ ኹሉ፡ ብርሃንን ይጠላልና፤ ሥራውም እንዳይገለጥ፡ ወደብርሃን አይመጣም። እውነትን የሚያደርግ ግን፡ ሥራው፡ በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደኾነ ይገለጥ ዘንድ፡ ወደብርሃን ይመጣል።"[፫፻፮] ብሎ፡ እውነተኛው መምህር፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለሕዝቡ በተናገረው ቃል፡ የአይሁድ ካህናት አለቆችና ሊቃውንት÷ የሕዝቡም ሽማግሌች፡ ሥልጣናቸውን÷ ክብራቸውንና ጥቅማቸውን ይጠብቁበት የነበረው ሰው ሠራሽ ሥርዓታቸው ሊፈራርስባቸው መኾኑን ከተገነዘቡበት ጊዜ ጀምሮ፡ ጽኑ ቅንዓት አድሮባቸው፡ በተንኰልና በሐሰት አስይዘው÷ በአረማውያኑ ሮማውያን እጅ ሊያስገድሉት፡ ምክንያት ሲፈልጉ ቆይተው ነበር።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዘለዓለማዊው የጽዮን ንጉሥ በመኾኑ፡ እንደነቢያት ቃል፡ *"ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ! በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ፡ ቡሩክ ነው! ሆሣዕና በአርያም!"* የሚለውን የምስጋና ቃል፡ ከደቀ መዛሙርቱና ዘንባባ ይዘው ከተከተሉት ሕዝብ፥ ከሕፃናትና ከድንጋዮች ሳይቀር እየተቀበለ፡ በአህያዋና በውርንጭላዋ ላይ ተቀምጦ፡ በፍጹም ትሕትና፡ ወደኢየሩሳሌም ከገባ በኋላ፡ *"ቤቴ፡ "የጸሎት ቤት' ትባላለች!"* [ማቴ ፳፩] *ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን፡ የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት!"* [ማቴ ፳፩] ብሎ፡ ቤተ መቅደሱን፡ የገንዘብ መሰብሰቢያ መደብር ያደረጉትን ሰዎች፡ ከነዕቃቸውና ገበታቸው፡ በሥልጣኑ ባስወጣበት ዕለት፡ ያ፡ የቅንዓታቸው ጽዋ ሞላ። የት፥ በምን ሰዓትና እንዴት እንደሚይዙት፡ ከዚያች ዕለት አንሥተው፡ ይዶልቱ ጀመር፤ ሰኞንና ማግሰኞን ተመካከረው፡ ረቡዕ፡ ነገራቸውን ቆረጡ። እንዲያሲዛቸውም፡ ከአስቆሮቱ ይሁዳ ጋር፡ በሰላሣ ብር ተስማሙ። ከኹለቱ፡ የጸመ ድኅነት ዕለታት መካከል የመጀመሪያዋ የኾነችው፡ "ረቡዕ"፡ የምትጸመው በዚህ ምክንያት ነው።

፩. ጸሎተ ሐሙስ/ምሴተ ሐሙስ/የሐሙስ ምሽት፡- ፈጣሪያችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በተቃዋሚዎቹ ተንኰልና ኃይል ተይዞ፡ ወደሊቃነ ካህናቱ ሸንጎና ወደሮማውያን የፍርድ አደባባይ የሚቀርብበት ጊዜ እንደደረሰ አውቆ፡ ቅዱሳን ሐዋርያቱን፡ ለመጨረሻዋ የፋሲካ ራት ሰበሰባቸው፤ ያችም ዕለት፡ "ጸሎተ ሐሙስ"፡ ወይም "ምሴተ ሐሙስ"፡ ማለትም፡ "የሐሙስ ምሽት" በሚል ስያሜ የምትታወቀው ናት።

በዚያች ራት ላይ፡ በአሪቱ ሕግ መሠረት፡ የብሉዩን (አሮጌውን) ኪዳን የፋሲካ በግ ሥርዓት፡ ለመጨረሻ ጊዜ ፈጸመ፤ የአዲሱ ኪዳን ዘለዓለማዊ ሥርዓት የኾነውንም፡ የቅዱስ ሥጋውንና የክቡር ደሙን ቁርባን መሠረተ፤ ምሥጢራትን ገለጸ፤ መመሪያዎችን ሰጠ፤ በአርአያነትም አስተማረ።

ይኸውም፡ ሲበሉ፡ ኅብስቱን አንሥቶ፥ ባርኮና ቆርሶ፡ *"ይህ ሥጋዬ ነው፤ እንካችሁ ብሉ!"*፥ ጽዋውንም አመስግኖ፡ *"ስለብዙዎች፡ ለኃጢኣት ይቅርታ የሚፈሰስ፡ የአዲስ ኪዳን ደሜ፡ ይህ ነው፤ ኹላችሁ ከእርሱ ጠጡ!"* ብሎ፡ የቅዱስ ቍርባንን ምሥጢርና ሥርዓት፥ እግራቸውንም በማጠብ፡ *"እኔ፡ ለእናንተ እንዳደረግሁ፡ እናንተ ደግሞ፡ እንዲሁ ታደርጉ ዘንድ፡ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ!"* ብሎ፡ ትሕትናን፥ በኑዛዜውም ቃል፡ *"ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ፡ ሰዎች ኹሉ ያውቁ ዘንድ፡ እርስ በእርሳችሁ እንድትዋደዱ፡ እነሆ፡ አዲስ ትእዛዝ ሰጥቻችኋለሁ!"* ብሎ፡ ፍቅርን፥ በጌቴሴማኒ ከመይያዙ በፊት፡ *"ወደፈተና እንዳትገቡ፡ ትጉ! ጸልዩም! መንፈስስ ተዘጋጅታለች፤ ሥጋ ግን ደካማ ነው!"* ብሎ፡ በሃይማኖት ቆራጥ ኾኖ፡ በጸሎት መትጋትን፡ ራሱ [ማቴ ፳፮፤] ፈጽሞ፥ ለእነርሱ በማሳየት ነው።

ሰሙነ ሕማማት፡ ይህን ምሥጢሩን እውቀን፥ ሥርዓቱን ተቀብለንና ትእዛዙን አክብረን፥ አርአያነቱንም ተከትለን የምንኖር መኾናችንን የምንመረምርበት፥ ለእየራሳችንም ኾነ፡ ለእርሱ፡ በግብር ፈጽመን የምናሳይበት ሳምንት ነው።

ከሕማማት ሰኞ ጀምሮ እስከጸሎተ ሐሙስ ድረስ፡ በጸም ተወስነን፡ በቤተ ክርስቲያን የምናካሂደው፡ የጸሎት÷ የስግደት÷ የጎጽበተ እግርና የቅዳሴ ሥርዓት፤ በእየቤታችንም፡ በጸሎተ ሐሙስ ማታ የሚዘረጋው ገበታ÷ በዚያም፡ የምንሳተፈው ኅብስት (ዳቦው)፡ ይህንና የአሪቱን የፋሲካ ቂጣ ያስታውሰናል። በተለይም፡ "ጕልባን"፡ ተብሎ የሚዘጋጀው ንፍሮ፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከጌቴሴማኒ የተከል ቦታ ጀምሮ፡ እስከመቃብሩ ድረስ፡ በተቀበላቸው የተለያዩና የበዙ ታላላቅ መከራዎች፡ የሥጋው አካል፡ እንደዚህ፡ በእሳት እንደሚከከው ቅይጥ እህል፡ መጕሣቈሉን ለማዘከር፡ በኀዘን የምንቀምሰው፡ ምግብ ነው።

፪. ዕለተ ዓርብ - ስቅለት፦ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሐሙስ ማታ ተይዞ÷ የአይሁድ ሊቃነ ካህናት÷ ሊቃውንትና የሕዝቡ ሽማግሌዎች፡ በሸንጎቸው ተሰብስበው፡ ሌሊቱን ሙሉ፡ ሲከስሱትና ሲወቅሱት ካደሩ በኋላ፡ በመጨረሻ፡ በመስቀል ስቅላት እንዲቀጣ፡ የበኩላቸውን ፍርድ ሰጥተው፡ ለፍርዱ አፈጻጸም፡ ወደሮማዊው ገዢ፡ ወደጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት። አረማዊው ጲላጦስም፡ ምንም እንኳ፡ የሞትን ፍርድ እንዲፈጽምበት፡ "ወንጀለኛ" ተብሎ፡ የቀረበለት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሚነገርበት ክስና ውቅስ ኹሉ፡ ፍጹም ንጹሕ መኾኑን ቢያረጋግጥም÷ ከዚህም የተነሣ፡ *"እኔ ከዚህ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ!"* ብሎ፡ እጆቹን፡ በአደባባይ ቢታጠብም÷ በምንም መንገድ ሊያድነው፡ ባለመቻሉ፡ በግፍ ይሰቅሉት ዘንድ፡ *"ደሙ፡ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይኹን!"* (ማቴ. ፳፯፥፳፭) ላሉት ከሳሾቹ፡ መልሶ ሰጥቷቸው ገደሉት፤ አስገደሉት።

ይህም ኹሉ የኾነው፡ ጲላጦስ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ሊለቅቀው ፈልጎ፡ ነገር ግን፡ ከሳሾቹን ለማስደሰት÷ ሥጋዊና ምድራዊ ሥልጣኑንም ለማቆየት ሲል፡ ከሕግ ውጪ፡ በግፍ ካስገረፈውና በዚያ ወቅት፡ በሮማውያን አገዛዝ ላይ ዐምፆ፡ የታሠረውን፡ "በርባን" የተባለውን ነፍሰ ገዳይ፡ በፍርድ አስወግዶ፡ ይኸኛውን ንጹሑን አስረኛ፡ በምሕረት ሊፈታው ሞክሮ፡ ሳይሳካለት ከቀረ በኋላ ነበር።

ጌታ፡ በዕለተ ዓርብ የተቀበላቸው የመስቀል መከራዎች፡ በግፈኛ ወንጀለኛ ላይ እንኳ፡ "ይደርሳሉ!" ተብለው የማይታሰቡ ናቸው፤ ምንም በደል÷ ጥፋትና ኃጢአት እንደሌለበት፡ ከሳሾቹም÷ ፈራጁም፡ ልቦናቸው እያወቀ፡ ይህን ያህል፡ ለምን ጨከኑበት? ይሙት በቃ የተፈረደበት፡ ነፍሰ ገዳዩ በርባን ተፈትቶ፡ የተራበ አጥጋቢና የተጠማ አርኪ÷ አካል አልባሽና ሕሙም ፈዋሽ÷ የእሥራት ፈቺና የባርነት ነጻ አውጪ÷ ሙት አሥነሽና ነፍስ አዳኝ የኾነው፡ የሕይወት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ይሰቀል!" ብሎ መፍረድና ፍርዱን በአስቸኳይ መፈጸም፡ ምን ማለት ነው? ቅድስት ነፍሱ፡ ከቅድስት ሥጋው ከመለየቷም በፊት፡ ገና፡ በመስቀል ላይ እየተሠቃየ ሣለ፡ የተራቡትን ያጠገበና የተጠሙትን ያረካ፡ ያ፡ ርኅሩኅና ቸር ጌታ፡ በድርቀት የተሰነጣጠቀ ጕረሮውን ለማርጠብ ፈልጎ፡ አንዲት የውኃ ጠብታን ቢጠይቅ፡ ያች፡ የውኃ ጠብታ እንኳ ተነፍጋው፡ መራራ ሓሞትን፡ በሰፍነግ ሞልተው፡ አፉ ላይ መጭመቅ፡ ምን ዓይነት ጭካኔ ነው?

ሰብአዊው ፍጡር፡ ለእርሱ ሊከፍለው የሚገባው ውለታ፡ ከቶ ይህን የመሰለውን ሊኾን ይገባ ነበርን? አልነበረም። ነገር ግን፡ በክፋት ጠንቅ፡ እንዲህ፡ ከመጨረሻው የጉሥቍልና ዐዘቅት ውስጥ የወደቀውን፡ ይህንኑ፡ ጨካኙን ሰብአዊ ፍጥረት ለማዳን የሚቀርበው ቤዛ፡ በዚህ መልክ ተገልጸ፡ መሠዋት ነበረበት።

ታዲያ፡ ዛሬ ያለነው የሰው ወገኖች፡ "በዚያ ዘመን የነበሩ አይሁድና ሮማውያን፡ በጌታ ላይ እንዲህ አደረጉ!" እንላለን። ይኹን እንጂ፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"እውነት እላችኋለሁ! ከኹሉ ከሚያንሱ፡ ከእነዚህ ወንድሞቼ፡ ለአንዱ እንኳ ያደረጋችሁት በጎ ሥራ፡ ለእኔ አደረጋችሁት! ካላደረጋችሁትም፡ ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም"* እንዳለው፡ እኛስ፡ በሌሎች ላይ ምን እያደረግን እና/ወይም እያላደረግን ነው?[ደግ]

እርሱ፡ እኛን፡ የቃል ኪዳን ወገኖቹን፡ ከዲያብሎስ ገዢነት ነጻ አውጥቶ፡ ከኃጢአት ቀንበር ፈትቶና ከሞት ቍራኝነት አላቅቆ፡ ለዘለዓለማዊው ደኅንነት ያበቃን፡ እንዲህ ባለው፡ የመስቀል መከራዎቹ ስለኾነ፡ "እኛስ፡ ዛሬ፡ እርሱን፡ በፍጹም ፍቅር ወድደነው፡ ድምፁንም፡ በእውነት ሰምተንና ቃሉቹን ተከትለን፡ ከእርሱ፡ በቃል ኪዳን የተቀበልነውን ሃይማኖትና ምግባር እየፈጸምን፡ በከፈተልን ሕይወት እንኖራለን ወይ? በእርግጥ፡ እየኖርነው ከኾነ ደግሞ፡ ከዚህ የተነሣ፡ የሚደርስብንን ፈተናና መከራ፡ እንዴት ነው እየተቀበልነው ያለነው?" ብለን፡ እየራሳችንን መመርመር ይኖርብናል።

በዚህ ዓለም፡ በእርሱ አምነውና የእርሱን ፈለግ ተከትለው የሚኖሩ ኹሉ፡ ምንም በጎ ሥራ ቢያደርጉ፡ የሚመለስላቸው ውለታ፡ ይህን የመሰለው ፈተናና መከራ መኾኑን ያውቁታል፤ እርሱ፡ በመስቀል ላይ እየተሠቃየ ሣለ፡ *"አባት ሆይ! የሚያደርጉትን አያውቁምና፡ ይቅር በላቸው!"* ሲል፡ ያሰማው የዕርቅ ቃል፡ ዘወትር በጆሮአቸው እየደወለ፥ እንዲሁም፡ *"በዓለም ሣላችሁ፡ መከራ አለባችሁ! ነገር ግን አይዟችሁ! እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ!"*[የማ] ብሎ በሰጣቸው ቃል እየተጽናኑ፡ ከክፉዎች ሰዎች የሚመጣባቸውን ማናቸውንም ፈተናና የሚደርስባቸውን መከራ፡ በትእግሥት በመቀበል፡ ተጋድሎአቸውን ይቀጥላሉ። በተለይ በዕለተ ዓርብ የምንጸመው ጾም፥ የምንጸልየው ጸሎትና የምንሰግደው ስግደት፡ በዚህ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ካልኾነ፡ ፋሲካችንም፡ እርሱ በመኾኑ፡ የምንፈስከው፡ በዶሮ፡ ወይም በበግ፡ ወይም በበሬ ሥጋ ሳይኾን፡ በእርሱ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ካልኾነ፡ ድካማችን ኹሉ ከንቱ ይኾናል።

ዓርብ፡ ወደስግደቱ መጨረሻ ግድም፡ ቀሳውስቱ፡ የወይራ ቀምበጥ፡ በቀኝ እጃቸው ይዘው፡ ከቤተ ልሔም ወጥተው ይመጣሉ። የዚህ ምሳሌ፡ ኖኅ፡ በጥፋት ውኃ ጊዜ፡ የውኃውን ሙላት መጉደልና የምድሪቱ የብስ መታየቱን አረጋግጣ እንድትመለስ፡ ርግብን፡ ከመርከቡ አውጥቶ በላካት ጊዜ፡ የወይራ ቀምበጥ፡ በአፏ ይዛ መጥታ፡ ያበረከተችለትን ምሥራች የሚያስታውስ ነው።

ቀሳውስቱም፡ በዚሁ መልክ፡ "በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል፡ ዲያብሎስ ታሠረ! ኃጢኣት ተደመሰሰ! ሞት ተወገደ! የሰው ልጅ ነጻ ወጣ! ከእንግዲህ ወዲህ፡ ሰላምና ደስታ ኾነ!" እያሉ፡ የምሥራቹን፡ ለሕዝቡ መንገራቸው ነው። ለእያንዳንዱ ምእመን፡ የንስሓ ስግደት በሚሰጠበት ጊዜም፡ ጀርባውን፡ በምሥራቹ የወይራ ቀምበጥ የሚጠበጥቡት፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንተን/አንቺን፡ ለኃጢኣት ስርየት ያበቃህ/ ያበቃሽ፡ እንዲህ ተገርፎና የመስቀል መከራዎችን ተቀብሎ መኾኑን በማስታወስ ስገድ/ስገጂ!" ማለታቸው ነው።

፫. ገብረ ሰላም፡- የሰንበት ፈጣሪዋና ጌታዋ የኾነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰውነቱ ሞቶ ሣለ፡ ሥጋውን፡ በመቃብር አሳድሮ፥ ነጻነትንም፡ ለማወጅ፡ በነፍሱ ወደሲያል ወርዶ ያሳለፋት፡ የሰሙነ ሕማማት ቅዳሜ፡ "ቅዳሜ ስውር" ተብላለች፤ በዚያን ጊዜ ብቻ፡ የሰንበት ጌታ እርሱ፡ በሥጋው ሞቶ፡ በመቃብር ያሳለፋት ስለኾነች፡ ዕለቷ፡ "ከሰንበትነቷ ተሽራለች!" ለማለት ነው፤ እንደእውነቱ ግን፡ በዕለቷ የኾነውን መለኮታዊ ድርጊት፡ አስተውለው ሲመለከቱት፡ ጌታ፡ በመቃብር ውስጥ፡ በሥጋው ያረፈባት በመኾኗ፡ ***የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አሰብ!*** በምትለው፡ በዓሠርቱ ቃላት መሠረት፡ ዕለቲቱን አከበራት እንጂ፡ አልሻራትም።

ሳምንቱም፡ ለጌታ ክብር ስለተሰጠ፡ በሕማማቱ ሰሞን፡ የሙታን፡ ጸሎተ ፍትሓት አይደረግበትም፤ ይህን የመሰለው አገልግሎት፡ ከሕማማቱ አስቀድሞ፥ ወይም፡ ከትንሣኤው ቀጥሎ ባሉት ሳምንታት ይፈጸማል።

"ገብረ ሰላመ በመስቀሉ! ትንሣኤሁ አማሃደ!" - "ጌታ፡ በመሰቀሉ፡ ሰላምን አስገኘልን! ትንሣኤውንም በገሃድ ገለጠልን!" እያሉ፡ ካህናቱ፡ በዚህች የቅዳሜ ዕለት፡ ቁጠማ ይዘው፡ ለሕዝበ ክርስቲያን በማደል፡ ምሥራቹን ያሰማሉ፤ ያደርሳሉ።

ፍኖ፡- ጸመ ድኅነት።

የአይሁድ ሊቃነ ካህናት፡ የሰውን ልጆች፡ ከዲያብሎስ ገዢነት፥ ከኃጢኣት ቀንበርና ከሞት ፍዳ ያድን ዘንድ፡ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፡ ከድንግል ማርያም ሰው በኾነው፡ በእግዚአብሔር ወልድ ላይ፡ በቅንዓት ተነሥተው፡ እንዴት ሊያጠፉት እንደሚችሉ ሲመክሩ ከቆዩ በኋላ፡ በሮማውያን እጅ አስገድለው ሊያስወግዱት የወሰኑባት ቀን፡ የሕማማት ***ረቡዕ*** ነበረች፤ በዚያ ውሳኔያቸው መሠረት፡ ተቃዋሚዎቹ፡ ለአረማውያኑ መንግሥት አሳልፈው የሰጡት፡ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የመስቀል መከራዎቹን ፈጽሞ፡ የመሥዋዕትነት ደሙን ያፈሰሰባትና የሞት ጽዋውን የተቀበለባት ዕለት፡ የሕማማት ***ዓርብ*** ነበረች። እነዚህ ኹለት ዕለታት፡ ለፍጥረቱ መዳን፡ መታሰቢያ ቀኖች ኾነውና ከበዓለ መንፈስ ቅዱስ (በዓለ ሃምሳ) እሑድ ቀጥሎ ያሉት፡ የ"ረቡዕ" እና የ"ዓርብ" ቀኖቻቸው፡ "**ጸመ ድኅነት**" በሚል ስያሜ ታውቀው፡ ለየብቻቸውም ኾነ፡ ከሌሎቹ አጽዋማት ጋር ተደርበው፡ በየሳምንቱ ይጸማሉ።

፮ኛ፦- ጾመ ሐዋርያት::

እውነተኛውና ዘለዓለማዊው ሙሽራ ኢየሱስ ክርስቶስ: የሙሽርነቱን ተልእኮ: በመስቀል ላይ ፈጽሞ÷ ሞቶና ተቀብሮ: ከመነሣቱና ከማረጉ በፊት: ስለደቀ መዛሙርቱ: *"ሙሽራው: ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ይጦማሉ!"* ብሎ በተናገረላቸው ቃል መሠረት: ሐዋርያት: ከእርሱ በኋላ÷ በተለይም: በበዓለ ሃምሳ ዕለት: መንፈስ ቅዱስ ከወረደላቸው በኋላ: ተልእኳቸውን ለመፈጸም ከመለያየታቸው በፊት: የጠሙት ጾም: "ጾመ ሐዋርያት" ተብሏል:: እርሱም: ከበዓለ መንፈስ ቅዱስ (በዓለ ሃምሳ) እሑድ ቀጥሎ ካለው ሰኞ ጀምሮ: በሐምሌ ፭ ቀን ያበቃል:: ኢትዮጵያውያን: የሐዋርያትን ፈለግ በመከተል÷ ራሳቸውንም: ለኢየሱስ ክርስቶስ ሕያዋን ሐዋርያት አድርገው በማቅረብ: ይህን የሐዋርያት ጾም: በሐዋርያት መንፈስ ይጸሙታል::[ደ፵፪]

፯ኛ፦- ጾመ ፍልሰታ::

ከነሐሴ ፩ እስከ፲፭ ቀን ድረስ የምትቆየው ጾም: "ጾመ ፍልሰታ" ትባላለች:: በክረምት ወራት ስለሚፈጸሙት ባህሎቻችን: ትዝ ከሚሉን መካከል: ዋናዋ: ይህች ጾም ኾና ትገኛለች:: ይህችን ጾም: ካህናት: ትላልቆች ወንዶችና ሴቶች÷ ብላቴኖችና ልጆች ብቻ ሳይኾኑ: ሕፃናት ጭምር እየጾሙ÷ እያስቀደሱና እየቆረቡ: በቤተ ክርስቲያን የሚያሳልፉት: የ፲ሱለት ሳምንት የሱባዔ ጊዜ ነው::

በዚህ የጾም ሰሞን: የእናታችንና የንግሥታችን: የቅድስት ድንግል ማርያም: ዜና ልደቷ÷ ሕይወቷና ዕረፍቷ÷ እንዲሁም: እግዚአብሔር: እርሷን ምክንያት አድርጎ: ራሱን: ለፍጥረቱ የገለጸበትና ፍጥረቱን ያዳነበት: የሥጋዌው ምሥጢር ተብራርቶ ይነገርበታል:: ቅዱሳን ሐዋርያት: ይህን ሱባዔ: ለምን እንደጀመሩት÷ በዓመቱም እንዴት እንደቀጠሉት: ታሪኩ ይወሳል:: በዚያም ውስጥ: ተካትተው ከሚቀርቡት: ዋና ዋናዎቹ ድርጊቶች መካከል: የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

፩ኛ: በጥር ፳፩ ቀን ከኾነው ከድንግል ማርያም ዕረፍት በኋላ: አይሁድ በተለመደ ጠላትነታቸው: አስከሬኗን: "እናቃጥላለን!" ማለታቸው÷

፪ኛ: በዚያን ጊዜ ግን: እግዚአብሔር ወልድ ሰው ኾኖ የተፀነሰበት÷ እስኪወለድ የኖረበትና ጠብቶ: በእቅፉ ያደገበት መቅደስ ሥጋዋ: በቅዱሳን መላእክት ተነጥቆ: ወደገነት መወሰዱ÷

፫ኛ: ወንጌላዊው ዮሐንስ: ይህንኑ ምሥጢር ያየ ሲኾን: ሌሎቹ ሐዋርያት ባለማየታቸው: በነሐሴ ፩ ቀን ሱባዔ መግባታቸውና ምሥጢሩ ተገልጠላቸው: ቅዱስ ሥጋዋን: እንደገና ተቀብለው: በነሐሴ ፲፩ ቀን መቅበራቸው÷

፬ኛ: በሦስተኛውም ቀን: እንደልጇ: ከሙታን ተለይታ መነሣቷና በሰኛው ቀን ማረጓ÷

፭ኛ: ይህንኑ ትንሣኤዋንና ዕርገትዋን ለማየትና ምስክር ለመኾን የታደለው: ለጊዜው ሐዋርያው ቶማስ ብቻ መኾኑ÷

፮ኛ፡ ልጇ፡ ለትንሣኤ፡ ቀዳማዊው በኵር ኾኖ፡ እርሷ፡ ለዚያ፡ ለትንሣኤው ብኵርና ዳግማዊትነትና ተከታይነት የበቃችበትን፡ ይህን የመለኮት ድንቅ ኃይል፡ በዚህ ጊዜ ለማየት ከመካከላቸው፡ የታደለው፡ ሐዋርያው ቶማስ ብቻ ስለነበረ፡ "እርሱ፡ ትንሣኤሽንና ዕርገትሽን አይቶ፡ እኛ ለዚህ፡ዕድል፡ እንዴት ሳንበቃ ቀረን?" በማለት፡ የቀሩት ሐዋርያት አዝነው፡ በዓመቱ፡ በነሐሴ ፩ ቀን፡ ለኹለተኛ ጊዜ ሱባዔ መግባታቸው÷

፯ኛ፡ በመጨረሻ፡ ነሐሴ ፲፮ ቀን በሚውለው በትንሣኤዋ መታሰቢያ ዕለት፡ ሐዋርያት፡ ወደሰማያዊቷ የእግዚአብሔር መንግሥት ተነጥቀው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም የምትገኝበትን ክብርና ምስጋና ማየታቸው÷ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡አ እርሷን፡ እናቱን፡ መንበር÷ ራሱን፡ ሠራዒ ቁስ፡ ሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስን፡ ረዳት ካህን÷ ቀዳሜ ሰማዕት እስጢፋኖስን፡ ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ፡ ቀድሶ፡ እነርሱን ማቍረቡ፡ በአርእስት ተከፋፍሎና በዝርዝር ተተንትኖ ይነገራል።

የዚህም ማጠቃለያው፡ *"ቃል ሥጋ ኾነ!"* ማለትም፡ "አምላክ ሰው ኾነ!" የሚለው የሥጋዌ ምሥጢርና በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል ተሰጥታ ቆይታ፡ ወደኢትዮጵያውያን ተዛውራና በአደራ ተጠብቃ የኖረችው ታቦተ ጽዮን፡ ለደሰማያት ተመልሳ የምትገኝበት ምሥጢር የተገለጠ መኾኑ ነው። ይህም፡ *"በሰማይም ያለው፡ የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ! የኪዳኑም ታቦት፡ በመቅደሱ ታየ!"* በሚለው በዮሐንስ ራእይ ተረጋግጧል።[ራእ. ፲፩፡፲፱]

በኢትዮጵያውያን ሕይወት፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ በካህናት÷ በትልልቆቹ ወንዶችና ሴቶች ዘንድ ብቻ ላይኾን፡ በወጣቶቹና በሕፃናቱ ዘንድ ጭምር፡ የእመቤታችን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የእናትነቷና የንግሥትነቷ÷ የአገርነቷም ፍቅር፡ የቱን ያህል የጠለቀና የመጠቀ መኾኑ፡ በይፋ ተረጋግጦ የሚታወቀው፡ በተለይ፡ በዚህችው፡ የፍልሰታ ሳምንታት መኾኑ በገሃድ ይታያል። "ፍልሰቷ"፡ "ከመ' ትንሣኤ ወልዳ!" ማለትም፡ "እንደልጅዋ ትንሣኤ ነው!" ስለዚህ፡ "እንደልጇ ትንሣኤ በዓል አድርገው ያክብሩት!" ሲሉ፡ አባቶቻችን በደነገጉት ውሳኔ መሠረት፡ የፍልሰታዋ በዓል፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እንደልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ በታላቅ ሐሤትና ይባቤ ይከበራል።

፰ኛ. ጾመ ጰጉሜ።

በመስከረም ፩ ቀን ለሚውለው፡ ለእውነተኛው የጌታ የልደት በዓል፡ ሰሙነ ዋዜማ የኾነችውና እስካኹን፡ በፈቃድ ስትጾም የቆየችው ጳጉሜ፡ አኹን ራሷን ችላ፡ ለጌታ የልደት ቀን፡ እንደጾመ ገሃድ÷ ለኢትዮጵያውያኑም፡ "ሰሙነ ሱባዔ" ኾና፡ አዲሱን ዓመተ ምሕረት፡ በንስሓ ተዘጋጅተው ስለሚቀበሉባት ፡ በአግባቡ ትጾማለች።

አምን! መስከረም ፩ ቀን፡ ክፉዉን ኹሉ፡ ካረጀው ዓመት ጋር፡ ከዲዮ ጥለንና ትተን÷ አስወግደንም÷ የእየራሳችንን ኹለንተና፡ ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት፡ በንስሓ አድሰን÷ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም በመወለዱ፡ የተገኘውን፡ ዘለዓለማዊዉን የምሕረት ዘመን፡ እንደአዲስ ተሸላሚ፡ የክብር ልብስና የሕይወት አክሊል ተቀብለን፡ የምንጐናጸፍባትና የምንቀዳጅባት፡ ቅድስት ዕለት ናት።

ከዚህ የተነሣም፡ የጌታችንንና የአመቤታችንን የልደት በዓላት፡ እውነተኛና ተገቢ በኾነው፡ የአምልኮ መንፈስ ለማክበር፡ ነፍሳችንንና ሥጋችንን÷ መንፈሳችንንም፡ በሥጋ ወደሙ ቀድሰን፡ ሰውነታችንን፡ ለቅዱሱ ሕይወት የምናበቃባት÷ "ኢትዮጵያ" ለተባለችው፡ እናቱና እናታችንም፡ "ዕንቊጣጣሽ! (እነሆ፡ ዕንቊ ለጣትሽ!)" ብለን፡ የደስታንና የምስጋናን ገጸ በረከት የምናቀርብባት÷ እርስ በርሳችንም፡ የአበባ ነዶና ጉንጉን አዘጋጅተን፡ "የምሥራች! እንኳን አሸጋገረን! እንኳን አደረሰን!" እያልን፡ መልካም ምኞታችንን የምንለዋወጥባት፡ የተመረጠች ቀን ናት፤ ስለዚህ፡ በዚህ መልክ፡ ከአሮጌው ዓመት፡ ወደአዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባትን ይህችን ጳጉሜን፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ንዑስ ሱባዔ አድርገን፡ በጸም÷ በጸሎትና በምጽዋት እናሳልፋታለን።

እንግዲህ፡ ጾምንና አጽዋማትን በሚመለከት የምሰጣችሁ ሓተታና ምርምር በዚህ ይጠቃለላል። አስተውላችሁ የመመልከቱና ለፍሬ የማብቃቱ ድርሻ፡ የእናንተ ነው።

ጥያቄ፡- ይህን አርእስት ከመዝጋትህ በፊት፡ ከዚህ ጋር የሚሼድ፡ ማለትም፡ እንደጾሙና አጽዋማቱ፡ የኢትዮጵያዊነት ሕይወታችንን የሚያሟላ፡ ሌላ ተጨማሪ ወይም ተመሳሳይ መመሪያ የሚኾን እውቀት ካለ፡ ብትገልጽልን? እንዲያውም፡ ከላይ ቀደም ብለህ፡ ከጾም ጋር አብረው የሚሼዱትን፡ ሰግደትንና ንስሓን በሚመለከት፡ ከአጽዋማቱ ቀጥለህ፡ እያከታተልህ "አነሣቸዋለሁ!" ያልኸንን እንዳትዘነጋው፡ እዚህ ላይ እንድናስታውስህ ትፈቅድልናለህ?

መልስ፡- እንዴታ! ይህን የመሰለው አድራጎታችሁ እኮ፡ የተነሣንበትን የእውቀት ዓላማ፡ በቁም ነገር የያዛችሁት መኾናችሁን፡ ይኸው፡ ለእኔም የሚያረጋግጥልኝ ነው፤ ስለዚህ፡ እንዲህ፡ ማስታወሳችሁ፡ "አበጃችሁ!" የሚያሰኝ ከመኾኑ በቀር፡ ፈቃዱን የሚያስጠይቃችሁ አይደለም።

አዎን! የጾሙንና የአጽዋማቱን ነገር ልጨርስላችሁ ብዬ ነው እንጂ፡ ከዚህ አርእስት ጋር፡ እንደነፍስና ሥጋ ተዋሕደውና ተያይዘው ስለሚኼዱት፡ "ሰግደት" እና "ንስሓ" ስለሚባሉት የሃይማኖት ምግባራት፡ ተገቢውን ሓተታ፡ ባጭሩም ቢኾን አቀርብላችኋለሁ።

ሰግደት።

ጥያቄ፡- ከ"ጾም" በማይለየው÷ በሥጋም አካል፡ ጎልቶና ገዝፎ በሚፈጸመው፡ በ"ሰግደት" ጀምርልና!

መልስ፡- መልካም! "ሰግደት"፡ ከጸምና ጸሎት የማይለይ፡ ሃይማኖታዊና የአምልኮ ምግባር ነው፤ ምክንያቱም፡ በምንጸምበት ጊዜ እንጸልያለን፤ በምንጸልይበትም ጊዜ፡ እንደየዓቅማችን እንሰግዳለን።

ጸሙም፡ ጸሎቱም፥ ስግደቱም፡ ነፍሳችንና ሥጋችን፥ መንፈሳችንም፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አንድ ኾነው፡ ለፈጣሪያቸው የሚያበረክቱት፡ የትክክለኛ አምልኮ መገለጫዎች ናቸው፤ ስለዚህ፡ እንዲህ ኾነው መቅረብ ይኖርባቸዋል። "ስግደት"፡ ነፍሳዊ ብቻ ሳይኾን፡ ሥጋዊ ጠባይ፥ ዓላማና ጥቅምም አለው፡ ይኸውም፡ መንፈስ ቅዱስ የተዋሓዳት፡ ረቂቋ ሰብአዊት ነፍስ፡ በጸም ኃይል እንደምትጠናከር ኹሉ፥ ግዙፉ ሥጋዊ አካልም፡ በዚህ የአምልኮ ስግደትም፡ ጤናማ እንደሚኾን ይታወቃል። ይኸውም፡ ቀጥ ብለን ከምንገኝበት ቁመታችን፡ ወደመሬት ተጎንብሰን፥ በጉልበታችን ተንበርክከንና በግንባራችን ተደፍተን በምንፈጽመው ስግደት፡ ነፍሳችን ብቻ ሳትኾን፡ ግዙፉ ሥጋችን ጭምር፡ ከራስ ፀጕሩ እስከእግር ጥፍሩ ድረስ፡ ከውስጥ የአካል ክፍሎቻችን፡ ሥሮቻችንና ሕዋሳታችን ጋር ስለሚንቀሳቀስ፡ መላው ሰውነታችን ይፋታታል፤ ይዝናናል፥ ይጠናከራል ማለት ነው። በሥጋውያንና በዓለማውያን ሰዎች ዘንድ፡ በየጧቱና ማታው የሚካኼደው፡ የሰውነት ማጠንከሪያ ልምምድ፡ በሃይማኖታውያንም ዘንድ፡ በስግደት አማካይነት፡ ከጸምና ጸሎቱ ጋር አብሮ ስለሚፈጸም፡ ጥንካሬውና ጤንነቱ፥ መዝናናቱም፡ በነፍስና በመንፈስ ብቻ ሳይኾን፡ ሥጋዊውንም ስለሚያካትት፡ የጸም ዓላማውና የስግደቱ ግብ የተሟላ ይኾናል ማለት ነው። ስለዚህ፡ በእውነተኛ ጸምና በመንፈሳዊ አምልኮ ኾነን የምናደርገው ስግደት፡ ከፈጣሪያችን ፊት ደርሰ፡ ለነፍሳችንና ለሥጋችን፡ የሚገባውን የጤንነት፥ የዕድገትና የኃይል ጸጋን የሚያስገኝልን መኾኑን፡ መጠራጠር አይቻልም።

"ስግደት"፡ በእኛ በኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ሥርዓት፡ "የባሕርይ"፡ "የጸጋ" እና "የአክብሮት" ተብሎ፡ በሦስት ይከፈላል።

፩. "የባሕርይ ስግደት"፡ በአንድነትና በሦስትነት ለተገለጸውና ለሚታወቀው፡ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚቀርብ ነው። ለእርሱ፡ ለአንዱ አምላክ ብቻ የሚቀርብ ስለኾነ፡ የ"አምልኮ" ስግደትም ይባላል። እግዚአብሔር፡ ቀድሞ፡ በኢትዮጵያውያን የልብ ጽላት ላይ፡ ኋላም፡ ለእስራኤላውያን፡ በድንጋይ ጽላት ላይ፡ በጣቶቹ ጽፎ፡ "ኢትዮጵያዊነትን" በተቀበለው ሙሴ አማካይነት ከሰጣቸው፡ ከአሥሩ ትእዛዛት መካከል፡ እንዲህ የሚሉት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ አምላካውያት ቃላት፡ ለዚህ እውነታ ማረጋገጫዎች ናቸው፡-

የመጀመሪያው፡ የብሉዩ ኪዳን አራታዊ ቃል፡ *"ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ነጻ ያወጣሁህ፡ እግዚአብሔር አምላክህ፡ እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር፡ ሌሎች አማልክት አይኹኑልህ! በላይ፡ በሰማይ ካለው፥ በታችም፡ በምድር ካለው፡ ከምድርም በታች፡ በውኃ ካለው ነገር፡ የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ! አትሰግድላቸው! አታምልካቸውምም! በሚጠሉኝ ዘንድ፡ እስከሦስተኛና እስከአራተኛ ትውልድ ድረስ፡ የአባቶችን ኃጢአት፡ በልጆች ላይ የማመጣ፡ ለሚወድዱኝና ትእዛዜን ለሚጠብቁ ግን፡ እስከሺህ ትውልድ ድረስ፡ ምሕረትን የማደርግ፡ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ፡ ቀናተኛ አምላክ ነኝ።"* የሚል ሲኾን፡ የመጨረሻው፡ የአዲስ ኪዳኑ የምሥራች ቃል ደግሞ፡ *"እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡ የሚሰግዱለትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።"* የሚለው ነው።

"አምላካችን ነው!" ብለን፡ በሃይማኖት ለተቀበልነውና ወድደን ለምናመልከው እግዚአብሔር፡ የምንሰግደው ስግደት፡ በሥጋችን ብቻ ሳይኾን፡ በነፍሳችንና በመንፈሳችን ጭምር መኾን አለበት። ይህንም ስናደርግ፡ "እነዚህ ሦስቱ፡ የሰውነታችን ባሕርያት፡ ማለትም፡ ሥጋችንና ነፍሳችን፥ መንፈሳችንም፡ እያንዳንዳቸውም፥ ኹሳቸውም፡ ከአንተ የተገኙ፡ አንተ የፈጠርሃቸው ናቸው፤ ስለዚህ፡ ኹለንተናችን የአንተ ነው!" ብለን በማመን፡ እኛ፡ ፍጡራኑ መኾናችንን፥ እርሱም፡ ፈጣሪያችን መኾኑን፡ ለእርሱ ለፈጣሪና ለእየራሳችን፥ ለሌላውም ፍጥረት ኹሉ በይፋ ለመንገር፡ ለማሳወቅና ለመመስከር ነው።

"እስራኤል ሆይ! ስማ! እግዚአብሔር አምላክህ፡ አንድ ነው። አንተም፡ በልብህ ኹሉ፥ በነፍስህም ኹሉ፥ በአሳብህም ኹሉ፥ በኃይልህም ኹሉ፡ እግዚአብሔር አምላክህን ውደድ!" የሚለውን፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ተከትለን፡ እግዚአብሔርን፡ በሃይማኖት የተቀበልነውና ወድደነው የምናመልከው፡ *በፍጹም ልባችን፥ በፍጹም ነፍሳችንም፥ በፍጹም አሳባችንም፡ በፍጹም ኃይላችንም* መኾኑን፡ ዘወትር፡ ለእየራሳችን፡ በእየልቦናችን ማረጋገጥ ይኖርብናል።[ገ፵፬]

ከዚህ የተነሣ፡ ስግደታችን፡ የእርሱን ፈጣሪነትና የእኛን ፍጡርነት ብቻ ሳይኾን፡ የእርሱን የበላይነትና የእኛን የበታችነት፥ የእርሱን ታላቅነትና የእኛን ታናሽነት፡ የእርሱን አዛዥነትና የእኛን ታዛዥነት፥ የእርሱን ኃያልነትና የእኛን ደካማነት፡ የእርሱን አዳኝነትና የእኛን ጠፊነት፥ የእርሱን ጻድቅነትና የእኛን ኃጢኣተኛነት፡ የእርሱን መሓሪነትና የእኛን በዳይነት፥ የእርሱን ንጉሥነትና የእኛን ዜጋዊነት፥ በመጨረሻም፡ የእርሱን አባትነትና የእኛን ልጅነት የምናረጋግጥበት ሥርዓት መኾኑን እንገነዘባለን።

"ወላዲተ አምላክ"፡ "እመ አምላክ"፥ "ምስለ ፍቁር ወልዳ"፡ ማለትም፡ "አምላክን የወለደች"፥ "የአምላክ እናት"፥ "ከተወዳጅ ልጇ ጋር" ተብላ፡ ሕፃን ልጇን እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በክንዶቿ እንዳቀፈች፡ በልቦናችን ጽላት ላይ ተሥላ፡ በዓይነ ሕሊና ለምናያት፥ በሰሌዳም ላይ ተሥላ፡ በዓይነ ሥጋ ለምንመለከታት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የምናቀርበው ስግደት፡ "የባሕርይና የአምልኮ ስግደት" ኾኖ መቅረብ ይኖርበታል። ምክንያቱም፡ በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ምን ጊዜም፡ እናትና ልጇ አብረው ያሉና የሚሣሉ እንጂ፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ ለብቻዋ፥ ልጇን፡ ኢየሱስ ክርስቶስንም፡ ለብቻው ሥሉ የማቅረብ ባህል የሌለን በመኾኑ ነው።

ይህ ጉዳይ፡ ሃይማኖትንና አምልኮን የሚመለከት ስለኾነ፡ **እናንተም፡** እውነታውን፡ በትክክል ልታውቁት፥ ድርጊቱንም፡ በብርቱ ልትጠነቀቁበት ይገባችኋል። ይህም፡ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ተሰቅሎ ከሚታይበት የሥነ ስቅለት ቅርጽና ከመስቀሉ ምልክት በቀር ማለት ነው።

በሥዕል ሲኾን ግን፡ በመስቀሉ ቀኝ፥ እርሷ እናቱ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፥ በመስቀሉ ግራም፡ "ፍቁረ እግዚእ"፡ ማለትም፡ "ጌታ የሚወድደው" የሚባለው፡ ደቀ መዝሙሩ ዮሐንስ፡ ተሥለው ሊታዩበት ይገባል። በዚህ ረገድ፡ ይህ ኹሉ መባሉ፡ በቤተ ክርስቲያንና በአምልኮ ቦታ ተሰቅሎ፡ ለሚሰገድለት ሥዕል፡ ተገቢው የአምልኮ ጥንቃቄ እንዲደረግ ለማሳሰብና ለማስጠንቀቅ ነው።

ከዚህ በቀር፡ ለማስተማሪያና ለምንባብ በሚዘጋጀው ጽሑፍና ዕትም ውስጥ፡ እናትና ልጇ፡ ለየብቻም ኾነ በተለያየ መልክ ተሥለው ሊቀርቡ አይችሉም ለማለት አይደለም። ይኹን እንጂ፡ ከዚህ ውጪ፡ እመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ለብቻዋ ኾና፥ ልጇ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለብቻው ኾኖ ተሥለው የሚታዩበት የሥዕል ሰሌዳ፡ የእኛ የኢትዮጵያውያን ባህል አለመኾኑን ልትገነዘቡት፥ እንዲያውም፡ የሥዕላቸው መልክ፡ ኢትዮጵያዊ ሊኾን ወዝና ቀለም ይዞ የማይገኝ ከኾነ፡ ያ፡ በሌላ መልክ ኾኖ የተዘጋጀው ሥዕላቸው፡ የባዕዳን መኾኑን ልታውቁት፡ ይህም ኹሉ፡ ሃይማኖትንና አምልኮን የሚመለከት ስለኾነ፡ ተገቢውን ጥንቃቄ ልታደርጉበት ያስፈልጋችኋል፡ ይገባችኋልም።

፪. "የጸጋ ስግደት" የሚባለው፡ ለቅዱሳን ጻድቃን፡ ስማዕታትና መላእክት፡ የሚቀርበው ስግደት ነው። "ጸጋ" በግእዝ፡ የሚሰጥና የሚነሣ፡ ተመልሶ ሊወሰድ የሚችልም "ሰጦታ፡ ወይም ችሮታ" ማለት ነው።

ይህን ዓይነቱ ስግደት፡ የአምልኮ፥ ወይም የባሕርይ አይደለም ማለት ነው፡ የአምልኮ ስግደት የሚደረግለት፡ በፍጡራኑ መመለክ ለሚገባውና ባሕርዩ ለኾነው፡ ለአንዱ አምላክ፡ ለእግዚአብሔር ብቻ ሲኾን፡ እኒህ ቅዱሳን ግን፡ ለእርሱ፡ ለአንዱ ፈጣሪያቸው፡ በሃይማኖታቸውና በምግባራቸው ባሳዩት፡ ፀፈተና ጠርቶ በተዋጣለት፡ ፍጹም ታማኝነታቸውና እውነተኛ አገልግሎታቸው፡ ከመጨረሻው ብቅዓት ስለደረሱ፡ "በእርሱ ዘንድ፡ ልዩ ሞገስንና የባለሟልነትን ክብር አግኝተዋል!" ብለን፡ እናከብራቸዋለን።

ስለዚህ፡ ይህን የመሰለው ክብርና ሞገስ፡ ጸጋ ኾኖ፡ ከፈጣሪያቸው ስለተሰጣቸው፡ ይህ በመለኮታዊው ሹመት፡ እንደዘውድ የተቀዳጁት ጸጋ፡ በሌሎቹ ፍጡራን ወገኖቻቸው ዘንድ፡ እንዲከበሩና እንዲሰገድላቸው አድርጓቸዋል። ሲከበሩና ሲሰገድላቸውም፡ ከእግዚአብሔር፡ በሹመት በተቀበሉት የባለሟልነት ጸጋ፡ ሊከብሩበትና ሊወደሱበት እንጂ፡ ከባሕርያቸው በተገኘ ክብር ባለመኾኑ፡ ምእመኑ፡ ለእነርሱ በሚሰግድበት ጊዜ፡ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት፡ ሊያውቅ ይገባዋል፡ ለእነርሱ የሚያቀርበው ስግደት፡ ጸጋ ኾኖ፡ በመንፈስ ቅዱስ በተሰጣቸው፡ የባለሟልነት ክብርና ሞገስ፡ ሊያከብራቸው፥ በባለሟልነታቸውም፡ ከፈጣሪያቸው ሊያማልዱት ብቻ መኾኑን መዘንጋት የለበትም።

፫. "የአክብሮት ስግደት"፡ ከወላጆቻችንና ዘመዶቻችን ጀምሮ፡ ለታላላቆቻችንና ለአስተማሪዎቻችን፥ በሥጋና በነፍስ እንዲጠብቁንና እንዲያገለግሉን፡ ከእግዚአብሔር ተሠይመው ለተሰጡን፡ መንፈላውያንና ሥጋውያን ባለሥልጣን አገልጋዮቻችንም፡ እጅ በመንሣት፡ የምናቀርበው ሲኾን፡ እርሱም፡ "የአክብሮት ሰላምታ" ይባላል።

የእጅ አነሣሡም መጠን፡ እንደአክብሮቱ ይለያያል፤ ለእኩያ፡ አንገትን ቀለስ በማድረግ ሲኾን÷ በዕድሜ ለሚበልጥ፡ ከወገብ ዝቅ በማለት÷ ለትልቅ ሰውና ለባለሥልጣን፡ በግማሽ ሰውነት፡ በማጐንበስ÷ ለአረጋውያን፡ ወረድ ብሎ፡ ጒልበትን በመሳም÷ ለአዛውንት አባቶችና እናቶች÷ ለተቀባ ያገር መሪ እስከመሬት ደርሶ፡ ጫማ በመሳም ይፈጸማል።

የአምልኮውና የጸጋው ስግደት ኾነ፡ የአክብሮት ሰላምታው፡ ኹሉም፡ የሚቀርቡት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በምሴተ ሐሙስ፡ የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብ ባሳየውና ባስተማረው፡ በፍጹም ትሕትና ላይ በተመሠረተ መንፈስና ኹኔታ መኾን ይገባቸዋል። በእየልቦናችን ውስጥ ኾነ፡ በሰሌዳ ላይ ተሥለው፡ በዓይነ ሕሊናም ኾነ በዓይነ ሥጋ ለምናያቸው፡ ለሥላሴ÷ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለምስለ ፍቁር ወልዳ (ሕፃን ልጇን እንደታቀፈች ለምትታየው፡ ድንግል ማርያም)፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ከምናቀርበው፡ የባሕርይ ስግደት በቀር፡ ቀደም ብዬ፡ በኹለተኛውና በሦስተኛው ተራዎች የጠቀስኋቸውን፡ ለቅዱሳንና ለታላላቆቻችን የምናበረክታቸውን የጸጋ ስግደትና የአክብሮት ሰላምታ፡ በእንዴት ያለ መልክ ልንፈጽማቸው እንደሚገባን፡ እያስጠነቀቀ የሚያስረዳን መልአካዊ ቃል አለ።

ይህም፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ ለዮሐንስ የተናገረውና ይኸው ወንጌላዊ፡ በራእዩ የጻፈው፡ እንዲህ የሚለው ቃል ነው፡- *"ይህንም ያየሁትና የሰማሁት፡ እኔ፡ ዮሐንስ ነኝ። በሰማሁትና ባየሁትም ጊዜ፡ ይህን ባሳየኝ፡ በመልአኩ እግር ፊት፡ እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ። እርሱም፡ 'እንዳታደርገው ተጠንቀቅ! ከአንተ ጋር፡ ከወንድሞችህም፡ ከነቢያት ጋር፡ የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር፡ አብሬ ባሪያ ነኝ። ለእግዚአብሔር ስገድ!' አለኝ።"*[የሮሜ ፪፥፲]

በአምልኮቱና በጸጋው ስግደት፡ በአክብሮቱ ሰላምታም ጊዜ፡ የነጠላው አለባበስና ድግድጋት፡ ይለያያል። ያም ሥርዓት፡ አግባብ በኾነው ጊዜና ቦታ ይብራራላችኋል።

ንስሓ።

ጥያቄ፡- የሰግደትን ነገር፡ በዚህ ከጨረስህ፡ የ"ጸም" እና የ"ስግደት" ፍሬ ስለኾነው፡ ስለ"ንስሓ" አያይዘህ ቀጥልልና!

መልስ፡- መልካም! ስለንስሓ፡ በሚቀጥለው፡ የዚህ መጽሐፍ ክፍል ውስጥ፡ በሚበቃ ተብራርቶ ታገኙታላችሁ። ለእኹኑ ጥያቄያችሁ፡ መልስ እንዲኾናችሁ ያህል ግን፡ የሚከተለውን አጭር መግለጫ እሰጣችኋለሁ።

የጸም እና የስግደት ግቡና ውጤቱ ንስሓ ነው። ንስሓም ማለት፡ በእውነተኛ ጸምና የአምልኮ መንፈስ ኾነን፡ በፈጣሪያችን ፊት በምንሰግድበት ጊዜ፡ አፍአዊና ውሳጣዊ ኹለንተናችንን፡ እኛው እየራሳችን ከምናውቀው በላይ ለሚያውቀን፡ ለእውነተኛው ካህንና ሊቀ ካህናት፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ በመናዘዝ÷ ያለማቋረጥ የምናካኺደው ግንኙነት ነው።

ይህንም ስናደርግ፡ ባለፈው ስለሠራነው ኃጢአትና ስለፈጸምነው በደል፡ እያዘንና እየተጸጸትን፥ ለወደፊቱም፡ የእግዚአብሔር እርዳታ እንዳይለየን ከመማጠን ጋር፡ ክፋትንና ተንኰልን፥ ሌላውንም ፍትወትና መጥፎ ልማድ የኾነውን ሱስ ኹሉ፡ ከእየኀሊናችንና ከእየሰውነታችን፡ በተቻለ መጠን አስወግደን፥ ከሚመጣው የኃጢአት ፈተናም፡ እየራሳችንን ለመጠበቅ፡ በየበኩላችን፡ በቁርጥ የወሰን መኾናችንን በማረጋገጥ ሊኾን ይገባል።

ንስሓችን የሠመረ ኾኖ፡ በፈጣሪያችን ፊት፡ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ፡ ከተቀያየየምነው፡ ማለትም፡ ከበደለን፥ ወይም፡ ከበደልነው ሰው ጋር በግንባር፡ ያም ባይቻል፡ በቃልና በመልእክት ተቀራርበን፥ በዚህ መልክ፡ ልናገኘው ባንችል እንኳ፡ ከእየልቦናችን፡ ቂምና በቀልን በማስወገድ፡ አስቀድመን ራሳችንን፡ ከሌላው ጋር አስታርቀን መቅረብ ይኖርብናል፥ በዚህ ጊዜ፡ እንዲህ የሚለውን፡ የመምህራችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ተከትለን መፈጸማችንን እናረጋግጣለን፡- *"ለሰዎች፡ ኃጢኣታቸውን ይቅር ብትሉ፡ የሰማይ አባታችሁ፡ እናንተን ደግሞ፡ ይቅር ይላችኋልና፥ ለሰዎች ግን፡ ኃጢኣታቸውን ይቅር ባትሉ፡ አባታችሁም፡ ኃጢኣታችሁን፡ ይቅር አይላችሁም!"* *"እንግዴህ፡ መባህን፡ በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፡ በዚያም፡ ወንድምህ፡ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፡ በዚያ፡ በመሠዊያው ፊት፡ መባህን ትተህ ሺድ! አስቀድመህም፡ ከወንድምህ ጋር ታረቅ! በኋላም መጥተህ፡ መባህን አቅርብ!"*

በአጠቃላይ፡ በስግደታችን ጊዜ፡ "አቤቱ አምላኬ! እኔን በደለኛውን ደካማ ፍጡርህን፡ ኃጢኣቴንና በደሌን ኹሉ፡ ይቅር በለኝ!" እያልን፡ ያለማቋረጥ መጸለይን መዘንጋት የለብንም።[የግርጌ]

ጾም፥ ጸሎትና ስግደት የሚያጅቡት፡ ይኸው "ንስሓ"፡ እንደመስታወት ነው፥ መስታወት፡ እኛው ራሳችን፡ እየራሳችንን፡ በእየራሳችን፡ ልናየው ያልቻልነውን ሥጋዊ አካላችንንና በላዩ ያለውን ጉድፍ፡ አጥርቶና አጉልቶ እንደሚያሳየን ኹሉ፡ "ንስሓ"ም፡ በውሳጣዊው የኅሊና ዓይናችን ሳይቀር ልናየው ያልቻልነውን፡ በአፍአዊውም ኾነ በረቂቋ ነፍሳችን ውስጥ የተከማቸውን የኃጢኣት ጉድፍ፡ ገላልጦና እንደግንድ አግዝፎ፡ በማሳየት፡ ምንነታችንን፡ በገሃድ የሚያሳውቀን፡ መንፈሳዊ ማጉያ መነጽር ነው። አምን! "ንስሓ"፡ *"ባወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ፡ ለምን ታያለህ? በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ፡ ለምን አትመለከትም? ወይም፡ ወንድምህን፡ 'ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ፡ ፍቀድልኝ!' እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆም፡ በዓይንህ ምሰሶ አለ። አንተ ግብዝ! አስቀድመህ፡ ከዓይንህ፡ ምሰሶውን አውጣ! ከዚያም በኋላ፡ ከወንድምህ ዓይን፡ ጉድፉን ታውጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።"*[የግርጌ] የሚለውን መለኮታዊ ቃል፡ እንድናውቀው ብቻ ሳይኾን፡ እውነተኛነቱን ተገንዝበን፡ በምግባር እንድንፈጽመው የሚያደርገን፡ መንፈሳዊ ኃይል ነው። በፈጣሪያችን ፊት፡ በእየግላችን ከምናቀርበው፡ ከዚህ ንስሓችን ጋር፡ በመምህረ ንስሓ ምክር፡ ዓቅም በሚፈቅደው መጠን የሚፈጸም፡ የቀኖና ጾምና ስግደት፡ ጸሎትና ምጽዋት መኖሩንም ልታውቁት ይገባል።

ይህ፡ የሃይማኖታዊ ምግባር ጣፋጭ ፍሬ የኾነው ንስሓ፡ ቸሩ እግዚአብሔር፡ እንደእናንተና እንደእኔ፡ በንስሓ ለሚመለሱ የሰው ልጆች፡ የኃጢአታቸው ፍጹም ማስተስረያ ይኾን ዘንድ፡ እውነተኛው ቁርባንና የዘለዓለም መሥዋዕት አድርጎ፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያሳረገውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ለመቀበል የሚያበቃቸው ይኾናል።

በዚህ ቅዱስ ሥርዓት፡ ከቸሩ ፈጣሪያችን፡ የኃጢአታችንን ሥርየት አግኝተን፡ በሥጋና በደም ብቻ ሳይኾን፡ በነፍስና መንፈስ ጭምር፡ ለመለኮታዊው አንድነት ስለምንበቃ፡ በዚያን ጊዜ፡ በእየኹለንተናችን ስለሚሰማን ደስታና ሰላም÷ ደኅንነትና እርካታ፡ እየራሳችን፡ በእየውስጣችን፡ ከምንገነዘበው በቀር፡ በሰው አንደበት÷ ወይም በብዕር ልሣን ሊገለጽ አይቻልም፡ ምሥጢር ኾኖ ይቀራል።

ማጠቃለያ።

የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ!

ጥያቄ፡- እንግዲህ፡ "'እኔ' የምለው እኔነቴ፡ ማነው?" ለሚለው ጥያቄ፡ እስካኹን ባገኘነው ሓተታ፡ መልሱ ተሰጥቶን፡ ይኸው፡ "እኔነታችንን" ለሚወቅ በቅተናል። ይህም ኹሉ፡ እንዲህ ሊሳካልንና ሊኾንልን የቻለው፡ በአንተ መሣሪያነትና አገልጋይነት ነው። ቀደም አድርገህ እንዳስረዳኸን፡ ምስጋና የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ መኾኑን በማወቅ÷ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ አንዱ፡ ለሌላው፡ ያደረገውን አውቆ፡ ተገቢውን ውለታ ሊከፍል፡ ሥልጣንና ችሎታ ያለው፡ እግዚአብሔር ብቻ መኾኑንም በመገንዘብ፡ "እግዚአብሔር ይስጥልን!" እንላለን። እኛም አኹን፡ በዚህ፡ በሚያኮራው ባህላችን፡ እጅግ ደስተኞች መኾናችንን እየገለጽን፡ ፈቃደኛ ኾነህ፡ እኛን በማነጋገር፡ ይህን በጎ ምግባር ስላደረግህልን፡ "እግዚአብሔር ይስጥልን!" እንልሃለን።

ለእኛ ያስገኘህልን፡ ይህ መልካም እውቀት፡ በእኛ ዘንድ ብቻ ተወስኖ ሳይቀር፡ እኛን ለመሰሉት ኢትዮጵያውያን ጭምር እንዲደርስ፡ "በመጽሓፍ መልክ ታትሞ ቢሠራጭ!" እያልን፡ ከማሳሰብ ጋር÷ እስካኹን ላቀረብንልህ ጥያቄዎቻችን፡ አጠቃላይ መልስ የሚኾን መልእክት ካለህ፡ ብታሰማን?

መልስ፡- ደስ ይለኛል። ይህን አጠቃላይ መልስ፡ እናንተን፡ ኹሉታችሁንም በሚያካትተው፡ "የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ!" በሚለው ቃል እጀምረዋለሁ፡ እንዲህ እያልሁም እቀጥለዋለሁ፡- "ምንነታችሁንና ማንነታችሁን ለይታችሁ ልታውቁ የምትችሉበት ግልጽ ገበታ፡ እነሆ ቀርቦላችኋል። ይኸውም፡-

በመጀመሪያ፡- ወንድና ሴት ኾናችሁ፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠራችሁ፡ "ሰው" የተባለው ፍጡር መኾናችሁን ነው።

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
ማጠቃለያ፤
የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ!

ይህም ማለት፡ አራቱን ባሕርያተ ሥጋ የለበሰችው "እኔነታችሁ"፡ በሦስቱ የነፍስ ባሕርያት፡ ከእግዚአብሔር እስትንፋስ የተገኘች መኾኗን፥ እንዲሁም፡ ይህች ረቂቅ መንፈሳዊት አካልና በሞት እስክትለየው ድረስ፡ በዚህ ዓለም ገዝፋ እንድትታይበትና ሃይማኖቷን በምግባር እንድትገልጽበት፡ ከማሕፀን ጀምራ ተዋሕዳ የለበሰችው፡ "ሥጋ" የተባለው መሬታዊ አካል፡ ኹለቱም፡ እንዲህ፡ በሥነ ፍጥረት፡ ከእግዚአብሔር ያገኛችኋቸው፡ የሰውነታችሁ ክፍሎች መኾናቸውን አውቃችኋል። ስለዚህ፡ በዚህ ኹለንተናችሁ፡ ማለትም፡ በሥጋችሁም ኾነ በነፍሳችሁ፡ ጤናማ ሕይወት ይኖራችሁ ዘንድ፡ የእርሱን፡ የፈጣሪያችሁን፡ የሃይማኖትና የምግባር መመሪያ ቃላት ተከትላችሁ፡ ኹለቱንም፡ በትክክልና በጥንቃቄ ልትጠብቋቸው ይገባችኋል።

ቀጥሎ፡- ከዓለም ሕዝቦች መካከል ተለይታችሁ የምትታወቁበት፡ "ኢትዮጵያዊ፥ ኢትዮጵያዊት" የሚል መጠሪያ ያላችሁ መኾናችሁን ነው፤ ይህም ማለት፡ የኖኅ ልጆች ከኾኑት፡ ከካም፥ ከሴምና ከያፌት ነገዶች ፍጹም ውሕደት ከተገኘው፡ ከፊተኛው መልከ ጼዴቅ ሠርጸ፡ በኋለኛው መልከ ጼዴቅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ከተፈጸመው "ኢትዮጵያዊነት" የተወለዳችሁ መኾናችሁን አውቃችኋል፤ ስለዚህ፡ ይህ ወገን፡ ቀድሞ፡ በሃይማኖታቸውና በምግባራቸው ብቅዓት ምክንያት፡ ለቅዱሱ ኪዳን ተቀባይነት፥ ባላደራነትና ባለቤትነት፡ በፈጣሪያቸው የተመረጡትን፡ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችሁንና እናቶቻችሁን ያስገኘ ሲኾን፡ ዛሬ ደግሞ፡ ይኸው፡ በእናንተ ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ ገዝፎና ሕያው ኾኖ ይታያል።

በመጨረሻ፡- ጥንት ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በኪዳነ ልቦና ተወጥኖላችሁ፡ ኋላ፡ በኪዳነ አሪት የጸናላችሁንና በፍጻሜ ዘመን፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ጸጋ በጥምቀት አግኝታችሁ፡ በስመ ክርስትናችሁ የታወቃችሁና በእግዚአብሔር መንግሥት የሕይወት መጽሐፍ የተመዘገባችሁ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት" ናችሁ።

ይህን ዓቢይ ቁም ነገር፡ ራሳችሁ አውቃችሁ፥ ልጆቻችሁም እንዲያውቁት አድርጉ! ራስን ማወቅና መውደድ ማለት፡ ይህ ነውና።

"ኢትዮጵያ ታብጽሕ፡ እደዊሃ፡ ኀበ እግዚአብሔር!"፡ ማለትም፡ *"ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!"* የተባለው ትንቢት የተፈጸመው፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ዘርግታ፡ አምላክን በማሕፀኗ በመቀበል፡ እናቱ ለመኾን በበቃችው፡ በንግሥት እናታችን፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ነው። የቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜና ዘለዓለማዊው መልከ ጼዴቅ የኾነው፡ እርሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስም፡ ፍጹም ሰው ኾኖ፡ መላውን የሰው ዘር ያዳነው፡ ከካም፥ ከሴምና ከያፌት የውሕደት ዘር ከተገኘው፡ ከእርሷ ኢትዮጵያዊ ማሕፀን ተወልዶ ነው።

ስለዚህ፡ እርሱ፡ "እግዚአብሔር" ሲኾን፡ እርሷ ደግሞ፡ "ኢትዮጵያ" ናት። እናንተም፡ ከዚሁ ኢትዮጵያዊ ዘር የተገኛችሁ እንደመኾናችሁ፡ በልጇ የአደራ ቃል፡ እርሷ፡ ለእናንተ ያላትን፡ የቃል ኪዳን እናትነት፥ እናንተም ለእርሷ የተሰጣችሁበትን የቃል ኪዳን ልጅነት፡ አምናችሁበት የምትኖሩ ናችሁ።

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት
"'እኔ' የምለው እኔነቴ፡ ማነው?"

እንዲህ በመኾናችሁ፡ "ኢትዮጵያ" የተባለችውና "ኢትዮጵያ"ን ኾና የተገኘችው፡ የእርሷ፡ የድንግል ማርያም ልጆች ናችሁ። ይህን፡ መሠረታዊ እውነት፡ *"የእስራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ፡ ለእኔ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?' ይላል እግዚአብሔር፣"* የሚለው የነቢያት ቃል፡ ለዓለሙ ኅብረተሰብ ገሃድ አድርጎ አረጋግጦታል፤ እናንተ "የኢትዮጵያ ልጆች"፡ ከ"እስራኤል ልጆች" በፊት፡ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቃችሁና የተወደዳችሁ መኾናችሁንም፡ ይኸው የነቢያት ቃል፡ አብራርቶ ተናግሩዋል።

ይህ እውነታ፡ በተጨማሪ የሚረጋገጥበት ሌላ ድንቅ መለኮታዊ ድርጊት አለ፡ ይኸውም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የትውልድ አባት የኾነው፡ የእግዚአብሔር ካህንና የሰላም ንጉሥ የተባለው፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መሪ የነበረው "መልከ ጼዴቅ"፡ "የእስራኤል ልጆች" የትውልድ አባት የኾነውን "አብርሃምን" መባረኩና በግርዛት ምልክትነት ጸንቶ እንዲቀጥል ለተደረገው ለመለኮታዊው ቃል ኪዳን ማብቃቱ ነው።

ከዚህ ጋር የሚያያዘው፡ ሌላው ድንቅ መለኮታዊ ድርጊት ደግሞ፡ የእስራኤላውያን ነቢይ፡ ሙሴ፡ "የእስራኤልን ልጆች" ከግብፃውያን የባርነት አገዛዝ ቀንበር አውጥቶ፡ ወደምድረ ከነዓን የመራቸው፡ ወደኢትዮጵያ መጥቶና ኢትዮጵያዊት ሚስት፡ ይህችውም፡ የኢትዮጵያዊዉ ካህን፡ የዮቶር ልጅ የኾነችውን፡ ሲጻራን አግብቶ፡ በኢትዮጵያ ከኖረና፡ የእግዚአብሔርን ምሥጢራዊ ነገር፡ "ከኢትዮጵያ ልጆች" ተምሮ፡ መለኮታዊዉን እውቀት ካደላደለ በኋላ መኾኑ ተመዝግቧል።

ይህም፡ በዚያ የምድረ በዳ ጕዟቸው ጊዜ፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓተ መንግሥት፡ ማለትም፡ "ቤተ ሕዝብ" የሚባለውን መሠረታዊ፥ ኅብረተሰባዊና ኹለንተናዊ አቋምና አመራር፥ "ቤተ ክህነት" የሚባለውን፡ የአምልኮ፥ የትምህርትና የዳኝነት ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ አገልግሎት፥ "ቤተ ምልክና" የሚባለውን የተግባረ ሰብ፥ የማኅበራዊ ኑሮና የአስተዳደር ምግባራዊና ሥጋዊ አገልግሎት፡ ለእስራኤላውያን ያስተማራቸው፥ መጻሕፍተ አሪትን፡ በተለይም፡ አሪት ዘፍጥረትን የጻፈው፡ ከኢትዮጵያ ኑሮውና ትምህርቱ በኋላ መኾኑ በመረጋገጡ ታውቋል።

እንዲሁም፡ በሥጋ ዘርና በሃይማኖት ፍሬ፡ ለአብርሃም፥ ለሙሴና ለዳዊት፡ በዳዊትም በኩል፡ ለሰሎሞን፡ የተሰጡት፡ እነዚህ ሦስት መለኮታውያን ቃል ኪዳናት፡ ከአባቶቻችሁና እናቶቻችሁ ሲያያዙ መጥተው፡ ከእናንተ የደረሱት፡ ለእነዚህ ቃል ኪዳናት ተቀባዮች ለኾኑት ቅዱሳን አባቶች፡ ሚስቶች ኾነው፡ ልጆችን በወለዱላቸው፡ ኢትዮጵያውያት በኾኑት እናቶቻችሁ፡ በአብርሃሚ ኬጡራ፥ በሙሴዋ ሲጻራና በሰሎሞኗ ማክዳ ማሕፀኖች አማካይነት መኾኑ፡ ሌላው ድንቅ መለኮታዊ ድርጊት ነው። በዚህ ረገድ የተከሠተውና ከኹሉም የሚልቀው መለኮታዊ ትንግርት፡ ድንግል ማርያም፡ ኢትዮጵያዊት መኾኗን፡ በሚያስተማምን መልክ ለማረጋገጥ፡ የእርሷና የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻ አርአያና ጥላ የኾነችው፡ የጽላተ ሕጉ ማደሪያ የኾነችው ታቦተ ጽዮን፡ ወደኢትዮጵያ መጥታ፡ እስከዘመነ ሥጋዊ፡ ማለትም፡ "ቃል ሥጋ ኾነ!" እስከተባለባት ቅጽበት ድረስ፡ በ"ኢትዮጵያ ልጆች" ዘንድ ተጠብቃ ስትመለክ መኖርዋ፡ እዚህ ላይ ሊመሳሳችሁ ይገባል።

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
ማጠቃለያ፤
የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ!

የቃል ኪዳናቱ ወደኢትዮጵያ ፈልሰው መግባትና የዘር ውሕደቱ የተከናወነው፡ ታቦተ ጽዮን፡ ወደኢትዮጵያ በመጣችበት ዘመን፡ ከዚያ በፊትና ከዚያ በኋላም፡ በነበሩት ዘመናት፡ በእግዚአብሔር ተመርጠውና ተጠርተው፡ ወደኢትዮጵያ በገቡት÷ ከኢትዮጵያውያንም ጋር በጋብቻ እየተዛመዱ በተዋሐዱት እስራኤላውያን አባቶች አማካይነት ጭምር መኾኑን እንድታስተውሉት ያስፈልጋል።

በፈጣሪያችሁና በአምላካችሁ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ እናንተ፡ እንዲህ እንድትወደዱ ያደረጋችሁ፡ መልከ ጼዴቅን÷ ንግሥት ማክዳን÷ ኢትዮጵያዊዉን፡ የብሉዩን ኪዳን አቤሜሌክ÷ "ኢትዮጵያዊዉ ጃንደረባ" የተባለውን፡ የአዲስ ኪዳኑን አቤሜሌክና በዘመኑ፡ የኢትዮጵያ ንግሥት የነበረችውን፡ ሕንደኬን የመሰሉት የዘር አባቶቻችሁና እናቶቻችሁ፡ ቀድሞ፡ በኪዳነ ልቦና÷ ቀጥሎ፡ በኪዳነ አሪት÷ በመጨረሻም፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ የተቀበሉትን ሃይማኖታቸውንና አምልኳቸውን÷ በአጠቃላይም፡ ቅዱሱን ኪዳን በመጠበቅ፡ እግዚአብሔርን ደስ ስላሰኙት መኾኑን አትርሱ! ስለዚህ፡ እናንተም፡ ከእነርሱ የወረሳችሁትን፡ የምንነታችሁና የማንነታችሁ መታወቂያና መለያ የኾኑትን፡ ይህች "ኢትዮጵያችሁን" እና ይህን "ኢትዮጵያዊነታችሁን"፡ በነጻነትና በሰላም÷ በብልጽግናና በመልካም ሕይወት፡ ለዘለዓለም ትኖሩባቸውና ትጠሩባቸው ዘንድ፡ እንደሃይማኖት አጽንታችሁ÷ እንደምግባርም አቅንታችሁ፡ ልትጠብቋቸውና ልትወዷቸው÷ ልታከብሩዋቸውም ይገባችኋል።

ይህን፡ የኢትዮጵያዊነት ግዳጃችሁን ለመፈጸም ትችሉ ዘንድ፡ ቀደም ብሎ፡ ሰፊ ሐተታ የተሰጠበትና ከፈጣሪያችሁ የታደላችሁት፡ ፍቱን መሣሪያና የማይበገር ኃይል አለ። እርሱም፡ በቅድሚያ፡ የእየራሳችሁን ምንነትና ማንነት በትክክል በማወቅ፡ የሰውነታችሁን ጤንነትና የኢትዮጵያዊነት ስማችሁን ለመጠበቅ÷ ቀጥሎ፡ የነፍሳችሁን ፈቃድና የሥጋችሁን ፈቃድ፡ እነዚህን ኹለት ተጻራሪ ፈቃዳት፡ በአንዱ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ አስማምታችሁ፡ ለእግዚአብሔር ፈቃድ በማስገዛት፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ሰላም አግኝታችሁ፡ እውነተኛዋን መልካም ኑሮ ለመኖር የምትችሉበት፡ "ጾም" የተባለው ምሥጢራዊ ምግባር ነው።

ስለዚህ፡ ፈጣሪያችሁ፡ ሰው ኾኖ፡ ስለጾም ያስተማራችሁን እያስባችሁ፡ አባቶቻችሁና እናቶቻችሁ ሲያደርጉት እንደቆዩት፡ እናንተም፡ በዚህ ክፍል ውስጥ፡ የተዘረዘሩትን አጽዋማት፡ ቀደም ብዬ ባብራራሁላችሁ መሠረት፡ አቅማችሁ በፈቀደ መጠን፡ ጹሟቸው! ጾምም፡ እስካኹን እንደተረዳችሁት፡ ራስን፡ ከእህልና ከውኃ መለየት ብቻ ሳይኾን፡ እስከተቻለ ድረስ፡ ክፉን ነገር ከማሰብ÷ ከመናገር ወይም በማናቸውም መንገድ ከመግለጽና ከማድረግ መከልከል ጭምር መኾኑን አትዘንጉ! በተፈጥሮአችሁ ደካማነት ምክንያት፡ ከዓቅማችሁ በላይ ኾኖባችሁ፡ የሠራችሁት ጥፋት÷ በደል ወይም ኃጢአት ቢኖር፡ ኹሉንም፡ ፈጥናችሁ፡ በንስሓ ደምስሱት!

\+ + +

ጊዜያዊ መሰናበቻ

"እኔ" የምለው እኔነቴ፡ ማነው? የሚለው፡ የዚህ ውይይት፡ የመጀመሪያ ክፍል፡ በዚህ አበቃ።

ይኸው ውይይት፡ በኹለተኛው ክፍል፡ በዚሁ መልኩ እንዲቀጥል፡ ከአዳምና ሔዋን ጋር ተስማምተን፡ ከዚህ ያደረሰን ቸሩ እግዚአብሔር፡ ለሚቀጥለው ቀጠሮአችንም እንዲያበቃን ጸልየን፡ በተለመደው አሸኛኘት፡ በፍቅር ተሳስመን፡ ተለያየን።

\+ + +

ክፍል ኹለት

"ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር ማነው?

እና

ክፍል ሦስት

"ባልንጀራዬ" የምለው ፍጡር ማነው?

በሚል አርእስት የተዘጋጁት

ዳግማዊው መጽሐፍና ሣልሳዊው መጽሐፍ፡

በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት፡

ከዚህ ቀጥለው፡ በመከታተል እየታተሙ ይወጣሉ።

የክፍል አንድ:

ጥቅሶችና ማብራሪያዎች::

፩ "ጉያ":- በኢትዮጵያኛ: "የውስጥ ዕቅፍ"÷ በግእዝ ደግሞ: "ስደት" ማለት ነው፤ ይህ መጽሓፍ: ስለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱ: በፈተናና በመከራ: እየተሰደደና እየተንገላታ÷ እየታገለም ላለ ሰው: ሲቀመጥ: ከእጹ÷ ሲጓዝ: ከጉያው÷ ሲተኛ: ከራስጌው የማይለየው: ጓዱ ስለኾነ: "የጉያ መጽሓፍ" ተብሏል::

፪ "ኢትዮጵያዊ" እና/ወይም "ኢትዮጵያውያን" ተብሎ: በዚህ መጽሐፍና በሌሎቹም ድርሰቶቼ ውስጥ: በወንድ አንቀጽ የተጻፈው ኹሉ: በነጠላና በብዙ: የሴትንም ያጠቃልላል:: ይህም የኾነው: *"እግዚአብሔር: ሰውን: በመልኩ ፈጠረ: በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው!"* የሚለውን የመጽሓፍ ቃል በመከተል ነው:: ኤር. ፲፰÷ ፳፫::

፫ ዮሐ. ፲፯÷ ፳፩-፳፪::

፬ ዘፍጥ. ፱÷ ፳-፲፯::

፭ መዝ. ፵፯÷ ፴፩:

፮ ራእ. ፭÷ ፮::

፯ ማቴ. ፯÷ ፳፬-፳፯::

፰ ማቴ. ፲፯÷ ፳፯::

፱ ዮሐ. ፬÷ ፳፬::

፲ ማቴ. ፳፬÷ ፲፭:: ኤር. ፯÷ ፩-፳፤ ፳÷ ፬-፯:: ራእ. ፳፩÷ ፳::

፲፩ ዘጸአ. ፳÷ ፩-፯::

፲፪ ከአሜሪካዊቷ ሴት የተገኘው: "የአዳምና ሔዋን ውድቀት" የሚል ስያሜ የተሰጠው ጠልሰም ብርሃናዊ ቅጂ እና ከእርሷ ጋር የተጻጻፍናቸው ደብዳቤዎች: በዚህ መጽሓፍ አሳታሚ ድርጅት ጽሕፈት ቤት ይገኛሉ::

<u>ጠልሰም</u>:- ጠንቋዮች÷ አስማተኞችና ሟርተኞች: በክታብ ውስጥ የሚሥሉት: በያይነቱ: የአስማትና የሓረግ ሥዕል ነው::

<u>ሾተላይ</u>:- በሴቶች ማሕፀን እያደረ: ወንዶችን የሚገድል÷ ሕፃናትን: ሲወለዱ: የሚያጨናግል÷ ወይም: የሚያጨናግፍ በሽታ::

<u>ምናሴ: የመከራዬ ደስታ: ዓለምን ረታ!</u> የሚለው መጽሓፌ: በአሜሪካ ምክር ቤት ቤተ መጻሕፍት: በጠንካራ ገፀታ ተጠርዞ አግኝተነዋል::

፲፫ ፪ቆሮ. ፮÷ ፲፩-፲፮::

፲፬ ራእ. ፳÷ ፩-፫፤ ፮-፲::

፲፭ ኤፌ. ፮÷ ፲-፲፰::

፲፮ ዘፍጥ. ፲፰÷ ፳፱-፴፱::

ገፅ ሉቃ. ገጽ÷ ፰።
ገፅ ኤር. ዕብፀ÷ ዕብፃ-ዕብዕ።
ገጽ ማቴ. ገፀፀ÷ ዕብዐ።
ገዐ ማቴ. ገ÷ ገ።
ጰ ዮሐ. ጌ÷ ዕብሯ።
ጰሰ ማቴ. ዮ÷ ገ፡ ጌ÷ ገዐ። የዮቱ ደቂቅ ጸሎት ዮ-ገ፡ ገዐ-ገጌ።
ጰፀ ስለአኮስም ጽዮን ንቡረ እድነት፡ ማብራሪያው፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው መጽሐፌ፡ በገጽ ፩፻ገዐ-፩፻ጰፀ ላይ ይገኛል።
ጰዮ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፡ በእየበታው፡ አስፈላጊ ኾኖ፡ ተለይቶ ካልተገለጸ በቀር፡ "ድርሰቴ"÷ ወይም፡ "ድርሰቶቼ" ስል፡ Ethiopia: The Classic Case÷ "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!" እና "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" የተባሉትን፡ እንደቅደም ተከተላቸው፡ በገዐዐ፻፯ ዓ. ም. (1997)÷ በገዐዐ፻፺፩ ዓ. ም. እና በገዐዐ፻ዘዐ ዓ. ም. የታተሙ መጻሕፍቴን መጥቀሴ ነው።
ጰፀ ዘጸአ. ገዐ÷ ፫-፮። ፩ጴጥ. ፪÷ ፱። ራእ. ፩÷ ፮።
ጰ፫ ማቴ. ፫÷ ገ።
ጰ፮ "አዳምና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!" ስለሚለው ድርሰት፡ አጭር መግለጫ፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው መጽሐፌ፡ በገጽ ፬፻ጰ፫-፬፻ጰ፮ ላይ ይገኛል።
ጰ፯ ፩ነገ. ገዐ፡ ገ፬-ገ፰። ሮሜ. ገ፩÷ ገ-፮።
ጰጰ ኤር. ዕብ፩÷ ዕብ፬።
ጰፀ ዮሐ. ገ፡ ገዐ-ጰ፩÷ ፰÷ ዕብ፩-ዕብ፪። ፩ኛ ዮሐ. ፬÷ ገ፰።
ፀ ማቴ. ጰ፬÷ ዕብሯ-ዕብ፪።
ፀሰ "ጴጥሮስ! ያቺን ሰዓት!" የጸጋዬ ገብረ መድኅን ተውኔት።
ፀፀ የሙሶሊኒ ወረራ በኢትዮጵያ፡ በአልቤርቶ ስባኪ÷ ትርጉም፡ ጋረደው ደምሴ ኃይሉ፡ ገጽ ፵፰።
ፀዐ ማቴ. ፮÷ ፩-፪።
ፀ፬ ገላ. ገ÷ ፩።
ፀ፮ "ግእዝ"፡ ኢትዮጵያውያን፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከዛሬ ጠብቀው የሚጠቀሙበት÷ ራሱን የቻለ÷ ፊደል ያለው÷ የመጀመሪያው የሰው ልጆች ቋንቋ ነው፡ ይህም፡ በባዕዳን ተመራማሪዎች ዘንድ ሳይቀር ታውቋል። ስለ"ግእዝ"፡ በበለጠ ለመረዳት፡ ሓተታው፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው መጽሐፌ፡ በገጽ ፬፻፩-፬፻ገዐ ላይ ይገኛል።
ፀ፯ ኢሳ. ፵፬÷ ገገ። ኤር. ፩÷ ፬-ገ፡ ዕብ፩÷ ዕብ፩-ዕብ፬። ማቴ. ገ÷ ገ፮-፳፫÷ ገ፳÷ ፭-፱። ዮሐ. ፳÷ ዕብ፱-ፃ እና ፃ፳-ፃ፵፡ ፮÷ ፃ፳÷ ፯÷ ገ፬-ገ፯÷ ገ፬÷ ገ፮። የሐዋ. ፬÷ ገገ-፳። ገላ. ፩÷ ገ-ገ፮። ፩ቆሮ. ፪÷ ገ፬-ገ፮።
ፀ፯ ማቴ. ፳÷ ገ ገ፮። ዮሐ. ፳÷ ፃገ-ፃ፯÷ ገ፳÷ ገ፳-ገ፱።
ፀ፳ ማቴ. ፮÷ ፃገ። ዮሐ. ፪÷ ፳።
ፀ፬ ማቴ. ፳፩÷ ፃገ።

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት
የክፍል አንድ፡ ጥቅሶችና ማብራሪያዎች።

፩ ማቴ. ፲፯÷ ፲፰። ዮሐ. ፩÷ ፳፫-፳፬። የሐዋ. ፭÷ ፴፯።
፩ቆሮ. ፫÷ ፲፯-፲፯። ፪ቆሮ. ፮÷ ፲፯።

፲፭ ዘፍጥ. ፩÷ ፳፯።

፲፯ ኤር. ፴፩÷ ፴፩-፴፬።

፲፰ ማቴ. ፲፫÷ ፵፫።

፲፱ ሆሴ. ፬÷ ፮። የሐዋ. ፲፯÷ ፳፪-፳፫ እና ፴።

፳፭ ምሳ. ፩÷ ፯። መዝ. ፻፲÷ ፩።

፳፯ መዝ. ፲፫ ÷ ፪።

፳፯ ፩ቆሮ. ፪÷ ፲፬-፲፭።

፳፰ ማቴ. ፮÷ ፳፭-፴፫።

፳፱ ዘፍጥ. ፩÷ ፩-፳፭።

፩ መዝ. ፻፫÷ ፬። ዕብ. ፩÷ ፯፤ ፲፬-፲፱።

፭፩ ዘፍጥ. ፩÷ ፩-፪÷ ፲፬-፲፱። መዝ. ፹፱÷ ፬። ፪ኛ ጴጥ. ፫÷ ፭።

፭፪ ራእ. ፲፪÷ ፯-፱። ዘፍጥ. ፩÷ ፪። ትርጓሜ ቅዱሳት መጻሕፍት፤ ድርሳነ ገብርኤል።

፭፫ ዘፍጥ. ፩÷ ፳፯-፴፩፤ ፪÷ ፩-፳፭፤ ፫÷ ፩-፳፬።

፭፬ ማቴ. ፭÷ ፴፯- ፵፭፤ ፳፭÷ ፵፡ ፵፭። ዮሐ. ፲፬÷ ፳፫።

፭፭ ማቴ. ፲፭÷ ፲-፲፬።

፭፮ ዘፍጥ. ፯÷ ፭-፯።

፭፯ ዘፍጥ. ፲፭÷ ፲፬። ማቴ. ፲፱÷ ፳፯። ሉቃ. ፩÷ ፴፯።

፭፰ ሮሜ ፯÷ ፲፬-፳፭፤ ፭÷ ፩-፲፩።

፭፱ ማቴ. ፳፭÷ ፴፬ እና ፵፩። ፩ቆሮ. ፲፭÷ ፶፩-፶፪። ፩ተሰ. ፬÷ ፲፫-፲፯።

፮ ኤር. ፲፫÷ ፳፫። መዝ. ፵፯÷ ፴፩፤ ፹፯÷ ፭። አሞ. ፱÷ ፯።

፮፩ ሉቃ. ፩÷ ፵፯-፷፪።

፮፪ ዘፍጥ. ፪÷ ፳፩-፳፭፤ ፱÷ ፭-፲፯፤ ፲፬÷ ፲፭-፳፤ ፲፯÷ ፩-፲፬፤ ፵፱÷ ፭-፲፪። ዘዳግ. ፭። ፪ሳሙ ፯÷ ፭-፲፯። ራእ. ፭። ማቴ. ፲፱÷ ፬-፯፤ ፳፯÷ ፳፯-፴፱። የሐዋ. ፫÷ ፳፭።

፮፫ ኤር. ፴፩÷ ፴፩-፴፬።

፮፬ ዘፍጥ. ፬÷ ፩-፲፯፤ ፯÷ ፩-፭።

፮፭ ዘፍጥ. ፩÷ ፳፯-፳፰፤ ፪÷ ፳፫-፳፬። ማቴ. ፲፱÷ ፭-፯።

፮፮ ዘፍጥ. ፪÷ ፳፭-፳፰። ማቴ. ፩÷ ፲፰-፳፫። ሉቃ. ፩÷ ፳፯-፴፭ ፮፯
ዘፍጥ. ፪÷ ፯፤ ፫÷ ፩-፲፱። ሮሜ ፭÷ ፲፪-፳፩። ፩ቆሮ. ፲፭÷ ፳፪፤ ፶፭-፶።

፮፯ ዘፍጥ. ፩÷ ፳፯-፴፤ ፫÷ ፳፪-፳፬። መዝ. ፶፬ (፶፭)። ማቴ. ፳፰÷ ፲፰።
ሉቃ. ፩÷ ፳፯-፴፭፤ ፶፯-፷፭። ፩ጴጥ. ፫÷ ፳፪።

፮፰ ዘፍጥ. ፫÷ ፲፬-፲፭። ራእ. ፲፪።

፰ ዘፍጥ. ፪÷ ፳-፳፭፤ ፫÷ ፩-፭። ዮሐ. ፯÷ ፳፭-፴፬። ማቴ. ፳፬÷ ፳፬።

ዘፍጥ. ፱÷ ፮-፲፯፣ የረቡዕ ውዳሴ ማርያም።
ዘፍጥ. ፭÷ ፳፬። ፩ጴጥ. ፫÷ ፳-፳፩።
ዘፍጥ. ፲፬÷ ፲፮-፳። ዕብ. ፯÷ ፩-፬።
ዕብ. ፯÷ ፩-፲፯፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ÷ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፡ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ ገጽ ፪፻፲፯።
፩ ነገ. ፲÷ ፩-፲፫። ማቴ. ፲፪÷ ፵፪። የሐዋ. ፯÷ ፳፯-፵።
፪ቆሮ. ፱÷ ፩-፲፪።
መዝ. ፹፯÷ ፬፣ በግእዙ መጽሐፍ።
ማቴ. ፩። ሉቃ. ፩÷ ፳፯-፴፮፣ ፫÷ ፳፫-፴፰።
ዘፍጥ. ፲፬÷ ፲፮-፳። የሐዋ. ፯÷ ፳፯-፴፭። ዕብ. ፯÷ ፫።
መዝ. ፷፪÷ ፱-፲፩፣ ፷፬÷ ፲፪-፲፬። በግእዙ መጽሐፍ።
ሮሜ ፱÷ ፳-፳፩።
ዘፍጥ. ፲፯÷ ፫-፲፪።
ዘፍጥ. ፲፫÷ ፮።
ማቴ. ፫÷ ፯-፲። ዮሐ. ፯÷ ፴፩-፵፯። ያዕ. ፪÷ ፳-፳፮።
ዘፍጥ. ፳ እና ፳፩፡ ፩-፭፡ ፳፪-፳፬÷ ፴፪ እና ፴፬፣ ፳፭÷ ፩-፬። ዘጸአ. ፪÷ ፲፭-፳፪። ዘኍል. ፲፪÷ ፩-፲፮። አሞ. ፱÷ ፯። ዕንባ. ፫÷ ፯።
አዴ ገላውዴዎስ፡ ለካቶሊካውያን የሰጠው፡ የሃይማኖት መግለጫ፡ የዚህ መጽሐፍ ተከታይ በኾነው፡ በኹለተኛው ክፍል ይገኛል።
ዘጸአ. ፲፱÷ ፭-፮÷ ፳÷ ፩-፲፯።
፪ዜና. ፴፮። አሞ. ፱÷ ፯።
ዘጸአ. ፪÷ ፩-፳፪፣ ፫÷ ፩-፲፱። ዕብ. ፲፩÷ ፳፬-፳፯።
ዘጸአ. ፲፰÷ ፩-፳፯።
ዘኍል. ፲፪÷ ፩-፲፫።
መዝ. ፻፴፩÷ ፲፫-፲፱። መኃ. ፩÷ ፭-፮÷ ፬÷ ፲፪። ማቴ. ፲፪÷ ፵፪። ዮሐ. ፩÷ ፲፬።
ዮሐ. ፳÷ ፳፱።
ዘጸ. ፴፪÷ ፩-፲፬።
ሕዝ. ፫÷ ፲፯-፲፱።
ዮሐ. ፩÷ ፩-፲፰።
ኤር. ፫÷ ፲፯-፲፯። ራእ. ፲፩÷ ፲፱፣ ፲፪÷ ፩-፮።
Coulbeaux, J.B. Histoire Politique et Religieuse d'Abyssinie, 3 vols., pp. 459-464, (Paris, 1929)
ራእ. ፲፩÷ ፲፱።
ዮሐ. ፬÷ ፳፭።
ኤር. ፴፩÷ ፴፩-፴፬። ዮሐ. ፮÷ ፵፭። ዕብ. ፰÷ ፰-፲፪። ፩ቆሮ. ፫÷ ፲፯-፲፯። ፪ቆሮ. ፮÷ ፲፮።

፲፩ የሐዋ. ፰÷ ፴፰-፴፱።

፲፪ ሉቃ. ፩÷ ፴-፴፰። ራእ. ፲፩÷ ፲፱፤

፲፫ ውዳሴ ማርያም፡ የረቡዕና የእሑድ÷ አንቀጸ ብርሃንና ቅዳሴ ማርያም፡ ሥርዓተ ቅዳሴ።

፲፬ ዮሐ. ፩÷ ፩-፲፰። ራእ. ፲፩÷ ፲፭-፲፱፤ ፲፪÷ ፩-፲፯።

፲፭ ኢሳ. ፳፱÷ ፲፫። ማቴ. ፲፭÷ ፯-፱።

፲፮ ፩ኛ ቆሮ. ፫÷ ፲፯።

፲፯ ገላ. ፩÷ ፳።

፲፰ ፪ሳሙ ፯÷ ፳-፲፯። ዘፍጥ. ፵፱÷ ፳-፲፪። ራእ. ፭። ሉቃ. ፩÷ ፴-፴፫።

፲፱ ሉቃ. ፲፯÷ ፳-፳፩።

፳፩ ሮሜ ፲፫÷ ፩-፯።

፳፲፩ ማቴ. ፲፪÷ ፴፯-፵፪። የሐዋ. ፳÷ ፳፯-፵።

፳፲፪ ዮሐ. ፯÷ ፬-፳፬።

፳፲፫ ዘኍል. ፲፪÷ ፩-፲፭። ፩ሳሙ. ፳÷ ፬-፳፪። ዮሐ. ፲፳÷ ፴፫-፵።

፳፲፬ ዘኍል. ፲፪÷ ፩-፲፭። ማቴ. ፩÷ ፩-፲፯። ሉቃ. ፫÷ ፳፫-፴፳።

፳፲፭ ዮሐ. ፩÷ ፲፬። ሉቃ. ፩÷ ፭-፯፤ ፴፩-፴፯።

፳፲፮ ዘፍጥ. ፫÷ ፲፭። ኢሳ. ፯÷ ፲፬።

፳፲፯ ራእ. ፲፪÷ ፩-፯። መዝ. ፻፴፩÷ ፲፫-፲፬፤ ፻፯÷ ፴፩። አሞ. ፱÷ ፯።

፳፲፰ ማቴ. ፲፫÷ ፶፬-፶፯። ማር. ፯÷ ፪-፫። ሉቃ. ፬÷ ፳፪። ዮሐ. ፯÷ ፵፩-፵፪፤ ፩÷ ፵፯፤ ፯÷ ፵፪።

፳፲፱ ኤር. ፴፱÷ ፲፭-፲፯። ፪ ሳሙ. ፲፩÷ ፩-፳፯። ሩት. ፩-፬።

፳፳ ማቴ. ፪÷ ፲፬-፲፭። ሆሴ. ፲፩÷ ፩።

፳፳፩ ዮሐ. ፩÷ ፲፪-፲፫። ሉቃ. ፩÷ ፳፯-፴፭። መዝ. ፹፱÷ ፲፱-፴፭፤ ፻፴፪÷ ፲፩-፲፯።

፳፳፪ መዝ. ፹፰÷ ፪-፫። ዮሐ. ፩÷ ፳፱። ማቴ. ፳፯÷ ፳፯-፳፰።

፳፳፫ ዮሐ. ፲፭÷ ፳፱።

፳፳፬ አሞ. ፱÷ ፯።

፳፳፭ ኤር. ፴፫÷ ፯-፲፫። ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ከደስታ ተክለ ወልድ፣ ገጽ ፫፻፲፱።

፳፳፮ ዮሐ. ፫÷ ፫-፰።

፳፳፯ ዮሐ. ፳÷ ፳፱። የሐዋ. ፰÷ ፳፯-፴፱።

፳፳፰ የሐዋ. ፲÷ ፵፬-፵፯።

፳፳፱ ማቴ. ፲፯÷ ፲፫-፳። ዮሐ. ፳÷ ፳፱። የሐዋ. ፰÷ ፳፯-፴፱።


፳፴ ዮሐ. ፲፱÷ ፯-፲፯።

፳፴፩ ማቴ. ፲፪÷ ፵፱። ፩ነገ. ፲÷ ፩-፲፫።

፳፴፪ ዐም-ሐራ፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ÷ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ ገጽ ፫፻፳፯÷ ፬፻፷፬ እና ፯፻፲፷።

ማቴ. ፬: ፩-፲፩፣ ፲፭: ፲፯-፲፰:: ዮሐ. ፯: ፳፯::
ማቴ. ፲: ፳፪::
ማቴ. ፪: ፩-፳፩::
ዮሐ. ፫: ፲፱-፳፩፣ ፳: ፲፪፣ ፲፳: ፴፯::
ማቴ. ፳፩: ፱-፲፫::
ማቴ. ፳፯: ፳፯-፳፰፣ ፵-፵፩:: ዮሐ. ፲፫: ፲፪-፲፯፣ ፴፬-፴፭::
ማቴ. ፳፯: ፲፱-፳፯::
ማቴ. ፳፭: ፴፩-፵፯::
ሉቃ. ፳፫: ፴፬:: ዮሐ. ፲፯: ፴፫::
ማቴ. ፱: ፲፭:: የሐዋ. ፲፫: ፩-፫::
ዮሐ. ፩: ፲፬:: ራእ.፲፩: ፲፱፣፲፪::
ዘዳግ. ፭: ፯-፲:: ዮሐ. ፬: ፳፬:: ማር. ፲፪: ፳፱-፴::
ራእ. ፳፪: ፰-፱::
ማቴ. ፭: ፳፫-፳፬፣ ፯: ፲፬-፲፭፣ ፲፯: ፫-፭::

+ + + + + + +



ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር

ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት



